
ይስማዕከ ወርቁ
ዮራቶራድ

# የራቶራድ

Ethiopian Bookstore
t.me/etbookstore

ይስማዕከ ወርቁ

አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ፡ ፪፻፻፮ ዓ.ም

## መግለቢያ

ለአራተኛ ጊዜ ወደ ዴርቶጋዳ እንኳን በደህና መጣችሁ፡፡ ዴርቶጋዳ- ራማቶሓራ- ዣንቶዣራ- ዮራቶራድ... ተከታታይ ልቦለዶች መሆናቸውን ለመጠቆም ያህል እንጂ በር ላይ ቆሜ የአንባቢዬን ጊዜ የመሻማት አላማ አልነበረኝም፡፡ በፈጣሪ እርዳታ እና በአንባቢዎቼ ድጋፍ የኸረረቱ ፍሰት ቀጥሏል፡፡ አራተኛው ኸረረትም እነሆ ወንዙን ተቀላቅሏል፡፡ በዚህ አጋጣሚ፣ እነዚህን ተከታታይ ሥራዎች ለመሥራት ስወጣ ስወርድ የማያልቅ ቅንነታቸውን ያልነፈጉኝን ወገኖችና በተለያዩ የመገናኛ ዜዴዎች ሙያዊ ሂሶችን የሰጡኝን አካላት ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ በሌላ በኩል ግን ከሌላ አላማ በመነሳት ሥራዎቼን ጭቃ ለመቀባት ጊዜ የሚያባክኑትን አንዳንድ ወገኖች ልብ ይሰጣቸው ዘንድ እንድትፀልዩላቸው አንባቢዎቼን እማፀናለሁ፡፡ ይህን በዚህ ትተን ጊዜ ሳናባክን... ወደ ዮራቶራድ ለመብረር እያኮበኮብን ስለሆነ ቀበቶችሁን እንድታጠብቁ ትጠየቃላችሁ፡፡

ይስማዕከ ወርቁ-፳፻፲፮ ዓ.ም

# ተቀላቀል

# ፩

## ዳጋ÷ኢትዮጵያ

ሚራኘ በጠራው ጨረቃ ስር ለጥ ያለውን ሓይቅ ፊቱ በመመልከት ላይ ነው። መንፈቀ ሌሊት። በስተደቡብ ምሥራቅ ባለው የሰማዩ ንፍቀ ክበብ የሚጎተት የደመና ባዘቶ ጨረቃዋን ስመዋጥ ይጣደፋል። ፀጥ ረጭ ያለው የዳጋ ደሴት አረንጓዴ ደበሎውን ተከናንቦ ጣና ሓይቅ ላይ ተኝቷል። ጣናም ራሱ፣ ሌሊት እንደሰው ለሽ ብሎ ይተኛና ጎሕ ሲቀድ ሲል ማንኮራፋት ይጀምራል። አንዳች የነፋስ ሽውታ ገሽሮ ማዕበሉን አስነስቶ ዛሩን እስኪያወርደው ድረስ እንዲህ ነው። ጣና፣ አንድ ነገር ገብቶት በሆዱ እያላወሰ የተኛ ሰው እንጂ ሚራኘ በልጅነቱ የተንቦራጨቀበት ውሃ አልመስልህ አለው።

የሚራኘን ጥቁር ካፖርት ከወደ ሰሜን ምስራቅ የመጣ መጠነኛ ነፋስ ሲያወናጭፈው፣ ጨረቃው ውሃው ላይ የጣለውን ጥቁር ጥላውን አይቶ ወደ ኋላው ሸሸ። ውሃውን በጥላው እንቅስቃሴ ይቀሰቅሰው ይመስል። ውሃው ላይ

ወድቆ የቀረው የደፋው ጥቁር ባርኔጣ ጥላ ብቻ ነበር:: በቀኝ እጁ ባርኔጣውን አነሳና የራሱን ጥላ ተመለከተ:: ውሃው መስታውት ቢሆን ኖሮ በጥቁር ፀጉሩ ውስጥ እንደ ጭድ ተሰግስጎ የወረረውን ሽበት በተመለከተ ነበር:: ሆኖም ይህን መገመት አላዳገተውም::

'አንድ ለውጥ ሳይታይ በከንቱ እድሜህ አለቀ::' ሲል የራሱ ሀሳብ በነገር ጠቅ አደረገው:: ከልጅነቱ ጀምሮ በመዋተት ያሳለፈው ጊዜ ሁሉ ተራ በተራ ተደቀነበት:: ከዚህ የሀሳብ ፍላፃ ያድነው ይመስል ያወለቀውን ባርኔጣ መልሶ ራሱ ላይ ደፋውና ዓይኖቹን አሻግሮ ወደ ሐይቁ አድማስ ወረወራቸው:: የሚጠባበቃት ጀልባ እስክትደርስ በመቸኮሉ የተነሳ፣ እንደ ልጅ ከውሃው ጋር በመጫዎቱ ራሱን ሳይታዘበው አልቀረም::

ጀልባዋ በታሰበው ጊዜ አልደረሰችም:: ምናልባት አንድ አደጋ ተፈጥሮ ይሆናል የሚል ሥጋት አደረበት:: በጥብቅ ምስጢር ለተልእኮ ከሳምንት በፊት የተሰማራችው ዴር33 በውስጧ ከያዘቻቸው አባላት ጋርም ሆነ ወደ ተገጠመላት መስመር የስልክ ግንኙነት እንዳያደርግ፣ በተሰጠ ጥብቅ ውሳኔ መሠረት ስልክ መደወል አይችልም እንጂ፣ ማራኘ ስልኩን አስሬ ከኪሱ ሲያወጣ ነበር:: ሌሊቱ ከመገባደዱ በፊት ዳጋ መድረስ ያለባትን ጀልባ በመጠባበቅ ላይ እያለ ጥቁሩ የደመና

ክምር ጨረቃዋን ጎፋፈናት፡፡ ነፋሱም ጨረቃዋን ያስጥል ይመስል ከደመናው ጋር ይፋለም ይዟል፡፡ ጣናም መንቦጫቦጩን ጀምሯል፡፡ ከዚህ የነፋስና የደመና ንትርክ በኋላ የካፊያ ነጠብጣብ ሓይቁን እንደሚፈላ ሽሮ ጡቅ ጡቅ ያደርገው ገባ፡፡

ሚራዥ ከጥጉ ካለው የዶቅማ ዛፍ ሥር ለመጠለል ቢሞክርም ዝናቡ እየበረታ ሲመጣ ሊያድነው አልቻለም፡፡ በዚሁ ቅፅበት በሓይቁ ላይ የሚንሳፈፍ ጭል ጭል የሚል ብርሃን የተመለከተ መሰለው፡፡ እየቆየም እየቀረበ መጣ፡፡ የዶሮ33 የፊት መብራት መሆኑን አልተጠራጠረም፡፡ ወደ ደማቅ ሰማያዊ የሚያደላው መብራት ለዚህ ማረጋገጫው ነው፡፡ የጀልባዋ መዘግየት ይጠባበቀው የነበረውን መርዶም ይሁን ብስራት ይበልጥ አናረበት፡፡ ከሓይቁ ዳርቻ መልህቋን እስክትጥል ድረስ ያለው ጊዜ ያመት ያህል የረዘመበት መሰለው፡፡

ዶሮ33 ከዳጋ ደሴት በስተደቡብ በሚገኘው ድብቅ የዶሮቶጋዳ ወደቧ መልህቋን ጥላ ቆመች፡፡ በዚሁ ቅፅበት ሚራዥ የባትሪ ብርሃን ምልክት ሶስት ጊዜ ቦግ እልም በማድረግ ሰጠ፡፡ ከዶሮ33 የወረዱት አባላት ሚራዥ ምልክት ወደ ሰጠበት አቅጣጫ በፍጥነት እየተራመዱ መጡ፡፡

ሚራኘ በጨለማው ውስጥ ወደርሱ የሚገሰግሱትን አባላት አለመጉደላቸውን በመቁጠር አረጋገጠ፡፡ ኪራኮስ፣ ማርዬ ዋቆ ማርዬ፣ ሳዶፍ፣ ሜሮዳ እና ጌራ ሁሉም በህይወት ተመልሰዋል፡፡ በአስፈሪ ፀጥታ ወደ ሚራኘ ቀረቡ፡፡ በብርዱ የተነሳ ይሁን አልያ በነሱ ፀጥታ ምክንያት የሚራኘ ከንፈር ተንቀጠቀጠ፡፡ የእጅ ባትሪውን አብርቶ ፊታቸውን ለመመልከት ሞከረ፡፡ ከሁሉም… የጌራ ፊት ያስፈራል፡፡ ጭጋግ ወርቷል፡፡ በሌሊቱ ቅዝቃዜ የተነሳ፣ ከአፉ የሚወጣው እስትንፋስ ሲጋራ የሚያጨስ ይመስል እንደጉም ይትጎለጎላል፡፡

"ሁሉም ነገር እያበቃለት ነው" አለ ጌራ ለሚራኘ ሰላምታ ሳያስቀድም፡፡ "ጋሙሶች ሁሉንም ነገር ደርሰውበታል፡፡ ታዴምስ ኢያሱ ጉድ ሰርቶናል፤ ሁሉንም ነገር አብጠርጥሮ አስረድቷቸዋል፡፡"

ሚራኘ አንገቱን ደፋና ስለ ታዴምስ ኢያሱ ለማስታወስ ሞከረ፡፡ ታዴምስ ኢያሱ፤ በገኘው አካል አዲስ አበባ ውስጥ የተቋቋመውን ጋሙስ የተሰኘ ቡድን እንዲመራ የተሰየመ መሆኑ በቅርቡ የተደረሰበት ጉዳይ ነው፡፡ ከአመታት በፊት ጎንደር ከተማ ውስጥ መሸጎ የነበረውን የዴርቶጋዳ አባል ለመያዝ ሚናፍ ደርሶ የነበረ ቢሆንም በደህንነት መስረያ ቤቱ

ውስጥ ሰርጎ እንዲገባ በተደረገው ዳግማዊ በተባለ አባል ተማርኮ ተራራው ውስጥ ታስሮ እንደነበር ይታወሳል። በተራራው ውስጥ በታሰረበት ወቅት የፍርድ ውሳኔ ሊሰጥበት ካላስቻሉት ምክንያቶች ውስጥ አያና እና አክሎግ የተባሉት የዴርቶጋዳ ሰርጎ ገብ አባላት ይጠቀሳሉ። በመጨረሻም ተራራው በተከበበበት ወቅት ጦርነቱ ሲጀመር ታዴዎስ ኢያሱን አስመልጠውታል። እሱን ወደ አዲስ አበባ ልከው፣ አክሎግ እና አያና፣ ኢንጂነር ሻጊዝን ለሲ.አይ.ኤው ወኪል ለሮበርት ጋሎ ሸጠው እየሄዱ ባሉበት ቅፅበት በዴርቶጋዳ አባላት ተደርሶባቸው መወገዳቸው ይታወቃል።

ሚራዥ የታዴዎስ ኢያሱን ጉዳይ እያስታወሰ ቀና አለ። ቀደም ባሉት ጊዜያት የተሠሩ አንዳንድ አልባሌና ጥቃቅን ስህተቶች ምን ያህል ድርጅቱን ዋጋ እያስከፈሉት እንደሆነ አላጣውም።

"እሺ. ቀጥል" አለ ሚራዥ ወደ ጌራ እየተመለከተ። ጌራ የሚራዥን ትኩረት እስኪያገኝ እየተጠባበቀው ነበር።

"ተራራውን እንደገና ሰብረው ለመግባት በጥናት ላይ ከመሆናቸውም በተጨማሪ፣ ይህንን ተግባር ለመፈፀም በታዴዎስ ኢያሱ መሪነት ተራራውን ሰንጥቀው ለመግባት ልዩ ስልጠና የተሰጣቸው ልዩ ኮማንዶዎች ትዕዛዝ በመጠበቅ

ላይ መሆናቸውን ደርሰንበታል። በታደምስ ኢያሱ ጠቋሚነት፣ በደህንነት መስሪያ ቤቱ ውስጥ ሰርገው ገብተው የነበሩት የዴርቶጋዳ አባላት በድብቅ እንዲዎገዱ ተደርገዋል። በዚህ ሰዓት ከአንድ አባል በስተቀር በደህንነት መስሪያ ቤቱ ውስጥ የሰረገ አባል የለንም። በጋሙስ ውስጥ የሚገኘው አባላችንም ምናልባት በቅርቡ ሊጠረጠር ይችል ይሆናል። በጥቅሉ ዴርቶጋዳ እያበቃለት ነው። ካላቸው ዝግጅት እንደተረዳነው ለቀነው የመጣነውን ተራራ ሰብረው ለመግባት የሚያዳግታቸው አንዳች ነገር አይኖርም።"

ተራራውን ሰብረው መግባታቸው ብቻ ችግር ላያመጣ ይችላል። ምክንያቱም እኛ በዛ የለንም። ችግሩ ከተራራው ከርሰ ምድር የሚነሳውን የምድር ውስጥ መንገድ ያገኙት እንደሆነ ነው። ካገኙት ውስጥ ለውስጥ ተጉዘው እንደኛ በዳጋ መዝለቃቸው የማይቀር ነው።" ማርዬ ዋቆ ስጋቱን ለሚራዥ በተሻለ መንገድ ለመግለፅ ይበልጥ ተጠግቶ ተናገረና መልሶ ዝም አለ።

"በሌላ በኩል..." አለ ኪራኮስ ከሁለቱም ለስለስ ባለና ዝግ ባለ ድምፅ። ይህን ቀዝቀዝ ማለቱን ከአባቱ የወረሰው ነው ይላሉ- የዴርቶጋዳ አባላት። አባቱ ድርጅቱን አሳልፈው ለጋሙስ ቢሸጡም በአባቱ ምክንያት ቂም አልተቋጠረበትም።

ከዛ ይልቅ በአባቱ ማስታወሻ ውስጥ የተገኙ ምስጠራትን ለድርጅቱ በመስጠቱ ከፍ ያለ ቦታ ተችሮታል። ድርጅቱን ከውድመት የታደገ ጀግና ተብሎም ተወድሷል። ከጣቅርን ተራራ ከርስ ምድር እስከ ዳጋ ደሴት የተዘረጋው የምድር ውስጥ መንገድ፣ ኪራኮስ የአባቱን ማስታወሻ ይዞ ባይደርስ ኖሮ ማንም ሊያገኘው እንደማይችል እያንዳንዱ የዴርቶጋዳ አባል ተገንዝቦታል። ሚራዥር ኪራኮስ ለመናገር በቃጣበት ቅፅበት ትዝ ያለው የታደጋቸው የአባቱ ማስታወሻ ነበር-የባኮስ ማስታወሻ። ከተራራው ካመለጡ በኋላ ኪራኮስ በስጦታ መልክ እንዳበረከተለት አስታወሰ። ሆኖም ያንን ማስታወሻ እንደገና ገልጦ አለማየቱ ራሱን እንዲታዘብ አደረገው።

"በሌላ በኩል..." ሲል ኪራኮስ እንደገና ንግግሩን ቀጠለ። "...የቀድሞው ሚኒስትር ከዲምላ ሞት በኋላ ውስ ጠፍቶበት የነበረውን ምስጢር እንደገና ማነፍነፍ ጀምሯል። የጋሙስ ዋና ሰው የሆነው ይህ ሚኒስትር፣ የሰጠመውን መርከብ አውጥቶ፣ በውስጡ በበርሜል እየተሞላ የተቀመጠውን ወርቅ ለማፈስ፣ ሞርሞሪዲኖ ከተባለው የጣሊያን ማፍያ ጋር በዳጋ አቅራቢያ በምትገኝ ትንሽ ደሴት ላይ ከትሞ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። ሆኖም ዲምላ የሚባል የዶን ሞርሞርዲኖ ተላላኪ ሞርሞርዲኖንና ጋሻጋጃግሬዎቹን ሲጨርስ ይህ ሚኒስትር አምልጧል። በኋላም እስከ ባህር ዳር ዲምላን ይከታተል እንደነበር

ይታወቃል፡፡ ዲምላ የሰጠመውን መርከብ ቁልፍ ፍንጭ አግኝቶ ወደ ጢስ አባይ ሲከንፍ ይህ ሚኒስትር የዲምላ ዱካ ስለጠፋበት ፍሊጋውን አቁሞ ነበር፡፡ አሁን ግን ለዘመናት ተቀብሮ የነበረው ምስጢር ወጥቷል፡፡ የሰጠመው መርከብ ቁልፍ የሆነው ካርታም የት እንዳለ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ይህን መርከብ ከተቀበረበት ግራጋዴዎስ ለማውጣት የቀድሞው ሚኒስትር እና ታዴዎስ እቅድ ነድፈዋል፡፡ በዚህ እቅድ መሠረት፣ ሚራዥር ተይዞ የካርታውን ቁልፍ እንዲተፋ ይደረጋል፡፡" ብሎ ኪራኮስ ሚራዥርን በጥሞና ተመለከተው፡፡

ሚራዥር ዓይኖቹን ኪራኮስ ላይ እንደተከለ አእምሮው በትዝታ የኋሊት ተወነጨፈ፡፡ ከሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን ገብረ መድህን ግጥም እስከ ዲምላ ግብግብ... ከሰቆቃዎ ጴጥሮስ ስንኞች እስከ የሎስ ምሰሶ ህቡዕ ምስጢር... ሁሉም ነገር ተራ በተራ ተደቀነበት፡፡

*"በወንዝ አፋፍ የትብት ሐረግ ቀንጃ አጣማጅ የደመና ዳስ ጢሎሽ መንጠልጠል አልፌ የሎስ ምሰሶ መቀነቻ ጥግ ለሀንዛሽ ዲብ ታድሞ የእናቴን የኢትዮጵያን ብር ööö አላጣም* የሚለውና ከብዙ የስንኝ አባሮሽ ፍልሚያ በኋላ የተገኘው ምስጢር ታወሰው፡፡ አባይ... ሰባሪ ድልድይ...የሎስ ምሰሶ... ööö የሚልና የ"ቶ" ቅርፅ የተቀረፀበት ድንጋይ... ዲምላ...ግብግብ... የሚጥመለመል ወንዝ... የሾሉ አለቶች

ባለጉጥ መስቀል… ቀይዋ ሳጥን… በቀይዋ ሳጥን ውስጥ ተጣጥፎ የተቀመጠ ፬፬፬ የብራና ገፅ… የሰጠመው መርከብ ካርታ… ይህ ሁሉ አንድ በአንድ ተሰትሮ ወደ ሚራኝ አእምሮ መጣ። ይህ ብቻ አይደለም፤ ከዳጋ ደሴት አቅራቢያ ሐይቁ ውስጥ አስጥመው አስቀምጠውት የነበረው ኤክስካቫተር ዶዘርም ትዝ አለው።

"በሌላ በኩል…" አለች ሜሮዳ ሚራኝን ከትዝታው አናጥባ። "በሌላ በኩል ኢንጂነር ሻጊዝንና ጥቁሩን ሳጥን ለመያዝ ከሮበርት ጋሉ ሞት በኋላ ሌላ ልዑክ አዲስ አበባ እንደሚገባ ታውቋል። የቀድሞው ሚኒስትር ከዚህ ልዑክ ጋር ለመነጋገር ቀጠሮ ይዘዋል። ስለዚህ…"

"ስለዚህማ… የምናባክነው ጊዜ ሳይኖር ወደ ትክክለኛ ውሳኔ መድረስ አለብን።" ሳዶና በደሴቱ ከርስ ምድር ውስጥ ወደ ሚያስገባው መንገድ አመራ። ሌሎቹም ተከታተሉት። ሚራኝ ግን ባለበት ደንግዞ እንደቆመ ቀረ። የደረሰትን መርዶዎች በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ አእምሮው ውዥንብር ውስጥ ገብቶ እንደ ቂቤ ይናጥ ጀመር።

# ፪

## አዲስ አበባ÷ ኢትዮጵያ

በባኮስ ማስታወሻ ላይ ሰፍሮ ከተገኘ ወዲህ፣ ጋሙስ የሚባለው ምስጢራዊ ቡድን ምስጢሩ ገሀድ መውጣት ጀምሯል። የኪራኮስ አባት ባኮስ፣ የዚህን ምስጢራዊ ቡድን ጉድ ከስሙ ትርጓሜ ጀምረው መተንተናቸው ይታወቃል። በማስታወሻቸው ላይ ሰፍሮ እንደደተገኘው ጋሙስ ማለት በጥቅሉ ጎሽ ማለት ነው። ጎሽ፣ ቀንደ ሹል፣ ቀንደ ገላላ የሆነ የበረሃ እንስሳ ነው። ባኮስ እንደሚሉት "መልኩ የበሬ ጠባዩ ያውሬ" የሆነ እንስሳ።

በዚህ ጠላቱን ለመበቀል አንቱ በተሰኘ እንስሳ ስም በ1989 በገገርው ፓርቲ ጉምቱ ሰዎች የታቋቋመው ድርጅት ዋና አላማ "ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች" እንዲሉ ለቆመለት አላማ እስከመጨረሻው የደም እንጥፍጣፊ መስገስ ነው። በቁጥር ዘጠኝ በሆኑ ሰዎች የተቋመው ይህ ድርጅት ገገርው ፓርቲ

በአንዳች አጋጣሚ ከተፈናጠጠበት የስልጣን ኮርቻው ላይ ቢንሸራተት፣ በጋሙስ ጥላ ሥር የተጠለሉት ሰዎች ያለ አንዳች እንቅፋት እንዲሸሹ የማድረግ፣ ያፈሩትን ንብረት በልዩ ልዩ መንገዶች ማሸሽ፣ ይህ አደጋ እስኪፈጠርም የአባላቱን ንብረት መጠበቅና ማስፋፋት፣ በተለያዩ ተጫራች ኩባንያዎች ስም ፕሮጀክቶችን ማካሄድ ነው። ከደህንነት መስሪያ ቤቱ ተሰውሮና ተነጥሎ በምስጢር የተቋቋመው ይህ ድርጅት አንዳንድ የሀሰት መረጃዎችን በማርቀቅ የገዥውን ፓርቲ ስልጣን የሚነቀንቁ እጆች እንዲሰበሰቡ ያደርጋል። በህቡዕ የሚደረጉ ሴራዎችን ያከሽፋል፤ ያጠፋል። ለአመፅ ይነሳሳሉ ብሎ የሚገምታቸውን የጦር ክፍሎችና አንዳንድ ለሆዱ አላድርም ብለው እጃቸውን እንደ ጲላጦስ የሚታጠቡ ባስልጣናትን በአይነ ቁራኛ ይቆጣጠራል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ዞር ያደርጋል። በደህንነት መስሪያ ቤቱ እጅ የገቡ አንዳንድ መረጃዎችን ያጨናግፋል፤ የፀረ ስለላ መረቦችንም ይዘረጋል። በሌሎች ስውር እጆች የሚንቀሳቀሱ የባለስልጣናቱን ንግዶች በበላይነት በመቆጣጠር ምስጢራዊነታቸው እንዲጠበቅ ያደርጋል።

በባኮስ ማስታወሻ ላይ ሰፍሮ እንደተገኘው ጋሙስ አላማው ይህ ብቻ አይደለም። ለሥርዓቱ አስጊ ይሆናሉ ብሎ ያሰባቸውን ኃይሎች ሁሉ ለመደምሰስ እንቅልፍ የለውም።

በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎችን ከፍተኛ ወንጀል በማሠራት ሥርዓቱን ከማገልገል በቀር ሌላ አማራጭ እንዳይኖራቸው ያደረጋል። በአፈንጋጩ ባኮስ ማስታወሻ ላይ ሰፍሮ እንደተገኘው ይህ ድርጅት በቢሲዮን የሚቆጠር ሀብት አፍርቷል። በተለያዩ የአለም አካባቢዎች ታላላቅ የንግድ ድርጅቶችን ከፍቷል። የዚህ ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ሆኖ በአማካሪ ድርጅት ሽፋን ሥራውን በትጋት ያከናውል።

ስለዚህ ድርጅት መኖር፣ ምስጢሩ አፈትልኮ በጴርቶጋዳ ከፍተኛ አባላት እጅ እስኪገባ ድረስ ማንም አያውቅም ነበር። ጋሙስ እና ጴርቶጋዳ የሚያደርጉት ሥውር ጦርነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተፋፋመ ቀጥሏል። ይህ ህቡዕ የጨለማ ውስጥ ጦርነት በጋሙስ ድል አድራጊነት ይጠናቀቅ ዘንድ የአንበሳውን ድርሻ ከወሰዱ ሰዎች መካከል ታዴዎስ ኢያሱና በቅዕል ስሙ ኒቆ እየተባለ የሚጠራው የቀድሞ ሚኒስትር ነው። ኒቆ የሚለው ቅፅል ስም በማንና ለምን እንደተሰጠው ባይታወቅም አንዳንድ መላምቶች ግን ተመተዋል። ከመላምቶቹ ውስጥ ሚዛን የደፋው፣ "ኒቆ" "ኒቆዲሞስ" ከሚለው ስም የተቀነጨበ ምህፃረ ስም ነው የሚለው ነው። "ቀን ቀን ከጲላጦስ፣ ማታ ማታ ከኢየሱስ" ተብሎም ተተንትኗል። ከምሽቱ አራት ሰአት ተኩል ላይ፣ በቀጠሮው

መሀረት፣ ታዴዎስ ኢያሱ ወደ ኒቆ ቢሮ ገብቷል። በአክሉግና አያና ተራዳኢነት ከተራራው አምልጦ እናት ድርጅቱን ከተቀላቀለ ጊዜ ጀምሮ የኒቆ ልዩ እንክብካቤ አልተለየውም። ጋሙስ አክሉግና አያና ቢገደሉበትም በታዴዎስ ማምለጥ ሳይፅናና አልቀረም። እንዲያውም የአክሉግና የአያና አገልግሎት ያበቃ መሰሎ ነበር። ሁለቱ ሰርጎ ገቦች ዴርቶጋዳ የመሸገበትን ተራራ እና ውስጡ ያለውን ምስጢር ሁሉ ካቀበሉ በኋላ የቀራቸው ጉዳይ እንደሌለ ለኒቆ ግልፅ ከሆነለት ቆይቷል። ከዚህ ከኋላ የቀረው ጉዳይ ተራራውን በልዩ ኃይሎች ባልተጠበቀ ሰዓት ሰብሮ ገብቶ ዴርቶጋዳን እስከወዲያኛው ማውደም ብቻ እንደሆነ ኒቆ ከደመደመ ቆይቷል። ሆኖም ይህን ኦፕሬሽን ለማካሄድ ካለፈው ስህተት የተገኙ ልምዶችንና እውቀቶችን መገምገም እንዳለበት ተረድቶታል። ከዚህም በተጨማሪ ድምሰሳው በሚካሄድበት ወቅት፣ በሚራኙር እጅ የሚገኘው የሰጠመው መርከብ ቁልፍ የሆነው ካርታ፣ ያለ አንዳች ብልሽት በእጁ መግባት እንዳለበት ያምናል።

ኒቆ ከአመታት በፊት አምልጦት የነበረው ምስጢር ውሉ ሰተት ብሎ ቢሮው ድረስ በመግባቱ ውስጡ በሐሴት እየተሞላ ደስታውን መደበቅ ባለመቻሉ ፈገግ አለ። ቢሮው ውስጥ ፈገግ ቢልም አእምሮው ግን ከራሱ ተነጥሎ

ወዳለፈው ጊዜ በረረ። በደቅ ደሴትና በዳጋ መካካል፣ በጉረር ወደብ አቅራቢያ ያለችውና የደሀ ሰው መዳፍ የምታክለው ትንሽ ደሴት ድቅን አለችበት። በቀጠልም የዶን ሞርሞርዲኖ ድንኳን... የሚቀዱ መጠጦች ድምፅ... ከአሥራ አምስት አመታት በላይ የቆዩና የበሰሉ ውድ የወይን መጠጦች... የዶን ሞርሞርዲኖ ቡስኪ ሳቅና በተስፋ የተሞሉ ዓይኖች... ሁሉም ነገር አንድ በአንድ እየተሰተረ የትውስታ ማህደሩን ይወጥረው ጀመር። የዶን ሞርሞርዲኖ ቡስኪ በእርግጠኝነት የተሞሉ ዓይኖች የተመለከቱት መስለው። የሞርሞርዲኖ በቀይ ወይን የተሞላ ብርጭቆ "ችርስ" ሲለው የተነሳ መሰለው። በዚህ ጊዜ በእውን እዛው ቦታ ያለ መሰለውና ባዶ እጁን ብርጭቆ እንደያዘ አድርጎ አየር ላይ አንሳፈፈው።

"ኒቆ!" የሚለው የታዱዎስ ድምፅ ከህልም አለሙ ሲያባትተው ብርጭቆውን የጣለው ያህል በድንጋጤ ክው አለ። "ምንው በሰላም ነው?!"

"አ... አይ... በሰላም ነው..." ኒቆ ዓይኖቹን ቦግ እልም በማድግ ከህልም አለሙ ለመንቃት ሞከረ። "ዶን ሞርሞርዲኖን አስታውሼ ነው።... ያ ባሪያ ነገሩን ሁሉ ባያበላሻሸው ኖሮ ለዘመናት ተቀብሮ የኖረው ሲሳይ እስከ ዛሬ በእጃችን ይገባ ነበር።"

"ልክ ነበር... ሆኖም 'ይዋል ይደር እንጂ አህያ የጅብ ናት' እንዲሉ ሲሳዩ በመጨረሻ በእጃችን ሊገባ እኛን እየጠበቀ ለመሆኑ ጥርጥር የሌለው ጉዳይ ነው።" የታዴዎስ ህሊና ወደ ጣና ሐይቁ ጠለቀ። በበርሜል ተሞልቶ የተከመረውን ወርቅ ዛቀ።

"ህ!... እውነት ነው። የኛን እንጀራ ይሸበርራል እንጂ ማንም አይበላውም። ያ ዲምላ የሚሉት ባሪያ ሁሉን ነገር ቢያሸበርረውም እንደ ሞርሞርዲኖ ቀይ ወይን የበለጠ ጣፍጦ ልናገኘው መቃረባችን እውን ሆኗል። ኒቆ የዲምላ ገፅታ ተደቀነበት ከሰል የመሰለ ፊቱ ፍም የመሰለ ከንፈሩ ያችን ትንሽ ደሴት ሲያጋያት ኒቆ የራሱ ኮት በእሳት ተያይዞ ወደ ሄሊኮፕተሩ ሲሮጥ... ልዩ ጠባቂዎቹ ሲከላከሉት... ታየው። ከዚህ ልዩ ጠባቆዎቹ ውስጥ አንዱ የነበረው ታዴዎስ ኢያሱ ከፊት ለፊቱ ተቀምጧል። ባህር ዳር ውስጥ ዲምላን ለመጨረሻ ጊዜ ያየው ይሄው ታዴዎስ ኢያሱ ነበር። "ያን እርጉም ባሪያ እስከ ዛሬ ድረስ ከአእምሮዬ አውጥቼ ልጥለው አልቻልኩም" ኒቆ ወደ ታዴዎስ ተመለከተ። "እርሳው! ከአሁን በኋላ ወደ ኋላ ማሰቡ ትርጉም የለውም። ወደ ፊት! ... ወደ ፊት ያለውን ብሩህ ጊዜ ማሰቡ ይሻላል። ጊዜም የለንም ክቡር ሚኒስትር።" ኒቆ ምንም እንኳ ሚኒስትር ሹመቱ ከተሻረ የቆዬ ቢሆንም ታዴዎስ ለምዶበትም ይሁን አልያ አክብሮቱን ለመግለፅ "ክቡር ሚኒስትር" ይለዋል አልፎ

አልፎ፡፡ ምናልባትም ከሚኒስትርነቱ ሲነፃፀር የተሻለ ቦታ ላይ እንደተቀመጠም ሳያስብ አይቀርም፡፡ "ልክ ነው ታዴ... " አለ ኒቆ ዛሬ ወደተገኙበት ፍሬ ነገር ለመግባት ማስታወሻውን እየገለጠ፡፡ ፀሀፊውና ሌሎች "የአማካሪ ድርጅቱ" ሠራተኞች እስኪ.ወጡ በይዋል ያስቀመጡትን ጉዳይ በቅደም ተከተል ይወያዩበት ገቡ፡፡

"ነገ ጠዋት ወደ ኮሎምቢያ ትበርና... ከዶን ቦናኖ ጋር ወርቁ የሚንንዝበትን መንገድ ትናጋገራለህ፡፡ ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደዚህ ትመለስና ተራረውን ሰብረው የሚገቡትን ልዩ ኮማንዶዎች ይዘህ ወደ ጣቅርን ተራራ ትሄዳለህ፡፡ ይህ ኦፕሬሽን ፈጣን፣ ፋታ የማይሰጥና ጠላትን እንዳያስብ ጊዜ የማያደላድል ሆኖ እንደተጠናቀቀ ሚራዥ እስከ ሰጠመው መርከብ ካርታ ተይዞ እንዲቀርብልኝ ይደረጋል፡፡ ሌላው መረሳት የሌለበት ጉዳይ የኢንጂነሩና የጥቁር ሳጥን ጉዳይ ነው፡፡ ሁለቱም ተይዘው እንዲሰጡኝ ታደርጋለህ፡፡ እነዚህን ነገሮች በእጃችን ካስገባን በኋላ ቀጣዩ ነገር የገለባ ያህል ቀላል ነው፡፡"

"ኒቆ... ነገሩን ይህን ያህል አቅለን ማየት ያለብን አይመስለኝም፡፡ በእነሱ በኩል ያለውን ዝግጅት እንዳለፈው ጊዜ የሚያቀብለን ያለመኖሩ ጉዳይ ሊታሰብበት ይገባል፡፡"

"ይህን ያህል የሚያሳስብ ጉዳይ አይደለም፡፡ ዋናው ትልቁ ጉዳይ ያለብትን ማወቅ ነው፡፡ ተራራውን ሰብረው

በሚገቡት ልዩ ኮማንዶዎቻችን ደግሞ መቶ በመቶ እተማመንባቸዋለሁ። ሰማይ ሰንጥቀው ካልወጡ በቀር ምድር ሰንጥቀው ካልቀለጡ በቀር የትም ሊያመልጡን አይችሉም።"

"ምድርማ ሰንጥቀው ገብተዋል!" ታዴዎስ ፈገግ አለ።

"ተወው... መቃብራቸውን ከመቆፈር ነው የገላገሉን።" ሁለቱም እርስ በእርስ ለረጅም ደቂቃዎች ዓይኖቻቸውን ተተካክለው ተያዩ።

# ፫

## ዳጋ÷ኢትዮጵያ

የዳጋ ከርሰ ምድር ውጥረት ነግሶበታል፡፡ ተራራውን ሰብሮ እንደገና ለመግባት ከተራራው የሚነሳውን የምድር ውስጥ መንገድ በመከተል ጠላቶቻቸው ዳጋ ደሴት ከርሰ ምድር ድረስ ላለመዝለቃቸው ማንም እርግጠኛ ባለመሆኑ ቀፎው እንደተነካ ንብ ሁሉም መተረማመሱ እንደቀጠለ ነው፡፡

በዚህ ትርምስ መሀል የሚቀርብ ሀሳብ ሁሉ ነፋስ እንደነካው ደመና ከመበተን በቀር ከማንም ሊደርስ አልቻለም፡፡ በዚህ ሁሉ ትርምስ ውስጥ አንዳችም ሀሳብ ያልሰነዘረው ሚራዥ ብቻ ነበር፡፡ አእምሮው ውስጥ የሚተራመሰውን ሀሳብ ቅጥ ያስይዝለት ይመስል የምድር ውስጥ ዋሻውን እየተዘዋወረ ይመለከት ጀመር፡፡ የዳጋው የምድር ውስጥ ከተማ እንዳልነበር ሆኗል፡፡ ሚራዥ ከኒዮርክ በመጣበት ጊዜ አይቶ የተደመመበት ያ ሁሉ ቴክኖሎጂ አሁን የለም፡፡ ለምልክት

ያህል የቀረው አመድና ከሰል ብቻ ነው፡፡ የዋሻው ውስጥ ግድግዳ ከመሰነጣጠቁም በላይ በቃጠሎው ወቅት የገረፈው የእሳት ላንቃ እና ጥቁር ጢስ ጽልማሞት አልብሰውታል፡፡

ሚራኘ ወደ ውስጥ እየዘለቀ ሲሄድ የከሰሉ የሰው አጥንቶች፣ የመጻህፍት ገፆች፣ በርሜሎችና ሌሎች ቁሳቁሶች እንዳልነበር ሆነው ተመለከተ፡፡ ከዚህ በላይ ማየት ባለመፈለጉ ቀደም ሲል ገዳሙ ውስጥ በቀሩ ሽማግሌዎች እንደገና እድሳት ወደተደረገለትና አሁን አባሳት በሙሉ ተሰብስበው ወደ ሚነታረኩበት ክፍል ተመለሰ፡፡ ይህም ክፍል ቢሆን የሽማግሌዎቹን ጥረትና እንደገና መነሳሳት ለማድነቅ ካልሆነ በቀር የጥንት መልኩ አልመጣም፡፡ በቃጠሎው ወቅት የለበሰው ጥቀርሻ እንኳ ሙሉ በሙሉ አልተጠረገም፡፡ በየጥጋ ጥጉ የፋኖስ መብራቶች ባይሰቀሉ ኖሮ በዋሻ ውስጥ ይኖር የነበረውን የጥንቱን ሰው የዋሻ ውስጥ ህይዎት ያስታውስ እንደሆነ እንጂ ሀገር ለመለወጥ ቴክኖሎጂን ታጥቀው የሚተረማመሱ ሳይንቲስቶች የኖሩበት አይመስልም፡፡

ሚራኘ በፋኖሶቹ ብርሃን ላይ ዓይኖቹን ተክሎ እያሰላሰለ እያለ፣ ኢንጂነር ሻጊዝ ከኋላው መጥቶ ትከሻውን ቸብ ቸብ አደረገው፡፡ ዞር ብሎ ምንም ሳይናገር ተመለከተው፡፡ እያረጀ መሆኑን ፀጉሩ ማሳበቅ ጀምሯል፡፡ የራስ ፀጉሩ ገብስማ

መስሏል። ነጭና ጥቁር እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ይፋለሙበታል። ምንም እንኳ ሎስ አላሞስ ውስጥ የተቀየረለት የዣክ ዶናልድ ሲሞን ፊት ቢሆንም ይኸው የተውሶ ፊቱም አልፎ አልፎ መስመር አርፎበታል የእድሜ ድር እያደራበት። ሆኖም በፋኑሱ ብርሃን የሚታዩት ዓይኖቹ የጥንካሬንና የተስፋን ጨረር እስከ አሁን ይረጫሉ።

"ወንድም ሚራዥር..." በግድ ፈገግ ለማለት ሞከረ። ሁልጊዜም እንደዚህ ነው- ሻጊዝ (ያሁኑ ዣክ ዶናልድ ሲሞን)። የትኛውንም ንግግር ከመጀመሩ በፊት ፈገግ ማለት ልማዱ ነው። በዚህ አስጨናቂ ጊዜ ፈገግ ለማለት በመቻሉ ሚራዥርን ሳይገርመው አልቀረም።

"...ሚራዥር... ምንድን ነው እንደዚህ ሳታስበው እንደፀነሰች ልጃገረድ መጨነቅ?... በጭንቀት የሚሆን ነገር አለ እንዴ?... በጭንቀት ጊዜ ከማባከን ያልሆነ ውሳኔ ወስኖ መፀፀት ይሻላል።"

"ያልሆነ ውሳኔ ራሱ እኮ የለም" አለ ሚራዥር የሚናገረው ያጣ ይመስል።

"እህ!...ውሳኔ የሌለው ነገርማ የለም። ምርጫ የሌለው ጉዳይማ የለም። ከእሳትና ከውሃ እንኳ አንዱን መምረጥ ይቻላል።" ሻጊዝ ፋኖሱን በአመልካች ጣቱ እየጠቆመ። "ይህንን የፋኖስ ብርሃን እየተመለከትክ ሳይህ ድቅድቅ የመሰለውን ጨለማ ሰንጥቃ የምትመጣ አንዳች የተስፋ

ብልጭታ የመጣችልህ መስሎኝ ነበር፡፡ ይህቺ የፋኖስ ብርሃን የምታመለክተው ይህንኑ ነው፡፡ እንከዛሬ ከተወጣነው ፈተና የበለጠ አልገጠመንም፡፡ "እስከዛሬ እኮ ቢያንስ መቀመጫ ቦታ እንኳ ነበረን፡፡ አሁን ግን እንደምታዬው ነው፡፡ ለጊዜው እዚህ ዋሻ ውስጥ ተጠልልን እንጂ የመጣንበትን ዱካ እየረገጠ ጠረናችንን እያነፈነፈ የሚገሰግሰው ጠላታችን መዳፍ ውስጥ አስገብቶ ሲጨምቀን እየተጣደፈ ነው፡፡"

"ሚራኘ… ይህንንማ ማንኛችንም እናውቃለን፡፡" ኪራኮስ መጥቶ ውርክባቸውን ሲያዳምጥ ከቆዬ በኋላ ሀሳቡን ሰነዘረ፡፡ "አዎ ጠላቶቻችን ወደኛ እየገሰገሱ ናቸው፡፡ ጥያቄው እኛም ወደ ነሱ እንገስግስባቸው ወይስ እንሸሻቸው ነው፡፡"

"ለመሸሽ ለመሸሽማ፣ ቆሞ ማቅማማትን ምን አመጣው? እንሸሽ ብንልስ ይህን ሁሉ ህዝብ ይዘን በምን እንሸሻለን? ህፃናቱንና ሽማግሌዎቹን ለማን ሰጥተን እንሸሻለን? ፕሮፌሰር በርናባስን ጨምሮ ከማርጀታቸው የተነሳ የረሱና የጃጁ ሽማጊሌዎችን ይዘን የት መሸሽ እንችላለን?" በዚህ መሀል በሚራኘ አእምሮ ውስጥ የሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን ስንኝ ጥልቅ አለ፡፡… 'እጠለልበት ጥግ አጣሁ' ይህን ስንኝ ሲያስታውስ የኪራኮስን አባት ማስታወሻም አብሮ ትዝ አለው፡፡ "ይልቅስ የአባትህን ማስታወሻ ብንመረምር ሳይሻል አይቀርም ምናልባት እዛ ውስጥ አንዳች ፍንጭ ልናገኝ እንችላለን፡፡"

"ሲጳራና ሜሮዳ ሲያገላብጡት ነበር ያደሩት። ያገኙበት ነገር ያለ አይመስለኝም" አለ ኪራኮስ በአባቱ ማስታወሻ ተስፋ ቆርጦ።

"ለማንኛውም ሁላችንም ብናዩው ሳይሻል አይቀርም። ለአንዱ የተደበቀበት ለሌላው ሲገለጥለት ይችላል።" ብሎ ሚራኧ ሜሮዳና ሲጳራ ወዳሉበት ክፍል ሲያመራ ሁሉም ተከታትለውት ሄዱ።

# ፩

## ቦጎታ÷ኮሎምቢያ

ታዴዎስ ኢያሱ የተሳፈረበት አውሮፕላን፣ በኢልዶራዶ አውሮፕላን ጣቢያ ለማረፍ በማንዣበብ ላይ ነው፡፡ በቦጎታ ሰማይ ላይ የሚንሳፈፈው ይህ ግዙፍ አውሮፕላን ከአዲስ አበባው ቦሌ አውሮፕላን ጣቢያ ከተነሳ ሶስት ሰአት ከአርባ አምስት ደቂቃ ሆኖታል፡፡ በሰላሳ ስምንት ሺህ ጫማ ከፍታና በዘጠኝ መቶ አርባ አምስት ሜትር በሰዓት አማካይ ፍጥነት ይውዘገዘግ የነበረው ይህ ግዙፍ አውሮፕላን፣ ያለ አንዳች ኮሽታ በኢልዶራዶ ማኮብኮቢያ ላይ በማረፍ እንዳውራ ዶሮ ይንደረደር ጀመር፡፡

ታዴዎስ ኢያሱ፣ በዚህ ኢልዶራዶ በተባለው ግዙፍ አውሮፕላን ጣቢያ ሲያርፍ ይህ የመጀሪያው አይደለም፣ እንደውሃ ቀጂ ተመላልሶበታል፡፡ ይህም ብቻ አይደለም የቦጎታን መንደሮች የእጁ መዳፍ ያህል ያውቃቸዋል፡፡

አቀማመጣቸውን ብቻ ሳይሆን ታሪካቸውን ሳይቀር አንድ በአንድ ያውቀዋል። ከሁሉም የሚመስጠው ግን ኢልዶራዶ የሚለው ስያሜ ነው። ለምን እንደሆነ ይገባዋል።

ኢልዶራዶ በጥንት የኮሎምቢያ ጎሳዎች የወርቅ ተራራ የሚል ስያሜ ያለውና በወርቅና በኢምራልድ የከበረ ተራራ እንደሆነ በአፈ ታሪክ የሚነገርለት ተራራ ነው። የእስፔን ወራሪዎች የዚህን ተራራ አፈ ታሪክ ባይሰሙ ኖሮ ኮሎምቢያን አይወሩም ነበር ተብሎም ይነገራል። ይህ የሆነው ኮሎምቢያ በአሳሹ ክርስቶፎር ኮሎምቦስ ስም ከመሰየሟ በፊት ነው።

ኮሎምቢያን ኮሎምቦስ በእግሩ ባይረግጣትም በስሙ ተጠርታለች። በእግሩ ረግጦ ያስረገጣት የክርስቶፎር ኮሎምቦስ ተከታይና አጋር የነበረው አሎንሶ አጀዳ የተባለ ቃኚ ነው። በጥንታዊያኑ ነዋሪዎቿ የኢንካ እና የአዜቴክ ቅይጥ ስልጣኔ ብቻም ሳይሆን፤ በኢምራልድና በወርቅ በደመቀው ኢልዶራዶ ተራራ ተደንቆ ኮሎምቢያን በእስፔን ወራሪዎች እንደ ዘመሚት መንጋ ከእግር እስከ ራሷ ያብሰከሰከባት አሎንሶ አጀዳ ነው።

ነገር ግን የእስፔን ወራሪዎች በወርቅ የነደደውን የኢልዶራዶን ተራራ እንደ ቋመጡለት አላገኙትም።

የጠቢቃቸው አፈ ታሪክ ነበር። እንደ አዜቴኮችና ኢንካዎች በቁጥር ብዙ ያልሆኑትና ሙስካ ተብለው የሚጠሩት ጎሳዎች አፈ ታሪክ ነበር ለካ ኢልዶራዶ። በዚሁ አፈ ታሪክ መሠረትም የኢልዶራዶ ተራራ የጠፋው፣ ጥንታውያን ነዋሪዎች፣ የእስፔን ወራሪዎች ከሚዘርፏት ብለው ተራራውን እየቆነጠሩ ወደ ተቀደሱ ውሃዎች ወርውረውት ነው።

የእስፔን ወራሪዎች የሙስካ ተረት የሆነውን ኢልዶራዶን ባያገኙትም ያገኙትን ሰቃቅመው፣ የህዝቡን ስልጣኔ አጥፍተው፣ ህዝቡን በራሳቸው ሥሪት በነገድና በጎሳ ከፋፍለው፣ የጥንቷን "ባካታ"- "ቦጎታ" ብለው ከተቱ። በዚህ ብቻም አላበቁ። ነዋሪዎችን ጎሳዎች ይበልጥ ለመቆጣጠርና የባርነት መንፈስ ለማጋባትም አያሌ ጥቁር ባሪያዎችን ከአፍሪካ አግዘው በለያቸው ላይ አሰፈሩባቸው። ከዚህም የተነሳ የቦጎታ ብቻም ሳይሆን የኮሎምቢያ ህዝብ ቅይጥ መልክ አለው። ከእስፔን ወራሪዎች፣ ከአፍሪካ ጥቁሮችና ከጥንት ጎሳዎች መልኩን የወረሰ ድፍርስርስ። ክልስልስ።

እ.ኤ.አ በ1812 ግብርና ታክሱ ናላውን እያዞረው ሲመጣ ሲሞን ቦሊቫር በተባለ ጀግና እየተመራ የኮሎምብያ ህዝብ በስመ ኮሎምቦስ የመጣበትን ወራሪ ዓይንህ ላፈር ብሎ በመፋለም፣ ከአያሌ ግብግብ በኋላ ቦጎታን ተቆጣጠረ። ህዝቡ

የድል ስሞውን ቢያነሳም ወራሪው ኃይል ኮሎምቢያን የአደንዛዥ እፅ ማሳ በማድረግ በእጅ አዙር ያደነዝዛት ጀመር። ይህ ብቻም አይደለም፣ ኮሎምቢያ የዝነኛ አለም አቀፍ ማፍያዎች መነኻሪያ ሆነች።

በተለይም በ1980ዎቹ እነ ኢስኮባር የተባሉ ማፍያዎች ሀገሪቷን በእጅ አዙር ያሾሯት ጀመር። ዘጠና በመቶ የሆነው የአለማችን የኮኬይን ምርት የሚታፈስባት ምድርም ሆነች-የእፅ ማሳዋ ኮሎምቢያ። ኢስኮባርና ጀሌዎቹ በቅንጦትና በመንፈላሰስ ከመኖራቸውም በላይ የራሳቸውን የፖለቲካ ፓርቲ በመመስረት ዓይናቸውን በጨው አጥበው የኮንግረሱን አያሌ ቦታዎች ተቆጣጠሩ። ሆኖም የኮሎምቢያ መንግሥት የአደንዛዥ እፅ ንግድን ለመቆጣጠር ዘመቻ በመክፈቱ ኢስኮባርና የመንግሥት ባለሥልጣናት ዓይንና ናጫ ሆኑ። የኢስኮባር ሰዎች የመንግሥት ባለስልጣናትን አይቀጡ ቅጣት ከመቅጣታቸው በፊት ለመደራደር ሞክረው ነበር። እንዲያውም የኮሎምቢያን ብድር በሙሉ እንክፈል ሲሉም ሀሳብ አቅርበው ነበር በመንግሥት ተቀባይነት አላገኘም እንጂ። አሻፈረኝ ያሉት የመንግሥት ባለስልጣናትም በኢስኮባር ሰዎች በየጥሻቸው የሞት ፅዋቸውን ይጎነጩ ጀመር። በኋላ ላይ ኢስኮባርን ለማለዘብ መንግሥት ድርድር በመጀመሩ ጦርነቱ ጋብ ብሎ ነበር። በዚህ ድርድር

የተዘነጋው ኢስኮባር እ.ኤ.አ በ1993 ሲገደል ነበር በኮሎምቢያ አዳዲስ ዶኖች ብቅ ያሉት፡፡ ከመሞቱ በፊት የኢስኮባር ጀሌዎች የነበሩት ማፍያዎች ለየግል ጥቅማቸው መሯሯጥ ይጀምራሉ፡፡

ከእነዚህ የቀድሞ የኢስኮባር ካፖ ዲካፒዎች መካከል የሲሲሊው ዶን ሞርሞርዲኖ ቡስኪ አንዱ ነበር፡፡ እሱም በበኩሉ የራሱን ማሳ ለማስከበር ሠራዊቱን አደራጀ፡፡ ፓፓ ቦናኖን የመሳሰሉ አደገኛ ማፍያዎች ጠንካራ ክንዶቹ ስለነበሩ ሞርሞርዲኖ በዚህ በኩል አልተቸገረም ነበር፡፡

ዶን ሞርሞርዲኖ ኢትዮጵያ ውስጥ በራሱ አሽከር በሆነውና ዲምላ በተባለ ጥቁር ጀሌው ባልተጠበቀ መልኩ ከተገደለ በኋላ ነበር- ቦናኖ የተባለው የዶን ሞርሞርዲኖ የቀድሞ ጥብቅ ወዳጅ ኮሎምቢያ ውስጥ የሚገኘውን የእፅ ማሳ ያለማንም ጣልቃ ገብነት የወረሰው፡፡

የዶን ቦናኖ ሰዎች፣ ዛሬ የሚቀበሉት አንድ ኢትዮጵያዊ ሰው የዶን ሞርሞርዲኖን አሟሟት ምስጢር ብቻም ሳይሆን፣ እንደ ኢልዶራዶ ተራራ በወርቅ የከበረውን ሓይቅ ምስጢርም ለማቀበል እንደ ቋመጠ ያውቃሉ፡፡ ይህም የሆነው አስቀድሞ ኒቆ የተባለ አለቃው ጉዳዩን ለዶን ቦናኖ በማስጨበጡ ነው፡፡

ታዴዎስ ኢያሱ፣ አንስተኛ ሻንጣውን እየጎተተ ከኢልዶሬዶ አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ ከመውጣቱ ነበር የዶን ቦናኖ ሰዎች አስቀድሞ የተነገረውን ምልክት ያሳዩት፡፡ ምልክቱ እጅግ ቀላልና ግልፅ ነበር፡፡ ገና ከኢትዮጵያ ሲነሳ እንደተነገረው አንድ ቀይ ባርኔጣ የለበሰ ሰው ጥቁር ማርቼዲስ መኪና ተደግፎ ሲያጨስ ይጠብቀው ነበር፡፡ መልእክተኛውም የአውሮፕላሱን መድረሻ ሰዓትና ጣቢያው ውስጥ የሚፈጀውን ጊዜ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ አንድ ደቂቃ ሳያዛንፍ፣ ጥቁር ማርቸዲሱን ተደገፎ፣ ቀይ ባርኔጣው አንክርፍፎ ሲጋራውን እየላፈ ጠበቀው፡፡

ታዴዎስ አላቅማማም፡፡ ቀይ ባርኔጣ ደፍቶ ወደ ቆመው ግዙፍ ሰው አመራ፡፡ ፈገግ ሲል፣ ከቀይ ድዱ ያመለጡ ጥርሶቹ ከመወየባቸው የተነሳ ሲያኝክባቸው ሳይሆን ሲያኝካቸው የኖረ አስመስለውታል፡፡

"ጎንዛሎ" ሲል እጁን ዘረጋለት፡፡ "ታዶ" በማለት "ዶ"ን በማላላት አፀፋውን መለሰ፡፡ "ታዴዎስ" የሚለው ስሙ ስለሚከብዳቸው እነ ቦናኖ ያወጡለት ስም ነው- "ታዶ"፡፡

"ወደ ቦጎታ እንኳን ደህና መጣህ"

"እንኳን ደህና ቆያችሁኝ፡፡" የሁለታቸውም እንግሊዝኛ አነጋገር፣ በቋንቋው ላይ ቂም የቋጠሩ ይመስል፣

ሲናገሩ ቃላቶቹን የሚቆረጥሟቸው እንጂ የሚጠቀሟቸው አይመስሉም፡፡

ብዙም ንግግር የለም፡፡ ታዴዎስ ኢያሱ ወደ ጥቁሩ ማርቼዲስ እንደገባ ባለቀይ ባርኔጣው ጎንዛሎ የቦጎታን ከተማ ምስራቃዊ አቅጣጫ ይዞ መክነፍ ጀመረ፡፡ ከመኪናው በኋላ መቀመጫ ለታዴዎስ ምንም ስላምታ ያልሰጡ ሁለት ሰዎች ጥቋቁር መነፅር ደንቅረው ተቀምጠዋል፡፡ ከግዝፈታቸው የተነሳ የኋላኛው መቀመጫ ከዚህ ጉዞ በኋላ ዱቄት የሚሆን ይመስላል፡፡

ጎንዛሎ፤ የስንኙ መድፊያ ሳብዕ የበዛበት የእስፔን ሙዚቃ ከጋቢናው ለቆ ሲጋራውን ይቦልቃል፡፡ ወደ ቪላ ደ ሌይቫ መንደር የሚደረገው የሶስት ሰዓታት ጉዞ "ታዶ" ን ይገፋው ዘንድም ሲጋራ ጋበዘው፡፡ ውድ ሲጋራ ቢይዝም የጎንዛሎን ግብዣ ተቀብሎ ያትጎለጉለው ጀመር፡፡

የኮሎምቢያ ጀግኖች ከእስፔን ወራሪዎች ነፃነታቸውን ለማስመለስ የተዋደቁበትን የቦያካ ድልድይ አቋርጠው ወደ ታሪካዊቷ የቅኝ ግዛት መንደር ቪላ ደ ሌይቫ አደባባይ እስኪደርሱ ድረስ ጎንዛሎ እና ታዶ ያጤሱት ሲጋራ የመኪናዋን ጠረን ውጧት ነበር፡፡

ከመንደሩ መሀል ያለውን አደባባይ ዞረው ወደ ደቡባዊ ምስራቅ አቅጣጫ የሚወስደውን ቀጭን መንገድ ከያዙ በኋላ፣ ጥንታዊ የድንጋይ ንጣፍ እንደ ሥጋጃ ከተነጠፈላት የቪላ ደ ሌይቫን መንደር ወጣ ብሎ ወደ ሚገኘው የዶን ቦናኖ ግቢ አመሩ::

# ፳

## ዳጋ÷ኢትዮጵያ

ሁሉም ተንጋግተው ሲጳራና ሜሮዳ የኪራኮስን አባት ማስታወሻ ወደ ሚያነቡበት ክፍል ሲገቡ፣ ሲጳራና ሜሮዳ ማስታወሻውን ዘግተው ተፋጠው ነበር።

"ምንም ፍንጭ አላገኛችሁም?" ሚራኘር ዘግተው ያስቀመጡትን ማስታወሻ እያነሳ ጠየቃቸው።

"ከፍንዳታው የተረፉ ስንት ሰዎች ነበሩ?" ሲጳራ ሚራኘርን እየተመለከተች ጠየቀችው። ቁሳሏ ጠግጓል። ተጠቅሎበት የነበረው ፋሻም ተፈቷል። ህፃኑን ገሮንጊዳ ታቅፎ ዓይን ዓይኑን ይመለከተዋል።

"እኔ እንደማውቀው እኔ፣ አንቺ፣ ሜሮዳ፣ ገሮንጊዳ፣ ጌራ፣..." ጣቱን ከንፈሩ ላይ ጣል አድርጎ በዚሁ በዳጋ ከርሰ ምድር ውስጥ በተፈጠረው ፍንዳታ ወቅት የተረፈ ሌላ ሰው ይኖር እንደሆን አስታወሰ። አባቱ አባ ገሮንበሩ የእሳቱ ላንቃ እንደዋጣቸው ያሳታውሳል።

"ሌላ የተረፈ.... ዲምላ ነበር እሱም ሰባራ ድልድይ ሞቷል። ሌላ... ማን ሊኖር ይችላል።"

"በባኮስ ማስታወሻ ውስጥ እንደሰፈረው ከሆነ ጥቂት አባላት፣ ከፍንዳታው ተርፈዋል። እነሱም የምድር ውስጡ ከተማ በእሳት ሲጋይ ወደ ውስጥ ሳይገቡ በደሴቱ ላይ የተለያዩ ተግባራትን ሲያካሂዱ የነበሩት ናቸው። ለምሳሌ እኛ ከጣቅርን ተራራ ስንመጣ ይህን ዋሻ በተወሰነ መልኩ ሲጠግኑ ያገኘናቸው መነኮሳት ከተረፉት ውስጥ ናቸው።

ሚራኝ አላስጨረሳትም፣ ወደ ውጭ ወጣና የተቀበሏቸውን መነኮሳት ሰብስቦ በሌላኛው ክፍል ውስጥ ይጠይቅ ጀመር።

"ለመሆኑ ስንቶቻችሁ ናችሁ በፍንዳታው ወቅት የነበራችሁ?"

"ይቅርታ ልጄ..." አሉ አንድ አዛውንት መነኩሴ እጃቸውን አውጥተው። በእድሜ መግፋት የተነሳ ድምፃቸው እንዳልተወጠረ የበገና ክር ሲር ሲር ይላል።

"ስድስት ያህል ነበርን። ስድስታችንም ይህ የምድር ውስጥ ከተማ ከመቃጠሉ በፊት በአባትህ በአባ ገ'ንበሩ ትዕዛዝ መሠረት ወደ ደቅ ደሴት ተልከን በሥራ ላይ ነበርን። ስንመለስ የጠበቀን እንደ ገሀነም በእሳት የጋመ ዋሻ ነበር።" ድምፃቸው ይባሱን ተናነቃቸው። የጭጨጭጨ ዓይኖቻቸው በዕንባ ተሸፈኑ።

"ምናለ... አብረን በነደድን ኖሮ!... እኔ ልክስልላቸው!... እ... እ. እኔ ልለብለብላቸው... እ..."

ሌሎችም እንባ እንደ ጠበል የታደሉ ይመስል አንገታቸውን ደፍተው ያለቅሱ ጀመር።

"ለመሆኑ..." ሚራዥ የተፈጠረውን ነገር ስሜቱን ቢነካውም ለቅሶውን ለማረጋጋት ሲል ሌላ ጥያቄ ሊያስከትል ታገለ። "ለመሆኑ አሁን ስንቶቻችሁ ናችሁ በህይዎት ያላችሁት?"

"በህይዎት አልክ ልጄ በህይዎት?!" አሉ ሌላኛው እድሜ እንደ ቋጥኝ የተጫናቸው መነኩሴ። "ያለ ተስፋና ያለ ህልም- የሚንቀሳቀስ በድን እንጂ ህይዎት አለውን?... የለንም እንጂ. የለንም።"

"ማለቱ..."

"እስን ከተባልን በዛ ወቅት ካልተቃጠልነው ከስድስታችን ውስጥ አራት ቀርተናል። ሁለቱ አባቶች ዘግተዋል።"

"ዘግተዋል?!"

"አዎ ልጄ... ከእኛ የተሻሉት እነርሱ ነበሩ። ከቃጠሎው በኋላ ከሰው ጋር መነጋገር አቆሙ። ስሜታቸው በጠና ተነካ። አንደኛው አባ ኤስድሮስ እድሜአቸውም በገዳሙ ውስጥም ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ ነበሩና ዘጉ። አንዳኛው አባ አልፋ ግን እድሜአቸውም ገና ስለነበር የአባ ኤስድሮስ አገልጋይ ሆነው ጥቂት ቆይተው ነበር።

"ከቶዩ በኋላስ?" ሚራዥ አባ አልፋ የተባሉት መነኩሴ ከአባቱ ከአባ ገርንበሩ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያላቸውና ምስጢረኛም እንደነበሩ ስለሚያውቅ እርሳቸው በህይዎት እንዲኖሩ በልቡ ተማፀነ፡፡

"አልፋ የት እንደ ደረሱ አይታወቅም፡፡ ስለ እርሳቸው ሊያውቁ የሚችሉት አባ ኤስድሮስ ብቻ ናቸው፡፡"

"አልፋ... አልፋ... አልፋ..." ሲጻራና ሜሮዳ ይህን ስም በባኮስ ማስታወሻ ውስጥ ያዩት መስሏቸው ከሚራዥ ኋላ ሆነው እርስ በእርስ ተንሾካሾኩ፡፡

"አባ ኤስድሮስን ማግኘት አንችልም ታዲያ..." ሚራዥ በእድሜ የገፉትን መነኩሴ አፋጠጣቸው፡፡

መነኩሴው ፈገግ አሉና "እያወከው ልጄ? የአባ ገርንበሩ ልጅ ሆነህ እንዴት ይህ ይጠፋሃል?!" ሲሉ ጥያቄውን በጥያቄ መለሱለት፡፡ "የዘጋ መነኩሴ እኮ ማንንም አያናግርም፡፡ እንኳንስ ከሌላ ሰው ጋር ለነፍሱ መያዣ በቀን አንዴ ብቻ ጭብጥ ጥሬና ጠብታ ውሃ በሸንቁር የሚያቀብለውን አገልጋዩን እንኳን አያናግርም፡፡"

ሁሉም በፀጥታ ተዋጠ፡፡ ሚራዥ ወደ ኋላው ዞሮ ሰያይ ከጀርባው የቆሙት አባላት በሙሉ ፊታቸው ከመቅፅበት ጠውልጎ ተመለከተ፡፡

ሚራኘ ጊዜ ማባከን አልፈለገም። በፍጥነት ጥቂት ሰዎችን ብቻ ከብዙሃኑ ውስጥ መርጦ ወደ ሌላ ክፍል እንዲከተሉት አደረገ። ዣንጊዳ፣ ኮራኮስ፣ ማርዬ ዋቆ ማርዬ፣ ጌራ፣ ሲጳራ፣ ሜሮዳ፣ ሳደፍ እና ሻጊዝ ብቻ ነበሩ ለስብሰባ የተጠሩት። ገና ገብተው ከመቀመጣቸው ነበር ሚራኘ ለምክክር መነሻ የሆነውን ጥያቄ ያስከተለው።

"አሁን ከሁላችንም ሀሳብ እንዲዋጣ የምፈልገው የዘጉትን መነኩሴ እንዴት ማናገር እንደ ምንችል መላ የሚል እንዲሆን ነው። ከማን ልጀምር... እሽ ሻጊዝ..."

"በገዳማዊነት... አንተ ከሁላችንም የተሻለ እውቀት እንዳለህ ጥርጥር የሌላው ጉዳይ ነው። እንደ'ኔ እኒህን የዘጉ መነኩሴ ማናገር የሚቻል አይመስለኝም። የጋለ ብረት በአፋቸው ብንሰድባቸው እንኳ የሚናገሩ አይመስለኝም።" ብሎ ሻጊዝ ዝም አለ።

"እኔም የምስማማው በሻጊዝ ሀሳብ ነው።" ሲል ጌራ ተከተለ። "አባ ኤስድሮስን አውቃቸዋለሁ። ከአላማቸው ንቅንቅ የሚሉ ሰው አይደሉም። እኛ እናናግረዎት ብንል፣ ሰይጣን ሊፈትነኝ እነሱን ተመስሎ መጣ ብለው እርፍ ነው የሚሉት። በመሆኑም ሰይጣናት ሊፈትኗቸው ስለመጡ ውጊያቸውን ይበልጥ በማጠናከር ላይ ብቻ ያተኩራሉ። ሰይጣናቱ ሊፈትኗቸው ስለመጡ ፈጣሪ ፅናታቸው ለመገምገምና ለተሻለ ክብር እንዳጫቸው ከመገመት በቀር

ለእኛ አዎንታዊ ምላሽ ይሰጡናል ብሎ ማሰብ ያስቸግረኛል።
ሲል ጌራም ደመደመ።

"እንደ እንደኔ ሲጻራና ሜሮዳ በፃፉት ማስታወሻ ውስጥ ስለ አልፋ አገኘነው ያሉት ጥቅስ ቢመረመር ሳይሻል አይቀርም።" ዣንጊዳ የሚወረውረው ሀሳብ ይህ ብቻ ነበር። ወዲያው ሲጻራ የባኮስን ማስታወሻ ከፍታ ስለ አልፋ ያገኙትን ጥቅስ አነበበች።

"በዚህ ማስታወሻ ውስጥ የሚበዙት አስማት መሰል ቃላት ቢሆኑም ስለ አልፋ የተፃፈው ግን በግዕዝ ቋንቋ ነው። እሱም አንድ አረፍተ ነገር ብቻ ሲሆን "አልፋ የአምር ባህቲቱ የሚል ነው።" ብላ ማስታወሻውን ከደነች።

"ይህ እኮ ታዲያ ግልፅ ነው" አለ ሜራዥ ማስታወሻውን ተቀብሎ ጥቅሱን ከመረመረ በኋላ። "አልፋ ብቻ የአምር ባህቲቶ ማለት- አልፋ ብቻ ያውቃል- ማለት ነው።"

"ምንድን ነው አልፋ ብቻውን የሚያውቀው ነገር?" ሜሮዳ ማስታወሻውን ተቀብላ ደጋግማ ተመለከተች። በግዕዝና በአማርኛ የተፃፈው ይህ ማስታወሻ ሌሎች አስማት መሰል ቃላትም እንደለማኝ ቆሎ ተሸባልክውበታል። ሜሮዳ ግዕዝ ባታውቅም ከተተረጎመላት በኋላ- አልፋ የአምር ባህቲቶ ከሚለው አረፍተ ነገር ላይ አፈጠጠች።

"አልፋ ብቻውን የሚያውቀው ነገርማ አልፋ ብቻውን የሚያውቀው ነገር ነው። አልፋ የሚያውቀን ለማዎቅ አልፋን ራሱን መጠየቅ ብቻ ነው።" ማራኺር ሁሉንም ተራ በተራ እየተመለከተ ተናገረ።

"ስለዚህ..." ሳዶና ለመጀመሪያ ጊዜ ተነፈሰ።

"ስለዚህማ አልፋ ያለበትን ቦታ የሚያውቁትን አባ ኤስድሮስን መጠየቅ ነው።" ማራኺር አሁንም በመጀመሪያ ሀሳቡ ፀና።

"አይቻልም እንጂ ቢቻልማ ኖሮ..." ማርዬ ጥቆ ማርዬ ነገሩ አዙሪት ሲሆንበት ፈገግ አለ።

"ይህን ለእኔ ተውት... " ማራኺር ጌራን ብቻ ይዞ ወጣ። "ጌራ አባ ኤስድሮስ ይረሱኛል ብለህ ትገምታለህ?!" ከዋሻው እየወጡ እያለ ጠየቀው።

"አዎ!"

"እንዴት?"

"ጃጅተዋል'ኮ... እንኳን ዛሬ ያኔም እርጅና እየተጫናቸው ነበር።"

"ያባ ጀንበሩ ልጅ እንደሆንኩ ደጋግሜ እነግራቸዋለሁ።"

"መጀመሪያ ሲያናግሩህ እኮ ነው። ጥያቄው እኮ እሱ ነው። ያናግሩሃል?" ከዋሻው ሲወጡ ሁለቱም በጭንቀት ተወጥረው ነበር።

# ፯

## ቦሌ÷አዲስ አበባ

በኒቆዲሞስ ቢሮ ውስጥ ግድግዳው ላይ የተንጠለጠለው ውድ ሰዓት 4:33 የሚል ቁጥር ያሳያል፡፡ ባሁኑ ሰዓት ከእርሱ በቀር በዚህ ቢሮ ውስጥ ሌላ ሠራተኛ የለም፡፡ በቅርቡ እንደሚያደርገው ፀሐፊውን በጊዜ ነበር ወደ ቤቷ እንድትሄድ ያዘዛት፡፡

ከእንግዳ መቀበያ ቢሮው ጀርባ ፈረስ የሚያስጋልበው ሳሎን ይገኛል፡፡ ወደዚህ ሳሎን ከእርሱ በቀር ማንኛውም የቢሮው ሠራተኛ እንዲገባ አይፈቀድለትም፡፡ የሚቷ አክስቱ ልጅ ብቻ በዚህ ሳሎን ውስጥ መግባት ያለባቸውን ነገሮች አስቀምጣ መለስ ትላለች፡፡ የሳሎኑን ዕዳት ጠብቃ፣ የሚገቡ መጠጦችን በየፈርጃቸው ደርድራ፣ ያለቁ ጠርሙሶችን ይዛ ትወጣለች፡፡ በተረፈ ወደዚህ ሳሎን ከጋሙስ አባላትና ከአንዳንድ ከጋሙስ ጋር ጥብቅ ድርድር ከሚያደርጉ ልዑካን በቀር የራሱ የኒቆዲሞስ ባለቤትና ልጆች እንኳ ዝር አይሉም፡፡

ኒቆዲሞስ የተንጣለለውን ግቢ በሙሉ በሥውር ካሜራ እያቀረፀ የሚያስተላልፈውን ሰፊ እስክሪን ተመለከተ። አስቀድሞ እጅግ ሥልጡን ለሆኑት የግቢው ጠባቂዎች በዚህ ሰዓት በሚመጡት እንግዶች በሩ እንዲከፈትላቸው ባስተላለፈው ትዕዛዝ መሠረት ሰፊው በር ተከፍቶ ጥቁር ላንድ ክሩዘር መኪና ገባ።

ወዲያው ከኋላኛው የመኪናው በር ሁለት ነጮች ወረዱ። መኪናውን ያሽከረክር የነበረው ሌላ ግዙፍ ጥቁር አሜሪካዊም እነሱን ተከትሎ ወረደ። ከጥጋቸው የቆሙት ሁለት ቀልጣፋ የጋሙስ ኮማንዶዎች በሶስቱም ሰዎች ላይ ቆዳ መግፈፍ የቀረውን ፍተሻ ካካሄዱ በኋላ ይዘዋቸው ወደ ኒቆዲሞስ ቢሮ አመሩ።

ኒቆዲሞስ ጥቁር እንግዶቹን ለመቀበል አቆበቆበ። ገና ወደ ቢሮው ከመግባታቸው የናፈቀ ዘመዱን እንሚቀበል በደስታ እየተፍለቀለቀ የእንኳን ደህና መጣችሁ ምኞቱን ከገለፀላቸው በኋላ፣ ሁለቱ ኮማንዶዎች ወደ ውጭ እንዲሄዱ በዓይኑ ነገራቸውና ሶስቱን እንግዶቹን እየመራ ወደ ልዩው ሳሎን ገባ።

ሳሎኑ ከወትሮው በተለዩ ሁኔታ ተሰናድቷል፡፡ መሀል ለመሀል የተዘረጋው ጠረጴዛ ልዩ ሀምራዊ ልብስ ለብሶ በላዩ ላይ ውድ መጠጦችና የሚበሩ ሻማዎች ተደርድረውበታል፡፡ ከግድግዳው ጥግ የተገጠመው ምድጃ እሳት ይንቀለቀልበታል፡፡

"ማስተር ኒቆዲሞስ… ይህ ቢሮህ ነው ወይስ መኖሪያህ ቤትህ?" ሲል ዶናልድ የተባለው ዋና እንግዳው በመስተንግዶው በመደነቅ ጠየቀ፡፡

"ሥራዬ እጅግ ፋታ ባለመስጠቱ የተነሳ ወደ ቤቴ ለመሄድ እንኳ ጊዜ አጣለሁ፡፡ ቢሮዬም ቤቴም ብንለው ይቀላል፡፡" ኒቆዲሞስ ፈገግ ብሎ መለሰ፡፡ "ይልቅስ ለጥም ያህል የምትፈልጉትን ቅዱ፡፡ እዚህ ቢሮዬ ውስጥ የገባ እንግዳ ራሱን እንዲያስተናግድ ይገደዳል፡፡ ነፃ ሁኑ፡፡"

"ስለዚህ መስተንግዶህ እናመሰግናለን፡፡" በማለት ዶናልድ የሚወደውን ብሉ ሌብል ቀድቶ ተጎነጨ፡፡ ሌሎችም ተከተሉት፡፡

"እኔ እንኳ ብላኩን እመርጣለሁ" ካለ በኋላ ኒቆዲሞስ ወደ ብላኩ እጁን ሰደደ፡፡ "አልፎ አልፎ የኖረ የጣሊያን ወይን ይመቸኛል፡፡"

"የፈረንሳይ አይሻልም?"

"እሱንም ከፈለክ አለልህ፡፡"

"ላሁኑ ይኸው የጀመርኩት ይሁን፡፡ አመሰግናለሁ፡፡" ዶናልድ "አመሰግናለሁ" የሚለውን በአማርኛ ለማለት ተኮላተፈ፡፡

"አማርኛ ለመድክ?" ሲል ኒቆዲሞስ የተደነቀ ለመምሰል ሞከረ፡፡ ዶናልድ ከአሜሪካ ከመጣ ገና አንድ ቀን ብቻ ያለፈው እንደሆነ ያውቃል፡፡

"ኢንጅነር ሻጊዝ ቶሎ ካልተያዘ፣ ያው እንግዲህ ጥሩ ያማርኛ አስተማሪ ሆኜ እዚሁ መቅረቴ ነው፡፡"

"ችግር የለም በቅርቡ እሱን ይዘህ ትሄድና አማርኛ ለመማር እንደገና መመለስህ የማይቀር ነው፡፡" ሲል ኒቆዲሞስ ብላክ ሌብሉን ቅድቶ ብርጭቆውን ለቺርስ ከፍ አደረገ፡፡ እነሱም አፀፋውን መለሱ፡፡

"ለመሆኑ የክፍያውን ጉዳይ አስበህ ጨረስክ?" ዶናልድ የተጎነጨውን ገርግጮ ካጣጣመ በኋላ ጠየቀው፡፡

"አዎ!" አለ ኒቆዲሞስ ወደጣራው ዓይኖቹን ወርውሮ፡፡ ጥቂት ካሰበ በኋላ "ሶስት ሚሊዮን ዶላር ይበቃል፡፡" "በዙ ነው!" አለ ዶናልድ በፍጥነት፡፡ "ሚስተር ዶናልድ…" ኒቆዲሞስ በረጅሙ ተንፍሶ ዶናልድ ላይ አፈጠጠ፡፡

"አገርህ አንድ አሸባሪ ለመያዝ ምን ያህል የሰውና የቁስ ዋጋ እንደ ምትከፍል አውቃለሁ፡፡ ኢንጂነሩ ደግሞ በጠላቶቻችሁ እጅ ቢገባ ምን ያህል ዋጋ እንደምትከፍሉ

ጠንቅቀህ ታውቃለህ፡፡ ሶስት ሚሊዮን ያልኩህ ክፍያ ለኢንጂነሩ ብቻ ነው፡፡ ለጥቁሩ ሳጥን ግን ሌላ ሶስት ሚሊዮን ዶላር እጠይቃለሁ፡፡ ኢንጂነሩንም ሆነ ጥቁሩን ሳጥን ለመያዝ ለማወጣው ወጪ ግን ምንም ክፍያ አልጠይቅም፡፡"

"ሚስተር ኒቆ..." አለ ዶናልድ ለመቃወም እየሞከረ፡፡ "...ኢንጂነሩ እኮ የናንተም ጠላት ነው፡፡ በእናንተ የሚመራው ሥርዓት ከሥሩ እንዲመነገል የሸፈተ ሽፍታ ነው፡፡ ወቅት እና ጊዜ ከተመቻቸለት ደግሞ እናንተን ከመጠራረግ ወደ ኋላ እንደማይል የተረገጠ ነገር ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ሰው የጋራ ጠላታችን ነው ማለት ነው፡፡"

"እሱን አላጣሁትም፡፡ ሰውየውን መያዝ ግን ቀላል ነገር እንዳልሆነ ታውቀዋለህ፡፡ ከዚህ በፊት ሮበርት ጋሎ የሚባል የናንተው ወኪል የሆነውን አታውቅም?... ያዝኩት ብሎ ጣጣውን ጨርሶ ሲመጣ ከአዲስ ዘመን ከተማ ከመውጣቱ ነው ለወሬ ነጋሪ ሳያስቀሩ ደምስሰው ኢንጂነሩንና ጥቁሩን ሳጥን የመለሱት፡፡ ስለዚህ ይህን ሰው ለመያዝ ከፍተኛ ስልጡን ኃይል እንደሚጠይቅ ካንተ የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡" ኒቆዲሞስ ውስኪውን ተጎንጭቶ እያወራረደ በሀሳቡን ወደ ጣቅርን ተራራ ወጣ፡፡ ያስለጠናቸው ኮምንዶዎች ተራራውን ሰብረው ገብተው ኢንጂነሩን እስከ ጥቁር ሳጥኑ አንቀው ሲያስረክቡት በሀሳቡ ተመልክቶ ፈገግ አለ፡፡

"ተግባባን ሚስተር ዶናልድ ይኸው ነው እንግዲህ። ይልቅስ ነገሩን በቀላል አትመልከተው። እንደ ከዚህ ቀደሙ ባልተጠናና በተቻኮለ ሁኔታ ሳይሆን እጅግ ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ይከናወናል።" ኒቆዲሞስ ከሀሳቡ ተመልሶ እንደገና ተንነጨና ሲጋራውን አቀጣጠለ።

# ፯

## ዲጋ÷ኢትዮጵያ

ሚራኘና ጌራ ከምድር ውስጡ ዓለም እንደወጡ በቀጥታ የዘጉ መናኞችን ወደ ሚያገለግለው ጎልማሳ መነኩሴ በአት ነበር ያመሩት፡፡ ከምሽቱ አምስት ሰዓት አካባቢ ቢሆንም መነኩሴው ሻማውን ለኩሶ “ማር ይስሐቅ” የሚባለውን መፅሐፍ ሲያነብ ነበር የደረሱበት፡፡ ሚራኘርንም ሆነ ጌራን ስለሚያውቃቸው ምን ገጥሟቸው ይሆን በሚል በድንጋጤ መፅሐፉን ዘግቶ ነበር የተቀበላቸው፡፡ ወደ ዋሻው እየገባ በቃጠሎ የወደመውን የምድር ውስጥ አለም ያቅሙን ሲያስተካክል የነበረ ትጉህ ሰው እንደሆነ ያውቃሉ ሚራኘና ጌራ፡፡ ጉዳዩን ባጭሩ ካስረዱትም አባ ኤስድሮስ የት እንደዘጉ ለማሳዬት እምቢ እንደማይላቸው እርግጠኞች ነበሩ፡፡ ሆኖም መነኩሴው የዋዛ አልነበረም፡፡ ይህ አይነቱ ጉዳይ ከዚህ በፊት ተደርጎ ባለመታወቁ ራሱን ለማሳመን ጊዜ ፈጀበት፡፡ የኋላ ኋላ ግን እያቅማማም ቢሆን አባ ኤስድሮስ ወደ ዘጉበት በአት ይዟቸው ሄደ፡፡

አባ ኤስድሮስ የዘጉባት በአት ከዳመ በስተምዕራብ በኩል እጅግ በጣም ወደ ውስጥ ገብታ የተቀለሰች ብቸኛ ጎጆ ናት። በሯ ተጠርቅሟል። ወደ ውስጥ የሚያሳይ ጭላንጭል እንኳ የለም። በጀርባ በኩል ግድግዳዋ ላይ ክብ ሽንቁር አለች። ይህቺ ሽንቁር አንድ ሰሃን ብቻ የምታሳልፍ መስኮት ተብዬ ናት። ረዳቱ መነኩሴ በዚህች መስኮት ነው ለነፍስ መያዣ የምትሆነውን አሹቅ አስቀምጦላቸው ዘወር የሚለው። አባ ኤስድሮስ ከስንት አንዴ ብቻ ነው እሹቁን ወደ ውስጥ የሚስቧት።

የዛሬዋን አሹቅ አልወሰዷትም። ሚራኘርና ጌራ በድንጋጤ ክው ብለው ተያዩ።

"አርፈው ይሆን?" ሲል ሚራኘር በጌራ ጆሮ አንሾካሾከ። "አርፈው ከሆነ 'ሁሉም ነገር አበቃለት' ስትል ባለፈው የተናገርከው እውን ሊሆን ነው።"

"ፈጣሪ ይርዳን ሚራኘር።"

"አባ" ሲል ረዳቱ መነኩሴ በለሆሳስ በመስኮቷ ተጠግቶ ተጣራ። "አባ" ምላሽ የለም። "አባ"... አሁንም አባ ኤስድሮስ ምላሽ አልሰጡም። ጥሪው በጌራም በሚራኘርም ተደጋገመ። ሆኖም ከራሳቸው ድምፅ በቀር የተሰማቸው ነገር የለም። ከነሱ ድምፅ በተጨማሪ የሚሰማው አንዳንድ ጥቃቅን የጫካው ውስጥ ፍጡራን የሚያሰማው ለነሱ ትርጉም

የማይሰጥ ድምፅ ነው። ጥሪውና ትንሹዋን ሽንቁር ማንኳኳቱ ከሁለት ሰዓት በላይ ዘለቀ። ሆኖም የአባ ኤስድሮስ ድምፅ ሊሰማ አልቻለም።

"ምንልባት ፀሎት ላይ ሆነው ይሆን?"

"ይሆናል..."

"ለምን በሩን ሰብረን አንገባም?" ሚራዥ ወደ በሩ ሄደ። "ይህማ ሊሆን አይችልም" ሲል ረዳቱ መነኩሴ ተቃወመ። "አይሆንም ሚራዥ! ይህ ተደርጎ የማይታወቅ ነገር ነው። ይህን ለማድረግ የጌታ ፈቃድም አይደለም። እርሳቸውንም ቢሆን መፈታተን ነው። የሚሆነው። በዛ ላይ መረገምም አለ። እኔም ብሆን እርሳቸው ከሰይጣን ጋር የሚያደርጉትን ውጊያ ከውጪ ሆኜ እንዳግዛቸው እንጂ እንዳሰናክላቸው አልተወከልኩም"

"እኛም ሥጋ ከለበሰው ከምድራዊው ሰይጣን ጋር በመፋለም ላይ ነን። ቢገባህ ይህ ጦርነት የርሳቸውም ጦርነት ነው። ለዘመናት የለፉለት አላማ ከእሳት በተረፍነው ልጆቻቸው አለመክሰሙን ማየት አለባቸው።" ሚራዥ በሩን በኃይል ወደ ውጪ ሲስበው ከእንጨት የተሠራውና ዘመን ያስቆጠረው በር አቃሰተ። የጭቃ ምርጉ እየተቀረፈ ወረደ።

ረዳቱ መነኩሴ ሚራዥን ከኋላ ትትቶ ግብግብ ገጠመው። ሚራዥ መነኩሴውን ወደ ኋላው ለመግፍተር ያደረገው

መከራ በቀላሉ አልተሳካም፡፡ ደባስ ብሎ መነኩሴው ሚራዥን ተሸክሞ ከጎጆዎ ለማሸሽ ሞከረ፡፡

"ምን ነካህ ሚራዥ?!...ኸረ በወላዲት አምላክ! ስንት ነገር እያወክ እንደዚህ ታደርጋለህ?..." ይማፀን ጀመር፡፡ መነኩሴው ሚራዥን ጠፍንጎ ቢያስቀርም ጌራ ከእንጨት የተሠራውን በር ገንጥሎ ጎጆዋን ከፍቷት ነበር፡፡

መነኩሴው ከዚህ በላይ መታገል አልፈለገም፡፡ ቀድሞም ቢሆን ኃላፊነቱን ለመወጣት ያህል እንጂ ሚራዥን መቃወም አልፈለገም ነበር፡፡

ጌራ በሩን እንደከፈተ ሲያውቁ ሁለቱም ተላቀው ወደ ተከፈተው በር ዓይኖቻቸውን ሰደዱ፡፡

ጎጆዋ በጨለማ ተውጣለች፡፡ በሩ ሲከፈት በጥቂቱ ወደ ውስጥ የገባው የጨረቃ ብርሃንም ከአንድ ክንድ በላይ አላሳያቸውም፡፡ ረዳቱ መነኩሴ ከቀሚስ ኪስ ክብሪትና ሻማ አውጥቶ ካበራ በኋላ ከበሩ መቃ ምድር ሳያልፍ ሻማውን ወደ ውስጥ አስቀደመ፡፡ አባ ኤስድሮስ ያለ አንዳች ብርሃን መፅሐፍ እያነበቡ ከጎጆዋ ግድግዳ ጥግ ተቀምጠው ነበር፡፡ ያነቡት የነበረው መፅሐፈ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከ388ዓ.ም የተለያዩ መናኞች እየተቀባበሉ የፃፉትንና መፅሐፈ ገነት

ተብሎ የሚታወቀውን መፅሐፍ ነው። ስለ በርሃ መናንያን ታሪክና ብሂል ይዘግባል።

አባ ኤስድሮስ አንዳች ኮሽታ እንኳ ያልተፈጠረ ያህል መፅሐፋቸውን ሲያነቡ ቆይተው ቀና አሉ። ምንም ሳይናገሩ ሶስቱንም አፈራርቀው ተመለከቷቸው። ሶስቱም በተቀመጡበት ባንገታቸው በመስገድ እጅ ነሱ።

ለደቂቃዎች ፀጥታ ከነገሰ በኋላ "አባ እባክዎትን ይቅርታ ያድርጉልን። ይህን ድፍረት የፈፀምነው ቢጨንቀን እንጂ ወደን አይደለም። መቼም ሁላችንንም ያውቁናል። እኔ የአባ ገ/ንበሩ ልጅ ነኝ። እነዚህንም ያውቋቸዋል። ከእሳቱ የተረፍን ጥቂት ሰዎች ነበርን። በተራራው ውስጥ እንኖር ነበር። አሁን ግን ከተራራውም ጠላቶቻችን አሳደውናል። ወደ ዚህም እኛን ተከትለው እየገሰገሱ ናቸው። መዳን የምንችለው በእርስዎ ፀሎትና መርዳትም እንደተጠበቀ ሆኖ... ከዚህ ወጥተን የምንጠለልበትን እንዲመሩን እንማፀነዎታለን።" ብሎ ሚራኘር ዓይን ዓይናቸውን በተማፅኖ ይመለከት ጀመር።

አባ ኤስድሮስ ለረጂም ደቂቃዎች ሶስቱንም ሲመለከቱ ከቆዩ በኋላ ፅንባ በእርጅና ከሞጨሞጩ ዓይኖቻቸው ቅርር ይል ጀመር። በኋላ ቀስ ብለው እየተንፏቀቁ ወደነ ሚራኘር ቀረቡ።

በሚቀጠቀጥ እጃቸው የሚራኘን እጅ ስበው ሳሙት፡፡ ከዛ ገሀነማዊ እሳት በመትረፋቸው ተአምር የተፈፀመ ያህል ቆጥረውታል፡፡

"እ... አባትህ ታላቅ ነበር... አን... ተም... ታላቅ ነህ..." አሉ አባ ኢስድሮስ እንደ ጎለጎለ ክር በሚንቀጠቀጥ ድምፃቸው፡፡ ሲናገሩ ራሳቸውም አብሮ ይንቀጠቀጣል፡፡ "... ጣ...ጣቅርን ተራራ ሄዱ፡፡ ... እዛ ነው ሌሎቹ ወንድሞቻችን ያሉት፡፡"

"እዛማ ነበርን፡፡ ጠላቶቻችን ያሳደዱን ከዛ ነው፡፡"

"እ... እኔ እላክ የነበረው ወደ'ዛ ነበር፡፡ ሌላኛውን የሚያውቀው..." አሉና አቀረቀሩ፡፡ ለረጂም ደቂቃዎች አቀርቅረው ቆይተው በቀጭን አንገታቸው ራሳቸውን በመከራ ጎትተው አቃኑና አፋቸውን ከፍተው ቆዩ፡፡ የሚናገሩበት ጊዜ ያመት ያህል የረዘመባቸው ሚራኘርና ጌራ አብረው አፋቸውን ሳይታወቃቸው ከፍተው ተጠባበቁ፡፡

"... አልፋ... አልፋ ነበር ሌላኛውን ቦታ ከሚያውቁት የተረፈው፡፡"

"አ... አልፋ... አልፋ ወዶት ነው... ወ..." ሚራኘር ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ አለ፡፡

"...ሩቅ ነው፡፡ አታገኙትም ሩቅ... ነው፡፡" አባ ኢስድሮስ ወደ ጣራው አንጋጠጡ፡፡

"ምነው... አርፏል?! ጌራ ተስፋ በቆረጠ ድምፅ ጠየቀ፡፡

"... አ... አይ... እሱን አላውቅም... ግን..." አባ ኤስድሮስ አልፋ የሄደበትን ለማስታወስ ሞከሩ፡፡ "... ገዳመ አስቄጥስ ሄዷል፡፡ አስቄጥስ በረሃ..."

ሚራችና ጌራ ዝነኛው አስቄጥስ በረሃ የት እንደሚገኝ ስለሚያውቁ በድንጋጤ ተያዩ፡፡ የአስቄጥስ በረሃ የሚገኘው ግብረፅ ሀገር ቢሆንም በውስጡ ብዙ ገዳማት ስለሚገኙ አባ አልፋ ከየተኛው ገዳም እንደገቡ ለማዎቅ አስቸጋሪ እንደሆነ ተገንዝበውታል፡፡

"አስቄጥስ በረሃ ከየትኛው ገዳም ለመግባት እንደሄዱ ነግሮዎታል?"

"ከአቡነ እንጦንስ ገዳም መግባት እንደሚፈልግ ነበር የነገረኝ፡፡ ተው እዚሁ ፅና... የበረሃውን ፈተና አትችለውም ብዬ ብመክረው አሻፈረኝ ሲል ጊዜ ፀሎት አድርጌ ላኩት፡፡ አልፋ ጥንታውያን አባቶች የተፈተኑበትን በረሃ የመረገጥ ህልም ነበረው፡፡ እግዚአብሔር በደህና ካደረሰው እንግዲህ እዛ ይሆናል፡፡ ከልቡ የተራመደ መድረሱ አይቀርም፡፡"

ረጅም ፀጥታ፡፡

# ፲

## ሺላ ደ ሴይቫ÷ኮሎምቢያ

ከአራት ሺህ ካሬ ሜትር በላይ በሆነ መሬት ላይ የተንጣለለው የዶን ቦናኖ ግቢ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ በታጠቁ ፈርጣማ ፈርጣማ ጋርዶች ይጠበቃል። ጥቅጥቅ ባለ ደን በተሞሸረው በዚህ ግቢ ውስጥ የምታርፍ ወፍ ሳትቀር በዓይነ ቁራኛ ትታያለች። ወደ ውስጥ የሚዘልቅ የታወቀም ሆነ ለጉዳይ ተጠርቶ የመጣ ወዝልውጥ ሰው፣ ጥብቅ ፍተሻ ይካሄድበታል።

ታዴዎስ ኢያሱ ቆዳውን የገፈፋት እስኪመስለው ድረስ በፈርጣማዎቹና ጊንጥና እባብ ክንዳቸው ላይ በተነቀሱ ጋርዶች ተፈትሾ ሲያበቃ፣ አንዲት ሴት ተጠርታ መጣች።

ሴቲቷ ከውስጥ ሱሪና ከጡት ማስያዣ በቀር የለበሰችው ሌላ ነገር የለም- መለመላዋን ናት ማለት ይቀላል። መላ አካሏ እንደ ቤተ መቅደስ ግድግዳ በስዕል ንቅሳት ተኈርጎርጉሯል። የዓይኖቿ ሽፋሎች ኩል ተደፍድፎባቸዋል። የዓይኖቿ ጭሯዎች ቀጥ ቀጥ ብለው ከመቆማቸው የተነሳ እንደ ጃርት

እሾህ የሚዋጉ ይመስላሉ። መላ አካሏ ከሥላስ የተሠራ ይመስል አብለሲት እንደበላች ፍየል በስጋኒሽ ቋንቋ ትለፈልፋለች።

ታዴዎስ ኢያሱን ስታስተውለው ከቆየች በኋላ ሌላ የማጣሪያ ፍተሻ አደረገችለት። ሁልጊዜም በዚህች ሴት ሳይፈተሽ ማንም ሰው ወደ ዶን ቦናኖ አይቀርብም። ከዚህች ሴት ፍተሻ የሚያመልጥ አንድም አደገኛ ነገር እንደማይኖር ይነገርላታል። በአካባቢው የታወቁት ካርዲናል እንኳ በዚህች ሴት ሳይፈተሹ ወደ ዶን ቦናኖ ቀርበው አያውቁም። በሴት መፈተሽ እንግዳ ነገር ቢሆንበትም በዚህች ሴት ጣቶች መላ አካሉ ሳይበረበር ማንም ቢሆን የዶን ቦናኖን ፊት አያይም።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ታዴዎስ ኢያሱ ሌላ ፍተሻ እንደሚቀረው ያውቃል። ሴቷ ፈትሻው እንደጨረሰች "ካላ" ብላ ተጣራች። ወዲያው አንዲት ጦጣ እየዘለለች መጣችና ከታዴዎስ ትክሻ ላይ ዘላ ጉብ አለችበት።

"ወይዘሪት ካላ" በፍተሻ እና በእፅ ማዘዋወር አንቱ የተባለች የዶን ቦናኖ ጦጣ ናት። የራሷ የግል ሀኪም ያላትና እፅ ማዘዋወርም ሆነ መፈተሽ ተክናበታለች ተብሎ የተጨበጨበላት ይህችው ጦጣ ታዴዎስን ምንትርትር

አድርጋ ከፈተሸችው በኋላ ከኪሱ ውስጥ ካገኘችው የሲጋራ መለኮሻ በቀር እንግዳ የሆነ ነገር ባለማግኘቷ ዘላ ወረደችና የሲጋራ መለኮሻውን ይዛ እየተንበቀበቀች ወደ ቤት ሮጠች። ሁልጊዜም ወይዘሪት ካሳ በፍተሻ ያገኘችውን ለማንም ሳትሰጥ ለዶን ቦናኖ ማስረከብ አለባት።

ሉቴቲም ሆነ ጋርዶቹ ይህችን ልዩ የሆነች የሲጋራ መለኮሻ ከዚህ በፊት ታዴዎስ ኢያሱ ይዟት እንደ ነበር ስለሚያውቁ በጦጣዋ ምርጥ ፈታሽነት ቢደነቁም ታዴዎስን ከዚህ በኋላ እዚህ ማቆም እንደሌለባቸው ስለሚያምኑ በሉቴቲ መሪነት ወደ ዶን ቦናኖ እንዲገባ ተፈቀደለት።

ታዴዎስ ኢያሱ እንደ ሁልጊዜው በጦጣዋ ድርጊት እየተገረመ በዚህ ግቢ ውስጥ ያሉትን ለማዳ እንስሳት ግራና ቀኝ እየተመለከተ ወደ ውስጥ አመራ። በግቢው ውስጥ ጥቋቁር አናብርት፣ ፓሮት እና ዘንዶዎች ይገኛሉ።

የዶን ቦናኖ ጠላት የሆነ ማንኛውም ሰው ተገድሎ ወይም እስከ ነፍሱ ለነዚህ እንስሳት ይጣላል። ፓሮቶቹ ዶን ቦናኖ የሚለውን በመድገም ትዕዛዙ በጥብቅ እየተላለፈ እንዲሆን እንዲገባው ማንኛውም ሰው ላይ ይጮሃሉ። ጥቋቁሮች ነብሮች አስቸጋሪን ለመቅጣት ወደር የላቸውም። ዘንዶዎቹ

በሬን እስከ ቀንዱ እንኳ ለመዋጥ አፍታ አይፈጅባቸውም። በተለይም አንደኛው ዘንዶ ርዝመቱም ሆነ ውፍረቱ ገና ሲያዩት በድንጋጤ ይገድላል። ይኸኛው ሞር ተብሎ የሚጠራው ግዙፍ ዘንዶ ሌላ ዘንዶ እየዋጠ ስላስቸገረ ለብቻው ቤት ተሰርቶለት ተቀምጧል። የዚህን ዘንዶ ጭካኔ የዶን ቦናኖ ጠባቂዎች ያውቃሉ። አንድ ጊዜ አንድ የተጠረጠረ የዶን ቦናኖ ጠባቂ ቢመረመር "ወይ ፍንክች ያባ ቢላዋ ልጅ" ብሎ አልናገር ይላል። በዶን ቦናኖና በአብዛኛዎቹ ማፍያዎች ያልተፃፈ ህግ መሠረት የተገረፈና የተመረመረ ሰው መልሶ ወዳጅ አይደረግምና ይገደላል። ይህንን ተጠርጣሪ ግን ለሌሎች ጠባቂዎች መቀጣጫ ይሆን ዘንድ ዶን ቦናኖ አንድ እድል ይሰጠዋል።

ይኸውም ዕድል ወደ ዘንዶዎች ተጥሎ ካመለጠ ነፃ ተደርጎ ወደ ሚፈልግበት እንዲሄድ ነበር። ሰውዬው ለነዚህ አደገኛ ዘንዶዎች ከመጣሉ እኔ እውጥ እኔ እውጥ እርስ በእርስ ይፋተላሉ። አንዱ በለስ የቀናው ዘንዶ ፈጠን ብሎ የሰውየውን ወገብ ጠፍንጎ ያስርና የሚሰፈልፍ አፉን ዘግቶ መዋጥ ይጀምሯል። ሌሎቹ ዘንዶዎች ተስፋ ቆርጠው ተጠቅልለው ሲቀመጡ ታላቁ ዘንዶ ግን ሰውዬውን የሚውጠውን ዘንዶ ከመጤፍ ሳይቆጥር ከሰውየው ጋር አብሮ ይውጠዋል።

ይህን ዘንዶ የመዋጥ ትርኢት ቆሞ ይመለከት የነበረው ዶን ቦናኖ በዚህ ሞር በተባለ ታላቅ ዘንዶ በመከራረት ከዛ ጊዜ ጀምሮ ሞር የሚል ስም አውጥቶለታል፡፡ "ሞር" የሚለውን ስያሜ የሰጠው ሞርሞርዲኖ የተባለ የጥንት ወዳጁን ለማስታወስ እንደሆነ በመናገር "ሞር" ማለት "ለጠላቱ የማይመለስ ማለት ነው" ሲልም የራሱን ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ታዬምስ ኢያሱ ወደ ዶን ቦናኖ አዳራሽ ሲገባ ወይዘሪት ካለ መለከሻውን ለዶን ቦናኖ እያገላበጠች ስታሳይ ደረሰ፡፡ ዶን ቦናኖ በጥንቃቄዋ እየተገረመና በከፍተኛ ኩራት ካላን እያወደሰ ነበር፡፡

በዙሪያው ስድስት እርቃን ሴቶች ከበው ይተሻሹታል፡፡ ከአዳራሹ መሃል የተዘረጋው ጠረጴዛ በሻማ ብርሃንና በወይን ደምቋል፡፡ ታዬምስ ኢያሱ ለእሱ አቀባበል ተብሎ ይህ ሁሉ እንደተሰናዳ ቆጥሮ እጁን ዘርግቶ በክብር ሊቀበለው ወደ ቆመው ቦናኖ እየተፍለቀለቀ ቀረበ፡፡

## ፱

### ዳጋ፥ኢትዮጵያ

የዶርቶጋዳ አባላትን ለሁለት ክፍሎ የሚያከራክር ሀሳብ ተፈጥሯል። አንደኛው ሀሳብ አልፋን ፍልጎ ሌላኛውን መደበቂያ መፈለግ ሲሆን ሁለተኛው ሀሳብ ደግሞ የዳጋውን ውስጥ ዋሻ አፅድቶ ወደ ቀድሞው መመለስ ነው። ሚራኝና ጌራ ወደ ዋሻው ከተመለሱ በኋላ አልፋ ግብፅ ውስጥ እንደሚገኝና ሌላኛውን ህዋስ የሚያውቀው እርሱ ብቻ እንደሆነ ነበር ክርክሩ የተጀመረው።

"አጉል ጊዜ ማባከን ነው። አልፋን በመፈለግ ጊዜ ከምናባክን ይህንኑ የቀድሞ ዋሻችንን አፅድተን ወደ ነበረበት መመለስ ነው።" ይላል አንዱ።

"ልክ ነው.. 'ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላ'..." ይላል ሌላው። "ከማያውቁት ተራራ የሚያውቁት ጉድጓድ ይሻላል።"

"ጣላቶቻችን እንደዘንዶ ሲውጡን አስፍስፈው እየመጡ ተጣጥበን እንጠብቃቸው ነው የምትሉት?"

"እዚሁ እየተፋለምን እንሞታለን።"

"ምን ማለት ነው? የመሞት አላማ ህልምን ለማኖር ካልሆነ ምን ዋጋ አለው?"

"ያለንበትን ላያውቁም ይችላሉ። ገና ለገና የምድር ውስጡን መንገድ ያገኙታል ብለን በመስጋት ባድማችንን ጥለን ለምን እንሰደዳለን? 'ሰማይ ይወድቃል ብሎ ባለ ተከለ አሉ'..."

"ላያውቁት ይችላሉ ብሎ ማሰብ እንኳ አዋጪ አይመስልም። ጠላትን ዝቅ አድርጎ መገመት የኋላ ኋላ ዋጋ ያስከፍላል። ሁልጊዜም ዝግጁ መሆን በኋላ 'ሱሪ ባንገት' ከማድረግ ያድናል። ...እንኳን ይህ ሁሉ ሰው የተጓዘበትን መንገድ ለመከተል... አንድ ሰው የተጓዘበትን እንኳ ለማግኘት የሚቀልበት ጊዜ አለ። በዛ ላይ ከኋላችን ጥለን የመጣነው ምልክት ሊኖር ይችላል።"

በክርክሩ መሀል "ከሁለቱም አንዱ ሳይሆን ቢቀርስ?" የሚል ድምፅ ከመሀል ተሰማ። ማን እንደተናገረው ግን አልታወቀም።

ይህ ሁሉ የጦፈ ክርክር ሲደረግ በአርምሞ ሲያዳምጥ የነበረው ሚራኘር የራሱን ሀሳብ ሰነዘረ። ሁልጊዜም ሀሳቡን በመጨረሻ በማቅረብ ይታወቃል።

"ሁለቱም ሀሳብ ልክ ነው።" ሲል ጀመረ ሚረኙ። ያባቶቻችን ቦታ ማዕዳቱና ወደነበረበት መመለሱ አስፈላጊ ነው። በዚህ ዋሻ ውስጥ የተከሰከሰው የወንድሞቻችንና ያባቶቻችን አጥንት ተሰብስቦ በክብር ቦታ መቀበር አለበት። ጥቅርሻና ስብርባሪው ሁሉ ተጠርጎ ቤታችን የድሮ መልኩን መያዝ አለበት። ይህ የሀገራችን ኢትዮጵያ ተምሳሌት ነው። ሁሉም ነገር ወደነበረበት ክብሩና ልዕልናው መመለስ አለበት። የሚጀምረው ከየትም አይደለም። ከዚሁ ነው። ሁላችንም መጥረጊያችን ማንሳት አለብን። ሀገራችንንም ሆነ ቤታችንን የወረሰውን ጥቅርሻ መጠራረግ አለብን። እዚህ የምንቀረው በሙሉ ይህንን የማድረግ ሀላፊነት አለብን። ሁለት ወይም ሶስት ሰው ደግሞ አልፋን ፍለጋ ወደ ግብፅ ይላክ። አባቶቻችን የሠሩት ሌላኛው ህዋስ ጠላት መጣም አልመጣም መገኘት አለበት። ደግሞም ቅድም እንደተባለው ጠላትን ዝቅ አርጎ መገመት ያስጠቃል። ቀኝም ነፊስ ግራ ሌላኛው ህዋስ ተፈልጎ ሁልጊዜ ከመሳደድ እንደ ከዚህ ቀደሙ በተረጋጋ ሁኔታ አላማችንን ለማሳካት ሥጋት አልባ ቦታ ማግኘት አለብን። በዚህ የማይስማማ አለ ብዬ አላምንም። 'መጀመሪያ የመቀመጫዬን' እንዲሉ ለዚህ ጉዳይ ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። ስለዚህ በተመሳሳይ ጊዜ ሁለቱንም ጉዳይ መሳ ለመሳ ማካሄድ ይቻላል። ይልቁንስ ጊዜ ሳናጠፋ ወደ ግብፅ

የሚላኩትን ሰዎች መምረጥ አለብን።" ብሎ ዝም አለ ሚራኘ።

"ወደ ግብዕ የሚላከው ሰው በዋናነት ሁለት ጉዳዮችን ማሟላት አለበት።" ሲል ሻጊዝ የሚራኘን ሀሳብ ያለማቅማማት ተቀብሎ ተናገረ። "አንደኛ አልፋ የሚፈለገው ገዳም ውስጥ በመሆኑ ገዳማዊ ህይዎትን በመጠኑ የሚያውቅ ሁለተኛ በረሃውን መቋቋም የሚችል መሆን አለበት።"

"ምን ጥያቄ አለው?..." ሲል ጌራ ወደ ሚራኘ ተመለከተ። "ሚራኘ ሁለቱንም ያሟላል፤ እኔም ብሆን የዴር33ን መሪ መጨበጤ አይቀርም። ሌላ አንድ ሰው ከተጨመረ በቂ ነው።"

"እኔ" አለች ሜሮዳ ወዲያው የተቆረጠ እጇን መኘርጣ።

"ሌላ ወዶ ዘማች አለ" ሲል ዣንጊዳ እጁን እሱም አወጣ።

"እኔስ" ስትል ሲጳራ ሁሉም ወደ እርሷ ግራ በመጋባት አፈጠጠ።

"እመጫት መሆንሽን ረስተሽ ነው?" ሻጊዝ ይህን ሲናገር ሁሉም ያፈነውን ሳቅ ለቀቀ። "ይልቁንስ እኔም አለሁ።"

"ሻጊዝ አንተ እንኳ እዚህ ያለውን ሁኔታ ብታስተባብር ይሻላል። እኛ እንበቃለን። መነኩሴ እንጂ አሸባሪ

ለመያዝ እኮ አይደለም ለመያዝ የምንሄደው!" አለ ሚራኘ በቁ እንደሆነ በመገመት።

ኀልህ እሺ። ሆኖም የምትሔዱት ወደ ግብፅ መሆኑን አትዘንጉ። በሆነ አጋጣሚ ብትያዙ ያለ አንዳች ፍርድ ማንኛውም ሰው በጎንጃችሁ ሊያርዳችሁ እንደሚችል ማወቅ አለባችሁ። ሀበሻ መሆናችሁ ከታወቀ ግብፅ ውስጥ ይህ ሁልጊዜም የሚደረግ ጉዳይ ነው። አያሌ ኢትዮጵያውያን የግብፅን በረሃ አቋርጠው ሲሰደዱ አንገታቸው ተቀልቶ የበረሃ አሞራ መጫዎቻ መሆናቸው የተረጋገጠ ነገር ነው።" በማለት ሻጊዝ አስጠነቀቀ።

ለእነ ሚራኘር ሽኝት ከተደረገ በኋላ መሽትሽት ሲል ዴር33 ከዳጋ ደሴት ተነስታ ሰማዩን እየሰነጠቀች የሰሜኑን አቅጣጫ ያዘች።

## ፲

## ቦሌ÷ አዲስ አበባ

ኒቆዲሞስና ዶናልድ ስለክፍያው አፈፃፀም ተነጋግረው እንዳበቁ "ኧረ ለመሆኑ የኢንጅነሩን ጥቁር ሳጥን ለምንድን ነው የምትፈልጉት?" ሲል ኒቆዲሞስ ሌላ ጥያቄ አስከተለ። "ለመሆኑ ምን ቢኖርበት ነው?" ዶናልድ ፈገግ ብሎ ጥቂት አሰብ አደረገና "አታውቁም ነበር?" ሲል ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት። "የማታውቁትን እቃ ነው ለመሸጥ ስትደራደሩ የኖራችሁት? ሚስተር ኒቆዲሞስ... ይህን አታውቅም ብዬ ለማመን እቸገራለሁ።"

"በእርግጥ ጫጫታውን ቀደም ሲል ሰምቻለሁ። ሰርጎ ገብ አባሎቻችን አንዳንድ ተረት ተረት የሚመስል ነገር ነግረውኛል። እኔ ግን ከአእምሮዬ ጭራሹን አስወጥቼዋለሁ።" አለ ኒቆዲሞስ ስለ ጥቁሩ ሳጥን ምስጢር የሰማውን ለማስታወስ እየሞከረ። "የጥንት አፈ ታሪኮቻችን በእንደዚህ አይነት አስማት መሰል ታሪኮች የተሞሉ ስለሆኑ በጥቁሩ ሳጥን ውስጥ የሚገኘው ምስጢር እፀ መሠውር ነው ሲሉኝ አላመንኩም።"

"ሚስተር ኒቆዲሞስ... የጥቁሩ ሳጥን ምስጢር በሙከራ የተረጋጠ ሳይንሳዊ ምስጢር እንጂ ተረት ተረት ቢሆን ኖሮ እኛም ይህን ያህል ባልደከምን፡፡ ኢንጂነር ሻጊዝ በሉስ አላሞስ የምርምር ማዕከል ውስጥ የሞከረው በምስጢር ተይዞ የነበረ ረቂቅ የምርምር ውጤት ነው፡፡ አንድ ብቻ አይደለም፤ የብዙ ግኝቶች ቀመር የተቀመጠበት ሳጥን ነው፡፡ ለምሳሌ አንዱን ተረት የሚመስል ግን እውነት የሆነ ግኝት ልነገርህ፡፡" ዶናልድ የጥቁሩን ሳጥን ምስጢር ያብራራለት ጀመር፡፡ "ግኝቱ በየቀኑ ከሚገጥመን እውነታ ላይ ተመስርቶ የተፈለሰፈ ግኝት ነው፡፡ በቀላሉ ለማስረዳት ያህል... ከእይታችን ላይ የተጨለፈ ፈጠራ ነው፡፡ ያለመታየት ምስጢር ነው፡፡ እንደሚታወቀው የትኛውንም ቁስ አካል የምናዬው በላዩ ላይ የሚያርፈውን የብርሃን ጨረር አንፀባርቆ ወደ ዓይናችን ሲያደርሰው ነው፡፡ ብርሃንን ውጦ የሚያስቀር፣ የሚያሳልፍ ወይም መልሶ የማያንፀባርቅ ቁስ አካል ሊታይ አይችልም፡፡ ሆኖም ሙሉ በሙሉ የብርሃንን ጨረር ውጦ የሚያስቀርም ሆነ የሚያሳልፍ ፍፁም ቁስ አካል የለም፡፡ በዚህ የብርሃንና የቁስ አካል መስተጋብር ጠባይ ላይ በመመሥረት ነው እንግዲህ ይህ መሰውር የተባለው ግኝት የተገኘው፡፡"

"ሚስተር ዶናልድ የምትለኝ ግኝት የኛን ሀገር አፈ ታርኮች የሚመስል መሳጭ ታሪክ ቢሆንም አሁንም ለማመን

ያስቸግረኛል። ለምሳሌ በቀድሞ የጎንደር ነገሥታት ዘመን አንድ የታወቀ አስማተኛ ነበር ይባላል። ስሙን ካልዘነጋሁት ሊቁ እንክንድር ይባላል። እስክንድር የንጉሡ ቅርብ ወዳጅና ቤተኛ ሆኖ ከቤተ መንግሥት የማይጠፋ ባለሟል ነበር። በዚሁ ወቅት የንጉሡ ሚስት በእስክንድር ፍቅር ትወድቃለች። እስክንድርም እንደዚያው። እሷን ለማየት ዘወትር ወደ ቤተ መንግሥት ሲመላለስ በፍቅር መንደዳቸው እንዳይታወቅ እፀ መሰውሩን ተቀብቶ ወደ ቤተ መንግሥት ሲገባ ማንም አያየውም ነበር ይባላል። እንዲያውም ወደ ንጉሡ ማዕድ ከንግሥቲቱ ጎን ተቀምጦ እጁን ይሰድ እንደነበር የታወቀው ማንም በማይቆርስበት በኩል ያለው የመሶቡ እንጀራ አልቆ የመሶቡ ቂጥ ሲጋለጥ ነው ይባላል። በኋላ ከንግሥቲቷ ጋር በስውር የሚያደርገውን ብቻውን በግላጭ ለማድረግ ይሺት ይሰደዳል። የንጉሡ ወታደሮች እየተከታተሉ ሲያሳድዱት ጣና ሐይቅ ውስጥ ወደምትገኝ ደሴት ይገባል። የንጉሡ ወታደሮች ወደ ደሴቲቷ ቀርበው ሲከቡትም ደሴቲቷን ይሰውራታል። እስከ ዛሬ ድረስ እስክንድር የሠወራት ደሴት ጣና ሐይቅ ውስጥ እንደ ቤርሙዳ ተሰውራ ትኖራለች ይባላል። እንዲህ አይነት አፈ ታሪኮች ባገራችን ሞልተዋል።"

"ይሆናል። ምክንያቱም አለመታየት የሰው ልጅ የዘወትር ምኞት ነው። ለዚህም ግማሹ ኮፍያን ግማሹ ጨለማን ተገን

ለማድረግ ይሞክራል፡፡" ዶናልድ ብሎ ሌብሉን ተጎንጭቶ ሊቀጥል ሲል ኒቆዲሞስ አቋረጠው፡፡

"ታዲያ የኛው ኢንጂነር የቀን ጨለማ በቅባት መልኩ ፈጠረ ነው የምትለኝ?"

"ከተፈጠረማ ቆይቷል፡፡ ዕንስ ሀሳቡ በመስፋፋቱ በተለያዩ አካባቢዎች ጭምጭምታዎች እየተሰሙ ነው፡፡ እንዳልከው ጨለማን በቅባት መልኩ የፈጠረው ሻጊዝ ከዚህ በፊት ከተደረጉ ሙከራዎች በላቀ ሁኔታ ነው፡፡"

"ለመሆኑ ጥቅሙ ምንድን ነው?" ኒቆዲሞስ ፈጠራውን በማጣጣል አይነት ትከሻውን ወደ ላይ ናጠ፡፡

"ጥቅሙማ የትየለሌ ነው፡፡ ለምሳሌ የኔ ሀገር አሜሪካ ለስለላ ተቋሟ በአመት በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ታወጣለች፡፡ በየሀገሩ መረጃ ለሚሸጡልን ቅጥረኞች አያሌ ዶላሮችን ታፈሳለች፡፡ ይህም ሆኖ ብዙ ኦፕሬሽኖች በፀረ ስለላ ተቋማት ይከሽፋሉ፡፡ ነገር ግን ይህ እፀ መሰውር ቢኖር ኖሮ በጠራራ ፀሐይ ጨለማን በቅባት መልኩ የተቀባ ወኪላችን የትኛውንም ምስጢር ይዞ መሰስ ቢል ማንም አያየውም ነበር፡፡"

"ለመሆኑ ሳይንቲስት ሻጊዝ ይህን እፀ መሰውር በጥቁሩ ሳጥን ውስጥ እንደያዘ እርግጠኞች ናችሁ?"

"መቶ በመቶ፡፡" አለ ዶናልድ ፈርጠም ብሎ፡፡

"እሱ ብቻ አይደለም በጥቁሩ ሳጥን ውስጥ ያለው። ሌሎች እሁን እስም ያልደረሰባቸው ቀመሮች ጭምር እንዳሉ ይታመናል።"

"ይህ እኮ ታዲዮ ለናንተ አደገኛ ነው። ይህን ምስጢረ መሠውር ለጠላቶቻችሁ ሰላዮች ቢሸጥ እኮ ኀይታ ሐውስን እንደ ማዕድ ቤታቸው ሸርጉድ ቢሉበት አታይዋችሁም። የሚሳኤል ማስወንጨፊያችሁንና ሳተላይቶቻችሁን ሁሉ አመድ ቢያረጓቸው አይታይዋችሁም። በጥቅሉ መኖር የምትችሉት የጨለማውን ቅባት በተቀቡት ሰዎች ቸርነት ብቻ መሆኑ ነው። ያንት ያለህ!..." ኒቆዲሞስ ዓይኖቹን ጎልጉሎ ዶናልድን ተመለከተው። "የአሜሪካ ጠላቶች ደግሞ ለናንተ ምህረት የሚያደርጉበት አንዳችም ምክንያት የላቸውም።" ካለ በኋላ ኒቆዲሞስ ጥቂት አሰብ አድርጎ "ስለዚህ የጠየኩት ክፍያ በቂ አይደለም ማለት ነው። ይህን ሰውዬ እስከ ጥቁሩ ሳጥን ይገፍ ካስረከብኩ የጠየኩትን እጥፍ እፈልጋለሁ። ይህን ታላቅ ኦፕሬሽን ለማካሄድም በቅድሚያ ሶስት ሚሊየን ዶላር ከዋናው ክፍያ የማይቀነስ እፈልጋለሁ። በነገራችን ላይ ይህንን ታላቅ ኦፕሬሽን 'ዘመቻ እፀ መሰውር' ስል ሰይሜዋለሁ።" ኒቆዲሞስ ይህን ብሎ ሲያበቃ ዶናልድ ለረጅም ደቂቃዎች አሸካካ።

"ሚስተር ኒቆዲሞስ... ስማኝ። ይህን ሳይንቲስት እኮ እኛ ብቻ አይደለም የምንፈልገው። እናንተም አድናችሁ

መያዝ ያለባችሁ አደገኛ ሰው ነው። የመሠረተው ድርጅት እኮ የእናንተን መንግሥት ከሥሩ መንግሎ ለመጣል የሚታገል ድርጅት እንደሆነ አሳምረን እናውቃለን። ይህ የዘመናት ህልሙ ነው። እኛ ደግሞ እንደምታውቀው የሚያዋጣንን ከመምረጥ ወደ ኋላ አንልም።"

"ማለት። ይህን ሽምቅ ተዋጊ ቡድን እንደግፋለን ብለህ እያስፈራራኸኝ ነው?... ይህ አሸባሪን ከመደገፍ በምን ይለያል? ዴርቶጋዳ እኮ እኛ በድብቅ አፍነን የያዝነው አሸባሪ ቡድን ነው።"

"ሚስተር ኒቆዲሞስ... ያም ሆነ ይህ... ይህ ሳይንቲስት የጋራ ጉዳያችን ነው። ክፍያውን በተመለከተ ለመስማማት የምንችል ይመስለኛል። ሆኖም ጊዜ ሳንፈጅ ኦፕሬሽኑን ማጠናቀቅ እንፈልጋለን።" በማለት ዶናልድ ለመለሳለስ ሞከረ።

"ስለ ኦፕሬሽኑ አትጠራጠር። እንደፍልፈል ቆፍሮ ከገባበት ገደል ቆፍረው ለማውጣት ጥፍሮቻቸውን ያሾሉ ቀያይ ቀበሮዎችን በበቂ ሁኔታ አሰልጥነናል።" አለና ኒቆዲሞስ ከግድግዳው ላይ የተሰቀለውን ሰፊ ስክሪን አበራው። በመቀጠልም "ቀያይ ቀበሮዎች" ተብለው የተሰየሙትንና ስማቸውን የሚመስል መለዮ የለበሱ ኮማንዶዎች ሲሰለጥኑ የሚታዩበትን ፊልም ጋበዘው።

# ፲፩

## አስቴጥስ በረሃ፥ ግብፅ

ዴር33 በጣና ሓይቅ ላይ እንደ ጆልባ እየተንሳፈፈች ስታኮበኩብ ከቆየች በኋላ ከኋላና ከፊት ልባስ አካሏ ወጥቶ እንደ ሽፈናት ክንፏን ከጎንና ከጎኗ አውጥታ ዘረጋችና ፍጥነቷን ጨመረች። የስሜኑን አቅጣጫ እንደ ያዘችም ወደ ሰማይ ወጥታ መክነፍ ጀመረች። እንደ ሸብሸቦ የተጨባበጠውን የኢትዮጵያን መሬት ቁልቁል እያየች ከጨረሰች በኋላ ጥንታዊውን የኑቢያን ምድር እየገረመመች የሱዳንን ልሳነ ምድር ጨርሳ የአባይን ሸለቆ በመከተል የግብፅን በረሃ ተያያዘችው።

የግብፅን ምድር ለሁለት ሰንጥቆ የሚያልፈው የአባይ ወንዝ በስተግራ ምዕራባዊውን በረሃ በስተቀኝ ደግሞ ምስራቃዊውን በረሃ እያረሰረሰ ነፍስ ዘርቶበት

ያልባፋል። የግብፅ ታላላቅም ሆኑ ታናናሽ ከተሞች የተመሠረቱት ይህንኑ ወንዝ ተከትለው ነው።

ሚራኘር የግብፅን ምድር ቁልቁል እየተመለከተ ከጥንታዊቷ ምስር እስከ አዲሷ ግብፅ ድረስ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየውን ካርታ ተርትሮ የአስቂጥስ በረሃ የሚገኝበትን አቅጣጫ ተመለከተ።

የአስቂጥስን በረሃ ካርታው ላይ ከአባይ ወንዝ በስተቀኝ በኩል ከሚገኘው ምስራቃዊው በረሃ ውስጥ ካገኘ በኋላ በቀይ ማርከር ከበበውና እንደገና ቁልቁል የግብፅን ምድር መመልከት ጀመረ። በዓይነ ህሊናው የሚያልፋበት ምድር ጥንታዊ ታሪክ ይሳልበት ጀመር።

ጥንታዊቷ ምስር አርነት ከመውጣቷ በፊት አንዷ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር እንደ ነበረችና የጥንታዊ ስልጣኔዋ አሻራ የሆኑት ፒራሚዶቿን ያሳነፁት አሥራ ሁለት ፈርኦኖችም ኢትዮጵያውን እንደነበሩ ያነበባቸው ጥናቶች በቀለም እየተኳሉ ከአእምሮው ተሳሉ። ይህ ሁሉ ታሪክ በቀለም በመሳል በፈደል በመኳል ቀርቶ

የዛሬዋ ኢትዮጵያ አይጥ እንደበላው ቆዳ ተቆርጥሩ ተቆርጥፉ ከማለቷ የተነሳ በብዙ ኪሎ ሜትሮች ከኋላው እንደቀረች ያሰበው ከናስር ሓይቅ አለፍ ብሎ በተንጣለለው የአስዋን ግድብ ላይ ሲያልፉ ነበር። በበርሃው መሃል የሚጥመለመለውን የአባይን ወንዝ ተከትለው ለሰዓታት ሲበሩ ከቆዩ በኋላ ወደ ካይሮ ከተማ የሚጥመለመለውን ወንዝ ወደ ግራ ትተው ጭው ያለውን የምስራቁን በረሃ ተያያዙት።

"ተመልከት ሚራዥ!" አለው ጌራ ቁልቁል እያመለከተው። "ከታች በረሃው መሃል የምታየው ከተማ የግብፅ ምስጢራዊ የጦር ሰፈር ነው። የተራቀቁ ሚሳኤሎች ለመወንጨፍ የሚዘጋጁበት የጦር ሰፈር። ዶር33 ከራዳራቸው እይታ ውጭ በመሆንዋ እንጂ ይህኔ ያየር ክልላቸውን ጥሰን ስንገባ ከመቅፅበት እንደ ወፍ ነበር የሚያወርዱን" አለው። "ግብፅ... አራት መቶ ሰባ ሺህ መደበኛና አንድ ሚሊዩን ተጠባባቂ ኃይል ያላት በአፍሪካ ወደር የሌለው የሚባል ጦር ያላት ሀገር ናት። ሚራዥ2000 ከተባለው ፈረንሳይ ሠራሽ የጦር ሚግ በተጨማሪ ሌሎች አሜሪካ፣ ሩሲያና ቻይና ሥራት በሆኑ ተዋጊ ጀቶች የተደራጀ የአየር ኃይል አላት።

ከዚህም በተጨማሪ የሚሳኤል አረሮች ማስወንጨፊያ የተሸከሙ መርከቦች የታጠቀ ጠንካራ የባህር ኃይል አላት፡፡ ኢትዮጵያ አባይን መገደብ ከጀመረች ወዲህ የጦር ኃይሏን በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት ዘመን ያለፈባቸውን ሩሲያና ጀርመን ሥራት የጦር መሣሪያዎቿን በዘመናዊ መሣሪያዎች በመተካት ላይ ናት፡፡ ውስጣዊ የፓለቲካ አለመረጋጋት ባይገጥማት ኖሮ በኢትዮጵያ ላይ ወታደራዊ ጥቃት ከመሠንዘር ወደ ኋላ አትልም ነበር፡፡"

"ጥቃት የመሠንዘር ፍላጎት እንዳላት በምን እርግጠኛ መሆን ይቻላል?" ሚራዥ ካርታውን እየጠቀለለ ወደ ውይይቱ ገባ፡፡

"በእርግጥ ግብፅ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ታሪካዊና ፓለቲካዊ ሁኔታ በጥልቀት ለሚከታተል ሰው ይህን መገመት አያዳግትም፡፡ ግብፅ ከጥንትም ጀምሮ ኢትዮጵያን ከማዳከም ተግባሯ ወደ ኋላ ብላ አታውቅም፡፡ አሥራ አንድ ጊዜ ወረራ ፈፅማለች፡፡ ከመጀመሪያ ጊዜ በኤርትራ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያነሳች ሀገር ናት፡፡ ግብፅ ይህን ጥያቄ እስከታነሳ ድረስ አንድም ኤርትራዊ ኤርትራ የምትባል ሀገር ትፈጠራለች የሚል

ግምት አልነበረውም፡፡ ግብፅ ኢትዮጵያን የማዳከም ደባዋን በማጠናከር ጅብሃ የሚባል ገንጣይ ቡድን አቋቁማ የዛሬውን ሻዕቢያ ወልዳለች፡፡ እንደተመኘችውም ኢትዮጵያ ተገንጣጥላለች፡፡ የግብፅን የባህር ኃይል የሚቋቋም የባህር ኃይል ቀርቶ ኢትዮጵያ የባህር በር እንኳ የላትም፡፡ የኢትዮጵያ የባህር ኃይል መለዮውን ለድልዳል አርጎ የባዕዳን መርከቦች ዕቃ አውራጅና ስቃይ ኖሯል፡፡" አለች ሜሮዳ ቁልቁል ለጥ ባለው በረሃ ላይ የተቋቋመውን የጦር ሰፈር እያለፉ እያለ፡፡

"እና ግብፅ ወታደራዊ ትንኮሳ ታደርጋለች ብላችሁ ታስባላችሁ?" ዣንጊዳ ዝም ብሎ ቆይቶ ከወሬው ለመሳተፍ ያህል ጠየቀ፡፡

"ግብፅ ሰላዮቿን ወደ ኢትዮጵያ አሥርጋ በማስገባት ላይ እንደሆነች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ባሁኑ ሰዓት ከኢትዮጵያ በስተቀር ሌላ ለጦርነት የሚያዘጋጃት ሀገር የለም፡፡ ከእስራኤል ጋር የነበራት ሰጣ ገባ ከስድስት ቀኑ ጦርነት በኋላ ተቀዛቅዟል፡፡ እንዲያውም እስራኤል የግብፅ ወዳጅ ሆናለች፡፡ ይህ ሁሉ ሽርጉድ መቼም ለሌላ ለማንም አይሆንም፡፡" ሜሮዳ ጌራን ዝቅ ብላ እንዲበር መፈለጓን ነገረችው፡፡

"ባሁኑ ጊዜ ያለውን የኢትዮጵያ ሁኔታ ደግሞ እንደምውቀው ነው። ዙሪያዋን በጠላት የታጠረች ሀገር ናት። አዲስ ግንጥል ሀገር ደቡብ ሱዳን ሳትቀር ከግብፅ ጋር ወታደራዊ ስምምነት አድርጋለች። ኢህአዴግ መራሹ የኢትዮጵያ መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀባይነት የለውም። ሠራዊቱም ቢሆን በሀገሩ ሳይሆን በገገርው ፓርቲ ፍቅር እንዲምድቅ በካድሬ ሲሰበክ ይውላል። ኢትዮጵያ ተፈጥሮ ካደላት ተራሮቿ በቀር በዚህ ሰዓት ሁነኛ ደጀን አላት ብሎ ማሰብ ያዳግታል። ለእግረኛም ሆነ ለአየር ጥቃት የማይመቹት ተራሮቿና ፈጣሪ ይጠብቃት ብሎ ማለፍ ይሻላል።" ጌራ ዶር33ን በአስቴጥስ በረሃ ላይ ዝቅ አድርጎ ማብረሩን ቀጠለ። ጭው ያለ አሸዋ ለብሶ የተኛ በርሃ። እንዳች ፍጡር ዝር የማይልበት ቁልፍጥፍጥ ያለ አሸዋ ያጠለቀው ምድረ በዳ። ሚራዥና ካርታውን መሀ እንደገና በመተርተር በአስቴጥስ በረሃ ውስጥ የሚገኘውን የእንጦንስ ገዳም የሚገኝበትን ሥፍራ ፈልገና ምልክት አደረገበት። ከእንጦንስ ገዳም ለመድረስ ሁለት ኪሎ ሜትር ገደማ ሲቀራቸው ዶር33ን በረሃው ውስጥ አሳረፏት።

በእቅዱ መሠረት ሚራዥርና ዣንጊዳ የተዘጋጀላቸውን የግብፅ በረሃ ኮፕቲክ መነኩሳት የሚለብሱትን አይነት ጥቁር ቀሚስና መጎናፀፊያ ለብሰው ወረዱ። ነጠላ ጫማ ከተጫሙ በኋላም የግብፅ ኮፕቲክ የሚይዙትን ዓይነት ምርኩዝ ያዙና ጌራንና ሚሮዳን ተሰናብተዋቸው ጉዟቸውን ከመቀጠላቸው በፊት፣ ዓይኖቻቸው ውስጥ በሽፋል መልክ የገባላቸው ካሜራ መሥራቱንና ጆሮአቸው ውስጥ የተተከለላቸው ንዑስ የድምፅ መገናኛ መሥራቱም ተረጋገጠ።

ከዶር33 እንደወረዱ የሚገፈትር ከባድ ነፋስ ወደ ፊት አዳፋቸው። ሚራዥር ቀና ብሎ የጠራውን ሰማይ ተመለከተ። ክቧ ጨረቃ ከብር የተሠራ ሰሀን መስላለች።

"ጨረቃዋን ጋብዤችኋላሁ።" ሲል ተናገረ።

"እኛ ደግሞ አልፋን እንድትጋብዘን ነው የምፈልገው።" አለ የጌራ ድምፅ ከዶር33። እግረ መንገዱን አሁንም የድምፅና የምስል መቅረጫዎቹ እንደሚሰሩ ለማረጋገጥ ነበር።

# ፲፪

## ቪላ ደ ሌይቫ፥ ኮሎምቢያ

ዶን ቦናኖ ከቪላ ደ ሌይቫ መንደር ወጣ ብሎ በሚገኘው ግቢው ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሲጠባበቀው የነበረው ጥቁር እንግዳው መድረሱን ማመን አቅቶታል። ይህንን እንግዳ የሚፈልገው ኢትዮጵያ ውስጥ በተንጣለለው ታላቁ ሐይቅ በሆዱ የቋጠረውን የወርቅ ሽል አገላግሎ ለመታቀፍ ብቻ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ እግረ መንገዱን የዱሮ ካፖ ዲካፒውን ደም ለመመለስም እቅድ አለው። የዶን ሞርሞርዲና ደም በከንቱ ፈሶ መቅረቱ ሁልጊዜም እንዳቃጠለው ይኖራል።

"ስመሆኑ ያ ባሪያ በህይወት ላለመኖሩ ማረጋገጫ ተገኝቷል?" ሲል የዲምላን ገጽታ በዓይነ ህሊናው እየተመለከተ ጠየቀ።

"በእርግጥ አስከሬኑ ተገኝቶ አልተቀበረም። ነገር ግን በታላቁ ወንዝ በአባይ ላይ በተሠራው ጥንታዊ ድልድይ ላይ አንድ ሚራኘር ከሚባል የአማፂው ቡድን አባል ጋር ተናንቆ እንደተገደለ ይታወቃል። የዲምላን መሞት የሰማነው

ዞግይተን ነው፡፡ ባለፈው በዚሁ አማፂ ቡድን የተገደሉት ሁለት ሰርጎ ገብ አባላቶቻችን ናቸው የዲምላን መገደልና መርከቡ የሰጠመበትን ካርታም በሚሬኝ እጅ እንደሚገኝ ያሳወቁን፡፡" ታዲምስ ይህን ብሎ ሳያበቃ ቦናኖ እጁን በማወናጨፍ አቋረጠው፡፡

"በፍፁም አላምንም፡፡ ያ ባሪያ እንዲህ በቀላሉ ይሞታል የሚል እምነት የለኝም፡፡ ዲምላን የኔን ያህል አታውቁትም፡፡ እኔና እሱ በዶን ሞርሞርዲኖ ቤት ውስጥ አብረን ለብዙ ዘመን ሠርተናል፡፡ እያንዳንዱ ህዋሱ በተንኮል የተሞላ እርጉም ሰው ነበር፡፡ አደገኛ ነፍሰ ገዳይ ከመሆኑ በተጨማሪ በቂላቂል ገፅታው እስስታዊ ባህሪውን ሸፋፍኖ የሚኖር አውሬ ነው፡፡ በአንድ ሀኪም ቡጢ ይሞታል ብላችሁ ገምታችሁ ከሆነ ተሳስታችኋል፡፡ ይህኔ የሞተ መስሎ አሞኝቷቸው እንደ እባብ አፈር ልሶ ተነስቶ ይሆናል፡፡"

"በሰርጎ ገብ አባላቶቻችን መረጃ መሠረት የሚሬኘ ፍቅረኛ የሆነችው ሲጳራ ግንባሩ ላይ በጥይት እንደነደለችው ተነግሮናል፡፡"

"ባይኔ ያላየሁትን ነገር ለማመን ብቸገርም ዲምላ ይሞታል ብዬ ማመን ግን አይቻለኝም፡፡ ዲምላ እንደተገደለና የአባይ ወንዝ እንደ ግንድ እያንሳበጠ እንደወሰደው በተደጋጋሚ ነግራችሁኛል፡፡ ሆኖም ቢሞት ኖሮ የአባይ ዳር ገበሬዎች አስከሬኑን አግኝተው ለፖሊስ ይነግሩ ነበር፡፡ ይህ

ባልሆነበት ደረጃ ዲምላን ሳይቀብሩ ሞቷል ብሎ ማመን ቂልነት ነው።"

"ሞቶም አልሞቶም መርከቡ የሰጠመበት ካርታ በእጁ አይገኝም። ስለዚህ የዲምላ መኖርና አለመኖር ምንም ፋይዳ የለውም።"

"የዶን ሞርሞርዲኖን ኤክስካቫተር ዶዘር የት እንዳስቀመጠው አይታወቅማ! ልክ እንደ መርከቡ እሱን ፍለጋም ልንከራተት ነው?"

"ኤክስካቫተር ዶዘር ...?"

"ለምን እስከ ዛሬ ይህን ለማሰብ አልቻላችሁም?... አሁኑኑ ወደ አዲስ አበባ ደውልና ኒቆዲሞስ የዲምላን ፋይል ፈልጎ ፎቶውን አባዝቶ እንዲያሰራጭ ንገረው!... ነገር ግን ዲምላ የሚፈለግበት ምክንያት በነፍስ ግድያ እንጂ ኤክስካቫተር ዶዘር በመደበቁ ምክንያት እንዳልሆነ ከኒቆዲሞስ በቀር ማንም ማወቅ የለበትም! በል ፍጠን!" ዶን ቦናኖ አንባረቀ።

# ፲፫

## አስቂጥስ በረሃ ÷ ግብፅ

ሚራኹና ዣንጊዳ ጭው ያለውን በረሃ ተያይዘውታል። ከኋላቸው የሚነፍሰው ኃይለኛ ነፋስ የለበሱትን መጐናፀፊያና ቀሚስ ከፊታቸው ያስቀድመዋል። ከጫማቸው የሚነሳው አሸዋ ከፊት ለፊታቸው እየቀደመ ዓይኖቻቸውን ይገርፋል።

ሚራኹ ሲር ሲር የሚለውን የቶፋስ ፉጨት እያዳመጠ ሲጓዝ ከቆዩ በኋላ ወደ ኋላው ዞሮ ዱካቸውን ተመለከተ። ኅበዝ ሰዓሊ በሸራ ላይ የቀለመው ይመስል ልዩ ኪናዊ ስሜት ይፈጥራል።

"ዱካችንን ዞረህ እየውማ ዣንጊዳ። ጥንት አባቶቻችን ወደዚህ ምድር ሲመጡ ያሳረፉትን ይመስላል።"

"ለእኔ ግን እንኳን የእነሱን የፈረሶቻቸውን እንኳ አልመሰለህ ብሎኛል።" አለ ዣንጊዳ ዞር ብሎ ዱካቸውን አይቶ ጉዞውን እየቀጠለ።

"ዣንጊዳ... በዚህ ነፋስ ሹክሹክታ የጥንቷ ኢትዮጵያና የግብፅ አማልዕክት እስከመሆን የደረሱት መሪዎቿ በጆሮዬ

የሚያናግሩኝ ይመስለኛል። እየቃዠሁ ይሆን? ፀሐዩ አምባከ የሚባለው አሞንሬ የቶ ቅርፅ ያለውን ዘንጉን ይዞ የህይወት ቁልፍ መሆኑን የሚነግረኝ ይመስለኛል። በአሞንሬ የፀሐዩ ቤተ መቅደስ ውስጥ ታላቁ ካህን ቆሞ ከራምሴስ እስከ ቱትሞሲስ፣ ከአክሱማይ እስከ ቲርሐቅ፣ ከፒያንኪ እስከ ሻባከ በግብፅ ላይ የነገሡ የጥንት ኢትያጵያውያን ነገሥታቶችን ገድል የሚተርክልኝ መሰለኝ። እየቃዠሁ ይሆን? ወይስ እንደ የበረሃ በሽታ ያዘኝ? ሮሜርና ሄሮዱተስ ስለጥንት ኢትያጵያውያን ጠባይና መልክ የተቀኙት ቅኔ በዚህ ነፋስ ፉጨት ታጅቦ በጆሮዬ እየተንቆረቆረ ነው። 'ኢትዮጵያውያን መልካቸው ያማረ፣ ቁመናቸው የሰመረ፣ እንግዳ ተቀባዮች፣ በአፋቸው ሐሰት የማይገባ፣ አርጅተው የሚሞቱ፣ አማልክት የሚያፈቅሯቸው፣ በማንም ተገዝተው የማያውቁ' ተብለው ስማቸው በደማቅ ቀለም በፓፒረስ ላይ የቀለመላቸው ኢትዮጵያውያን ዛሬ የት ደረሱ? 'በአፋቸው ሐሰት የማይገባ' የተባሉት ኢትዮጵያውያን ዛሬ በሥርቆት እና በውሸት አንቱ ለመባል በቅተዋል። 'አርጅተው የሚሞቱ' የተባሉት ኢትዮጵያውያን ዛሬ በሽታ ይቀጥፋቸዋል። 'በማንም ተገዝተው የማያውቁ' የተባሉት ኢትዮጵያውያን ዛሬ በባዕዳን ባህል ሸቀን ተወርሰዋል። ነቢያን የቆረቆሩት፣ አክሱምን የወቀሩት፣ ባለ መቶ በሩን የቴብን ከተማ ያበጁት፣

ኢትዮጵያውያን የት ደረሱ?" ሚራኸ፣ ዣንጊዳ ይነግረው ይመስል የዣንጊዳን እጅ ይዞ አስቁሞ ይለፈልፍ ጀመር፡፡

ዣንጊዳ፣ አልፎ ፈልፎ ሚራኸን እንዲህ እንደሚያደርገው ስለሚያውቅ በጥሞና ሲመለከተው ከቆዬ በኋላ፣

"በኤልቆሻዊው ናሆም የትንቢት መፅሐፍ ውስጥ የተፃፈውን አላነበብክም? ... ከመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ በቃሌ እስካጠናው ደጋግሜ ያነበብኩት ጥቅስ ነው፡፡ እንዲያውም በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለጠቀስከው አሞን-ራ ተፅፎ ያገኘሁት በዚህ ስለነነዌ የትንቢት ሸክም በሚናገር መፅሀፍ ብቻ ነው፡፡" ካለ በኋላ ከትንቢተ ናሆም በቃሉ የሚያውቃቸውን ንባቦች አልፎ አልፎ ያነበንብለት ጀመረ፡፡

"የኃያላኑ ጋሻ ቀልቶአል፣ ፅኑአንም ቀይ ልብስ ለብሰዋል፣... ነነዌ ግን ከድሮ ዘመን ጀምራ እንደተከማቸ ውኃ ነበረች፣ መዝገብዋ መጨረሻ የለውምና፣ የከበረውም የእቃዋ ሁሉ ብዛት አይቆጠርምና ብሩን በዝብዙ፤ ወርቁንም በዝብዙ... ባዶና ምድረ በዳም ሆናለች፤ ልብ ቀልጦአል፤ ጉልበቶችም ተብረክርከዋል፤ በወገብም ሁሉ ሕማም አለ፤ የሰዎችም ሁሉ ፊት ጠቁሮአል፡፡... አንበሳው ለልጆቹ የሚበቃውን ነጠቀ፣ ለእንስቶቹም ሰበረላቸው ዋሻውን በንጥቂያ፣ መደቡንም በቅሚያሞልቶታል፡፡"

"የፈጣሪ ያለህ! ዣንጊዳ... ይህን ያህል በቃልህ ታውቀዋለህ?"

"---ይህንን ስለነገዌ ሸክም የተነገረ ትንቢት ባለብኩ ቁጥር ሁልጊዜም ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እያዛመድኩ እብከነከናለሁ። የእኔ ነነዌ ኢትዮጵያም የሰወችዋ ፊት ጠቁሮአል። አንበሶችዋ የሚበቃቸውን ነጥቀው አላበቁም። ብርዋንም ወርቅዋንም ነጥቀው አልጠረቁም። ... ይልቁንስ ከትንቢቱ ናሆም ጥቂት ልጨምርልህ።"

"እባክህን..."

"...አሕዛብንም በግልሙትናዋ፣ ወገኖችንም በመተትዋ ሸጠች..."

"...የእኛ ነነዌም... እረኞችዋን ለአረብ ግመል ጥበቃ... ልጃገረጆችዋን ለባዕዳን የጭን እቃ ሸጣለች ቀጥል..."

"...ነነዌ ባድማ ሆናለች። የሚያለቅስላትስ ማነው? የሚያጽናናትስ ከወዴት እፈልጋለሁ?..."

"ልክ ነው ..."

"... በአንቺ ዘንድ ዘውድ የጫኑት እንደ አንበጣ፣ አለቆችሽም እንደሚንቀሳቀሱ ኩብኩባዎች ናቸው፤ ...በብርድ ቀን በቅጥር ውስጥ ይቀመጣሉ፤ ፀሐይም በወጣች ያኰበኩባሉ፤ ስፍራቸው በየት እንደሆን አይታወቅም..."

"ልክ ነህ ኘ'ንጊዳ... የእኛዎቹ ኩብኩባዎችም ሥፍራቸው የት እንደሆነ አይታወቅም።"

"... ለደም ከተማ ወዮላት። በሁለንተናዋ ሐሰትና ቅሚያ ሞልቶባታል፤ ንጥቂያ ከእርስዋ አያልቅም..."

"ስለ አሞን-ራ፣ የተጠቀሰውን ግን እስካሁን አላልክልኝም።"

"......አንቺ ነነዌ፣ በመስኖች መካከል ከተቀመጠችው÷ ውኃም በዙሪያዋ ከነበራት፣ ምሽግዋም ባሕር ከነበረ፣ ቅጥርዋም በባህር ውስጥ ከነበረ ከአሞን ከተማ ትበልጪለሽን? ኢትዮጵያና ግብፅ የማይቆጠር ኃይልዋ ነበሩ፤ ፉጥና ኑብያ ረዳቶችዋ ነበሩ።' ይላል። ይህቺ የአሞን ከተማ የተባለችው ቴብ... መፈራረስዋ በዚሁ መፅሀፍ ተጠቅሶአል። እርስዋ ግን ተማርካ ፈለሰች፤ ሕፃናትዋ በመንገድ ሁሉ ራስ ላይ ተፈጠፈጡ፤ በከበርቴዎችም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ፤ ታላላቆችዋም ሁሉ በሰንሰለት ታሰሩ። በማለት መፈራረሷ ተገልጧል። ሆኖም በዚህች ጥንታዊ ከተማ እስከአሁን ድረስ የአሞን-ራ የፀሐይ ቤተ መቅደስ ፍርስራሽ ይገኛል፤ በየአመቱም በብዙ ሰዎች ይጎበኛል። ቅድም በዶ.ር33 ስንበር ቁልቁል የአባይን ሸለቆ ስመለከት ይህንን እያሰብኩ ነበር።"

አለና፣ "የአሞን-ራ ከተማ ቴብ ስትፈርስ እንደሆነችው፣ የእኛም ሀገር የሚታይ ቅጥርዋ ፈራርሶ፣ ታላላቆቿ ታስረውና ተሰደው ባዶዋን ቀርታለች። በመከባበር

የሚታዎቁት ኢትዮጵያውያን አሁን እርስ በእርስ በመናናቅ የሚስተካከላቸው ጠፍቷል፡፡ ሚራኘርን ወደኋላ እንዲዞር ጎተተው፡፡

ሚራኘር ያየውን ማመን አቃተው፡፡ ከኋላቸው ያለው ሰማይ የደመና መአት ተጭኖበታል፡፡

"ካምሲን ነው ደመና?"

"የምን ደመና ነው ከምሲን ነው እንጂ! ወቅቱ እኮ ነው አታይም እንዴ?... ከደቡባዊ አረቢያ ፔኒንዝላ ተነስቶ እኮ ወደኛ እየገሰገሰ ነው፡፡ ከኋላችን የሚገፊትረን ሞቃት ነፋስ ለካ የከምሲኑ መሪ ነበር!... ስለዚህ አደገኛ አውሎ ነፋስ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶን ነበር ረሳኸው? ይህ ነፋስ አሸዋውን ተሸክሞ ከደረሰብን ይዞን የትም ተጉዞ ከአሸዋው ጋር ያዘንብንና እዛው ተቀብረን መቅረታችን ነው፡፡ ጥንት ናፖሊዮን ግብፅን ሲወር ካዘመተው ወታደር አብዛኛው በዚህ የአሸዋ ዝናብ ተቀብሮ በረሃ ውስጥ የቀረ ነው፡፡ በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት የጀርመን ወታደሮችን አሳር ያበላው ይህ አውሎ ነፋስ ጦርነቶችን በማቋረጥ ጠላትን ከጠላት ሰማይ ላይ አገናኝቶ እንደ ገለባ አንኳሎ ይቀብር ነበር፡፡"

"ታዲያ ለምን ቆመን እናየዋለን? ወደፊት እንሩጥ ወይስ ወደኋላ?" ሚራኘር ዣንጊዳን አዋከበው፡፡

"ወደፊት ነው እንጂ ወደ ገዳሙ ገብተን ካላመለጥነው ወደ ኋላ የት እንጠለላለን?"

"ዴርን33 ውስጥ ነዋ!"

"እሷንስ ይዟት እንደማይበር ምን ማረጋገጫ አለን? ቢሆንስ እሷን ጥለናት ብዙ ርቀት መጓዛችንን ረሳኸው? ከእርሷ ይልቅስ ገደሙ ሳይቀርብ ይቀራል?"

"ቁመን ከመቀበር እያመለጥን ብንሞት ይሻላል።"

ዣንጊዳና ሚራዥ ከኋላ እየተጥመለመለ የሚከተላቸውን አውሎ ነፋስ ለማምለጥ ወደፊት እግሬ አውጭኝ ይሉ ጀመር።

# 10

## አዲስ አበባ÷ኢትዮጵያ

ኒቆዲሞስ የዲምላን ፋይል በመፈለግ ቢሮውን ሲያመሰቃቅል ቢያድርም ሊያገኘው አልቻለም። 'አርቀው የቀበሩት ኮራስም ይደበቃል' በማለት ራሱን ከወቀሰ በኋላ በጠዋት ወደ ቤቱ በመገሥገሥ ቤቱ ውስጥ የሚገኝ የግል ቢሮውን ከፍቶ እንደገባ ሚስቱ የሌሊት ልብሷን እንደለበሰች ከተፍ አለችበት።

"አልበዛም?!" ስትል ተንጨረጨረች። "ስንተኛ ቀንህ እንደሆነ አውቀኸዋል? ሁሉም ነገር በልክ ቢሆን ምናለ? ንቀት ነው? ምንም አታመጣም ብለህ ነው?..."

ዝም ብሎ ቢሮውን ማተረማመሱን ቀጠለ። ወደ ግል ቢሮው ከእርሱ በቀር ማንም ስለማይገባ ሚስቱ ወደ ውስጥ ሳትዘልቅ በሩን ይዛ ነው የምትንጨረጨረው።

"አትቀባጥሪ!" ኒቆዲሞስ ፍሲጋውን አቁሞ ወደ ኋላዋ እንድትመለስ እጆቹን አወናጨፈባት።

"ጭራሽ ለማዬትም ተጠየፍከኝ በል ለውሽሞችህ ሰላምታ አቅርብልኝ!" ብላ ከንፈሯን አሽራምጣ እስክትመስል ያለ እንቅልፍ፡ ጭቅጭቅ በርበሬ መስለው ያደፉትን ዓይኖቹን እያንቦገቦገባት ነበር።

ኒቆዲሞስ የሰነድ መደርደሪያውን መንጋ እንደተቃናበት ከምር ናንዶ ጨርሶ ተስፋ በመቁረጥ በእግሩ መሬቱን ደለቀና ቢሮውን ዘግቶ ሳሎኑ መሃል ቆሞ ማሰላሰል ቀጠለ።

ጣራና ግድግዳው የዲምላን ሰነድ ይወልድ ይመስል ባይኑ ሲግጠው ከቆዬ በኋላ "አንቺ?!..." ሲል ባለቤቱን ተጣራ።

"አትሰሚም?!" ሳትመልስለት ስትቀር ወደመኝታ ክፍሏ ዘሎ ገባ።

"እየጠራሁሽ አይደለም እንዴ?!"

"ውሽሞችህን ጥራቸው እንጂ! እኔ ምን እሠራልሃለሁ።"

"የሚጠራ ይጥራሽ"

"በጠራኝና በተገላገልኩ!"

"ለመሆኑ የዛሬ ሁለት አመት አካባቢ የሰጠሁሽን ሰነዶች የት ነው ያስቀመጥሻቸው?!" ሲል ንዴቱን እየተቆጣጠረ ጠየቃት። እንደ ሌላው ጊዜ ቢሆን ግን አንቆ ይፈጠርቃት ነበር።

ካንቺ ጋር ግብግብ የምገጥምበት ጊዜ የለኝም" አለ በልቡ። 'ለሌላ ጊዜ አስተላልፌውና አሳይሻለሁ።'

"አንቺን እኮ ነው የማናግረው! የት ነው ያስቀመጥሽው?!"

መልስ አልሰጠችውም። ጣቶቹን አሹሎ ወደ አንገቷ ሥር ከተታቸው። ከእግር እስከራሷ ትንቀጠቀጥ ጀመር። ከጀመራት ለሳምንታት የሚያስተኛ ቁስል ሳይሰጣት አይለቃትም። ይህን አመሉን ስለምታውቅ እየተንዘፈዘፈች ተነሳች። አሁንም አንገቷ በኒቆዲሞስ ቾብ ውስጥ ነው። እንደሚታጨድ ገብስ ፍጥርቅ አርጎ ይዟታል። የአንገቷ ደም ሥሮች ተግተርትረው ይቆጠራሉ። ለጥቂት ደቂቃዎች ሲያጉረጠርጥባት ቆይቶ "ጊዜ የለኝም። እንዳ'ህያ መደብደቡን እንደሆን ለምደሽዋል። ፈጠን ብለሽ አምጫቸው።" በማለት ደነፋና አንድ ጥፊ አቅምሶ ማራት። ጥፊዋን እያጣጣመች ገባችና ቀይ የፋይል ሳጥን ይዛ ተመለሰች። ከሁለት አመታት በፊት የሰጣት ነበር።

ኒቆዲሞስ ከእጇ ላይ በፍጥነት መንጭቆ ሳሎኑ መሀል ላይ ወዳለው የምግብ ጠረጴዛ በፍጥነት አመራ። ወንበር ስቦ ተቀመጠና ቀዩን የፋይል ሳጥን ከፍቶ ሰነዶቹን ያተረማምስ ጀመር። ከጥቂት ፍለጋ በኋላ ፊቱ እንደ ኑጋት ሰማይ ሲፈካ ታወቀው። የዲምላ ፋይል ሳይነካካ ተቀምጦ እየጠበቀው

ነበር። ዝርዝር ጉዳዮችን መመልከት አልፈለገም። ሶስት ገፃች ያህል እንደገለበጠ የዲምላን ፎቶ አገኘው። ጥቁር፣ አስፈሪ፣ ፊቱ እንደ መፀው ማሳ የታረሰ አንድ ዓይኑ ጭራሽ ያልተፈጠረ ያህል ከገደሉ የጠፋ ፎቶ።

ኒቆዲሞስ በመረረ ጥላቻ ሲመለከተው ከቆዩ በኋላ የፊካ ፊቱ እንደገና ሲመሽ ታወቀው። ልቡ የሚረጨው ደም ወደ አሲድነት የተለወጠ መሰለው። ሃሞት የጠጣ ይመስል በአፉ የእሬት ኮምጣጤ የተሞላ መሰለው። መራራ ምራቁን በዲምላ ፎቶ ላይ ለቆጠበት። የዲምላ ፊት ሲጨማለቅ ወዲያው ከዚህ ፎቶ በቀር ሌላ እንደማያገኝ ተገንዝቦ በኩቱ እጅጌ ሞጅርጎ ጠረገውና ተነሳ።

“የትም አታመልጠኝም አንተ ኮሶ ፊት ባሪያ! የገባህበት ገብቼ አንቅሀለሁ።” እያለ ከፎቶ ጋር እየተሰዳደበ ሲወጣ ሚስቱ ቆማ እየተመለከተችው ነበር። ‘ለየለት!’ ብላ ኒቆዲሞስ እያበደ እንደሆነ በመገመት ጠረጴዛው ላይ በታትኖት የሄደውን ሰነድ በቅጥ በቅጡ ታረግ ጀመር።

# ፲፫

### እስቴፕስ በረሃ÷ግብፅ

ጌራና ሜሮዳ በዶር33 ውስጥ ተቀምጠው የሚራቸሮንና የዢሮንጊዳን ጉዞ በተገጠመው ስክሪን ሲመለከቱ ቆይተው የግል ወሬያቸውን ይዘዋል፡፡

"ቀጣይ እጣፈንታችን ምን ይመስልሃል ጌራ?" አለች ሜሮዳ ከግል ወሬያቸው እንደወጡ፡፡

"እኔ እንጃ!" አለ ጌራ በረጅሙ ተንፍሶ፡፡

"ውሃ ላይ እንደሚንሳፈፍ ኩበት እስከመቼ ያለ አቅጣጫ ስንኳዳ እንደምንኖር ሊገባኝ አልቻለም፡፡ ወይ የራሳችንን ህይወት አልመራን ወይ ለሀገራችን የተመኘነውን አላደረግን… ጭራሽ ለህልውናችን አስጊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ መውደቃችን ያሳዝናል፡፡ ከሚራቸር በቀር ተስፋ ያልቆረጠ ያለ አይመስለኝም፡፡"

"አንቺም ተስፋ ቆርጠሻል ማለት ነው?" ጌራ በድንጋጤ ክው ብሎ ጠየቃት፡፡

"አንተስ ብትሆን ተስፋ አልቆረጥኩም ልትል ነው? የበፊቱ ዕናትህ አሁን አብሮህ ያለ አይመስለኝም፡፡ ፈገግታህ የለም፡፡ ሳቅህ የለም፡፡"

"በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንኳን የምስቀው የማገጠው ከወዴት አመጣለሁ? እኔና ሀገሬ መቼ ፊገግ እንግደምንል ታውቂያለሽ?" አለ ጌራ በግድ ፊገግ ለማለት እየሞከረ።

"ድንጋዩ ዳቦ ሲሆን?" ሜሮዳ እጇን አወናጫፈችበት።

"ሀገሬ ፍቅር እንጂ ዳቦ አላጣችም። እኔም ብሆን የራሴን ከርስ መሞያ አጥቼ አይደለም። ጥሩ ሞያ ያለኝ ሰው ነኝ። ዶርቶጋዳ ውስጥ ያሉ አባላት በሙሉ የዳቦ ችግር የለባቸውም፤ ሁሉም የተለያዩ ሞያና ብቃት ያለው ነው። ሁላችንም የግል ህይዎታችንን ወደጎን ትተን ከእድሜአችን ቀንሰን፣ ከድሎታችን ቀንሰን፣ ከሳቃችን ቀንሰን የምንሰጣት ሀገራችን ዘላለም በእንብርክክ መዳኋን አቁማ ቀና ብላ እንድትራመድ ነው። አንድም ቀን አስቤው የማላውቀው ለሀገሬ የቀነስኩትን እድሜዬን፣ የቀነስኩትን ድሎቴን፣ የቀነስኩትን ሳቄን ነው። እውነቱን ልንገርሽ? እንደገና ብፈጠር እንኳ ሀገሬ እንደዚህ ሆና ካገኘኋት ይህንኑ እደግመዋለሁ።" ጌራ ሳይታወቀው ይደነፋ ጀመር።

"እንዴ?! ኧረ በቃ! ሁሁ... ስፈትንህ ነው ባክህ አውቀዋለሁ።"

"ሁለተኛ እንደዚህ አይነት ጥያቄ እንዳትጠይቂኝ። ይህ ድርጅት በፈተና ውስጥ ሳይታለፍ ፍትፍት አይገኝም። ይህ ድርጅት በፈተና ውስጥ ሳይታለፍ ፍትፍት አይገኝም።" 

በድል ተወጥቶ ህልሙን እንደሚያሳካ አንዳች ጥርጥር የለኝም፡፡ እንደገና እናንሰራራለን፡፡ የሻጊዝ ፊት ይቀየራል፤ ያነቺም እጅ ይቀጠላል፡፡ ብቻዬን ብቀር እንኳ ትግሌን አላቆምም፡፡ ትግሉ ሲጀመር በብዙ ሰዎች አይደለም የተጀመረው፡፡ በአንድ አባ ዠንበሩ በሚባሉ መነኩሴ እንደሆነ ላንቺ መንገር አያስፈልግም፡፡ የአባ ዠንበሩ ዕናት አጥንቴ ውስጥ ዘልቆ ይሰማኛል፡፡ በዛ ላይ…" ወደ እስክሪኑ ተመለከተ፡፡ ሚራዥና ዠንጊዳ ሲሮጡ ታዩት፡፡ "…በዛ ላይ አባ ዠንበሩ አልሞቱም፡፡ ከእርሳቸው የበለጠ ጀግና ተክተውልን አልፈዋል፡፡"

"የኔ ቆንጆ አንተም የእሱን ያህል ጀግና ነህ፡፡ እኔ ደግሞ በእሱ አንተን ተክቻለሁ፡፡" ከንፈሩን ግጥም አርጋ ሳመችው፡፡ ጌራ በዚሁ ቅጽበት ዓይኖቹን ወደ ስክሪኑ መለሰ፡፡ በእስክሪኑ ውስጥ በሚሮጡት ሚራዥና ዠንጊዳ ግራ ተጋባ፡፡ "ለምንድን ነው የሚሮጡት? የሆነ ነገር ተፈጥሮ መሆን አለበት፡፡" ይህን ብሎ ሳይጨርስ ኃይለኛ ነፋስ ዱር33 ከኋላ ወደፊት እንደ ቂቤ ናጣት፡፡ ቀጥሎም ከፊት ለፊታቸው እንደጉም የሚወናጨፍ አቧራ ተመለከቱ፡፡ ወደ ኋላቸው ሲዞሩ የዱር33 መስታውት የሚውጀመጀም አውሎ ነፋስ ጋበዛቸው፡፡

"ኮምሲን ነው!" ሜሮዳ ጮኸች፡፡ ጌራ የዱር33ን ሞተር ለማስነሳት ቁልፎቿን ይነካካ ጀመር፡፡

# ፲፮

## ቪላ ደ ሌይቫ፥ ኮሎምቢያ

ዶን ቦናኖ ሁልጊዜም ሲናደድ እንደሚያደርገው ሳሎኑ መሃል ሲንጎራደድ ከቆዬ በኋላ ጥርሱን እያንቀጫቀጨ ወደ ታዴዎስ ተመልሶ እስከ አፍንጫው አጎነበሰና፣ "ኮሎምቢያ የመጣሁት፣ የኢንካንና የአዜቴክን ጥንታዊ ስልጣኔ ለማጥናት አይደለም። ወደ ኢትዮጵያስ ለምን የምንዝ ይመስልሃል? ጥንታዊውን የኩሽ ስልጣኔ ለመመርመር?" ዶን ቦናኖ በንዴት ሲናገር ከንፈሩ ይሸራመጣል። "ንገረኝ እንጂ! ሉሲ ምናምን እያልኩ የጥንቱን ዝንጀሮ አጥንት ለመቆፈር?"

"አይደለም..." ታዴዎስ በቀስታ መለሰለት።

"የትም ሀገር የምሄደው ወርቅ ለመቆፈር ነው። ይገባሃል? ወርቅ! ወርቅ! ወርቅ! ወርቅ!..."

"ይገባኛል።" ታዴዎስ በለሆሳስ አንሾካሸከ።

"ምን ይገባሃል?! ቢገባህማ ያኔ ሞርሞርዲኖ ባንድ ባሪያ ተለብልቦ ሲሞት ይገባህ ነበር። አሁንም ቢሆን እኔ የምሄደው እንደሞርሞርዲኖ ለመጠበስ ሳይሆን... የሚገባውን አሮስቶ ለማድረግ ነው። እኔ ማነኝ?!.. ንገረኛ እኔ ማነኝ?!"

ዶን ቦናኖ እንደገና ሳሎኑን ሲዞር ቆይቶ ከታዴዎስ ፊት ለፊት ተቀመጠ።

"እየውልህ ታዶ... ያዘጋጀሁት እቅድ ይህን ይመስላል።" አለና ዶን ቦናኖ አንድ ወረቀት ከመሳቢያው አወጣና ወደ ታዴዎስ ፊት ገፋለት። በጣሊያንኛ የተዘጋጀ ፅሁፍ ነበር። ዓይኖቹን ወረቀቱ ላይ ቢያሽከረክርም አንዱን ቃል እንኳ ሊያውቀው አልቻለም። ቀና ብሎ ዶን ቦናኖን ሲመለከት ቱሶካኖውን ለኩሶ እየማገ ይመለከተው ነበር።

"ጣልያንኛ እኮ..."

"አታነብም አውቃለሁ። ይህኔ ጣልያንኛ ብታውቅ ኑሮ ስንት ምስጢር በገባህ።" አለውና የማገውን ቱሶካኖ ጭስ ሁለቴ ለቆ ወረቀቱን አነሳው። "ግዴለም እኔ እተረጉምልሃለሁ። አይዞህ ለዚህ ክፍያ አልጠይቅም።" ብሎ ፈገግ አለ። ያመለ ጥርሱ ከአፋር በረሃ የወጣ ጥንታዊ አጥንት ይመስላል።

"በዚህ እቅድ መሠረት፣ በመመሪያ ኤክስካቫተር ዶዘሩ ተፈልጎ እንዲገኝ ይደረጋል። ከዚህ በፊት ግን ያ ባሪያ ተይዞ ከተደበቀበት እንዲያወጣ ይደረጋል።"
"እሱ ካልተገኘስ?"

ታደምስ አቋረጠው። "ማለቴ ምናልባት ሞቶ ቢሆንስ?"

"አይሞትም! ዲምላ አይሞትም! እንኳንስ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲሲሊ ውስጥ እንኳ እሱን የሚገድል ጀግና አይገኝም።" ዶን ቦናኖ አፈጠጠበት።

"እሺ ቀጥል..."

"በሁለተኛ ደረጃ... ያ ሚራዥ የምትሉት አዞ ይያዝና መርከቡ ሰጥሞ የሚገኝበትን የሚያመለክተውን ካርታ እንዲተፋ ይደረጋል። ሶስተኛ ደረጃ የሚሆነው መርከቡን ማውጣት ነው። ጊዜው ሌሊት ስለሚሆን ታላላቅ ባውዛ የሚያበሩ ጀልባዎች ያስፈልጉናል። ከዚህ በተጨማሪ አራት ታላላቅ ጀልባዎች በሰጠመው መርከብ ውስጥ የሚገኘውን ወርቅ ጭነው ወደ ጎርጎራ ወደብ እንዲወስዱ ይደረጋል።"

"እነዚህ ጀልባዎች በኪራይ ወይስ..."

"ተዘጋጅተዋል። እዛው ጣና ውስጥ ይገኛሉ።"

"ማለት..."

"አንድ በኢንቨስትመንት ዘርፍ የተሰማራ የእኛ ሰው አስቀድሞ ይዟቸው ገብቷል። ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለስክ ያገኘሃል።"

"እሺ ወደ ጎርጎራ በጀልባ ከተጫኑ በኋላስ?"

“ከዛ በኋላ ቀላል ነው፡፡ ደቡብ ሱዳን ውስጥ በማዕድን ቁፋሮ የተሠማራ ድርጅት አለኝ፡፡ ወደ ደቡብ ሱዳን በዚህ ኢንቨስትመንቴ ብዙ ጊዜ በመመላለስ ብዙ ወዳጆች አፍርቻለሁ፡፡ የአዲሷ አገር ደቡብ ሱዳን ባለስልጣናት ወዳጆቼ ናቸው፡፡ ስለዚህ የድርጅቴ መኪኖች ወደ ጎርጎሬ የሚገቡበትን መንገድ ያዘጋጁልኛል፤ ይህንንም ተነጋግሬ ጨርሻለሁ፡፡

“ ከዛስ...”

“ከዛማ መኪኖቹ ወርቁን ወደ ደቡብ ሱዳን ያሻግሩልኛል፡፡ ደቡብ ሱዳን ከገባ በኋላ በግል አውሮኘላኔ እንዲጫን ይደረግና እዚህ ድረስ እንዲመጣ ይደረጋል፡፡ በቃ!...”

“የእኛ ድርሻስ?...”

“ተመልከት!” አለና ዶን ቦናኖ ግድግዳው የተሰቀለውን ስክሪን በርቀት መቆጣጠሪያው ከፈተለት፡፡ ታዴዎስ በስክሪኑ ላይ የተቸነከረውን ተንቀሳቃሽ ምስል ላይ አይኖቹን እንደሚስማር ተከለ፡፡

በእስክሪኑ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ምስል እጅግ የተዋበ መኖሪያ ግቢ ነበር፡፡ አፀዱ በልምላሜና በአበባ የደመቀ ነው፡፡ ውድ መኪና ቆሞበታል፡፡ ሰማያዊ ቀለም የተላበሰ መዋኛ

ገንዳ ለጥ ብሎበታል፡፡ የቤቱ ውስጣዊ ውበት የታዬዎስን አፍ አስከፈተው፡፡

"ይህ የምትመለከተው የተዋበ ግቢ አንተ እስክትገባበት የሚጠባበቅ ነው፡፡ የት እንደሚገኝ ታውቃለህ?"

ታዬዎስ ፊቱ በደስታ ፈክቶ ይህ ገነት የመሰለ ቤቱ የት እንደሚገኝ ለማወቅ ተጠባበቀ፡፡

"ቦነስ አይረስ!--- አርጀንቲና!" ዶን ቦናኖ ተንፈቀፈቀ፡፡ "ከዚህ ጥቂት የሚበልጠው ደግሞ ለኔቶ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ ኦፕሬሽን በኋላ የምትኖረውን ኑሮ መቼም ቢሆን እንዳትዘነጋ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የዛፍ ላይ እንቅልፍ ከሆነው ስልጣንህ ተላቀህ በገነት ውስጥ ለመኖር የቀረህ ጥቂት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ኦፕሬሽን በድል እስኪጠናቀቅ እንቅልፍ ከወሰደህ አህያ ነህ ማለት ነው፡፡"

"የምን እንቅልፍ ነው?"

"ቶሎ ቶሎ የያዛችሁትን ይዛችሁ ከኢትዮጵያ ብትወጡ ነው የሚሻላችሁ፡፡ ህዝቡ እንደሆነ አንቅሮ ተፍቷችኋል፡፡ የካድሬ ጭብጨባ ለጊዜው ቢደምቅም የጭንቅ ቀን ከመጣ ወደ ጥሬነት እንደሚቀየር እወቅ፡፡ ከሃያ አመታት በላይ ሰበካችሁ በአንድም ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ አልገባችሁም፡፡ ይልቅስ ከቀን ወደቀን ጥላቻው እየመረረ መጥቷል፡፡ የሠራችሁትን ሥህተት መቼም ቢሆን ይዘነጋዋል

ብላችሁ እንዲታሰቡ፡፡ በዘር ከፋፍላችሁታል ሀገሩን ገንጥላችሁበታል፡፡ ወደብ አሳጥታችሁታል፡፡ ዙሪያውን በጠላት አስከብባችሁታል፡፡ በቀረጥና በግብር አንገብግባችሁታል በስሙ ተመዕውታችሁበታል፡፡ በወሬና በጉራ አስልችታችሁታል፡፡ ዛሬ ከጫካ እንደወጣችሁ በጠበንጃ አስፈራርታችሁታል፡፡ አይወዳችሁም፡፡ ከቅቤ ባህር ብትነከሩት እንኳ ጥርሱን እንጂ ልቡን አይሰጣችሁም፡፡

"ዶን ቦናኖ... ለአሥራ ሰባት አመት ተዋግተን ያገኘነውን ሥልጣን እንዲሁ የምንለቅ ይመስልሃል? ብንፈቀርም ባንፈቀርም፣ የጓዶቻችን ደም በከንቱ ፈሶ አይቀርም፡፡"

"ሃሃሃ... ደሞ?!... ስማ ታዶ!... ግልፅና ጉልህ ስለሆነው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ቀርቶ ስንት ውስብስብ ፖለቲካዊ ጥልፍልፎችን እንደማውቅ ጠንቅቀህ ታውቃለህ፡፡ ማፍያ መሆኔን ዘነጋኸው?... በዛ ላይ ዶን ቦናኖ ነኝ፡፡ ...ስማኝ ልንገርህ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ሥልጣን ለመረከብ ብቁ የሆነ ፓርቲ ቢኖረው ኖሮ አንድ ቀን አያሳድራችሁም ነበር፡፡ ይልቁንስ ነገን መተንበይ ስለማይቻል ለክፉም ለደጉም መዘጋጀት ነው የሚያዋጣህ፡፡ አርጀንቲና ውስጥ መኖር ምኞትህ እንደነበር የነገርከኝን መሠረት በማድረግ ምራቅ የሚያስውጥ መኖሪያ አዘጋጅቼልሃለሁ፡፡ ለኒቆም ከዚህ ቀደም የእርሱን መኖሪያ ብቻ ሳይሆን ያንተንም አሳይቸው ምራቁን

ውጠ ተመልሷል። ይልቁንስ ሃያና ዓዝሀን ቀርቅበሀ ለመምጣት ተዘጋጅ።" ይን በናዋ ቲረቃኛውን ኼሁንኛ በሜሱ ውስጥ ታይምስን ተመለከተውና ፈገግ አለ። ታይምስም በምላሹ ፈገግ ብሎ ሲጋራውን ከለኮሰ በኋላ ሻይትን ጨፉና የተቀዳለትን መጠጥ ጨለጠው።

# 17

## አስቴሮፕስ በረሃ ፥ ግብፅ

የሚጥመሰመሰው ከምሲን ምላስ ያሬር33ን ከኋላቁ ይሞጨልፋል፤ አፉን ከፍቶ ሲውጣት እንደ ዳይኖሰር መንጋ ከኋላዋ ይጋልባል። ጌራ በአሳር ወደ ሰማይ ካወጣት በኋላ እስክሪኗን ለመመልከት ሞከረ። አካባቢው ድፍንፍን ስላለ ከአሸዋ ብናኝ በቀር በስክሪኑ ላይ የሚታይ ነገር የለም። ሁሉም ነገር ጨላልሟል። ደጎጎን።

ጌራ የያሬር33ን አገጭ ወደ ደቡባዊ ምስራቅ ለማዞር ሞከረ፤ ነገር ግን አልቻለም። ከምሲኑ የራሱን አቅጣጫ አስይዞ ወደ ምሥራቅ ይነዳው ጀምሯል። ከፊቱም ከኋላውም የሚታየው ነገር የለም።

“ኧረ ከአንዱ ተራራ ወይም ከአንዱ ፒራሚድ እንዳንላተም!” ብላ ሜሮዳ ጮኸች። “ከፍታ ጨምር! ከፍታ! ከፍታ!...”

“አልቻልኩም ሜሮዳ! ጭራሽ ወደታች እየደፈቀን ነው!”

ይባሱን የዶ.ር33 ፍጥነት ጨመረ።

"እነ ሚራዥ አይታዩህም?"

"ሳያዳፍኗቸው አልቀረም! አይታዩኝም! ስክሪኑ ላይ ከአውሎ ነፋስ በቀር የሚታይ ነገር የለም!"

ጌራ ከዶ.ር33 ጋር ግብግብ ገጥሞ አውሎ ነፋሱ እንዳይገለብጣትና በራሱ አቅጣጫ እንኳ እንድትጓዝ ለማድረግ ሞከረ። ነገር ግን ከምሲኑ እያየለ መጥቶ እንደ ባዶ ጀሪካን ሲያገለባብጣት ሆነ።

"ፍጥነት ጨምር!" አለች ሜሮዳ ፍጥነት መስጫ ቁልፉን ለመጫን እየቃጣች። "ከነፋሱ ፍጥነት ከበለጠ ግፊቱ ይቀንሳል።"

"ይልቁንስ ቀበቶሽን ጠበቅ አርጊ!... ከግብዕ ለምን ወጣን እንዳትይ ብቻ እንጂ ፍጥነቱን ልጨምረው ነው!" አለና ጌራ የዶ.ር33ን ፍጥነት መጨመሪያ ተጫነው። የነፋሱም ፍጥነት የዋዛ አልነበረም። ለሰዓታት እየተጥመለመለ ይዟቸው ሲጓዝ ከቆዩ በኋላ ከማያውቁት ቦታ ወስዶ ወደታች ደፈቃቸው። ዶ.ር33 ከምን ጋር እንደሆነ ተላትማ አረፈች። ከውጭ የሚታይ ነገር የለም። ከውስጥ ሆነው በላያቸው ላይ የሆነ ነገር እንደመርግ ሲጫናቸው ተሰማቸው።

# ፲፰

## አስቴጥስ በረሃ÷ ግብፅ

ሚራኘ ከሰመመኑ እየወጣ፣ ዓይኖቹን ለሶስተኛ ጊዜ በጥቂቱ ለመክፈት ታገለ። አልቻለም። የዓይኑ ቅንድብ የእንቅብ ያህል ከበደው። ከአካሉ አንዱንም ማንቀሳቀስ አልቻለም። በጆሮው ጭው ከሚል ስቅጣጭ ድምጽ በቀር የሚሰማው ነገር የለም። አፍንጫው በአሸዋ ጥቅጥቅ ብሏል። እንደምንም አፉን ከፍቶ ለመተንፈስ ሞከረ። ከከንፈሮቹ የአሸዋ ቅርፊት ሲወድቅ ታወቀው። ምላሱን ወደውጭ ቢልክ የአሸዋ ክምር ይዞ ተመለሰበት። እንትፍ የማለት አቅም እንኳ አልነበረውም። 'ፊንት ነቅዬ ነው' ሲል አሰበ። በትውስታው ማህደር ውስጥ አውሎ ነፋስ ሲያባርረው ትዝ አለው። ቀጥሎ መጉናፀፊያውን ነፋስ ቀምቶ ሲወስድበት። ቀጥሎ ቆቡን ሲያወልቀው። ቀጥሎ ቀሚሱን ሲገልበው። ከዛ በኋላ የሚያስታውሰው ነገር የለም። ዓይኖቹን በጥቂቱ ገልጦ አጨንቁሮ አየ። ጭው ያለ በረሃ ውስጥ እንደወደቀ ገመተ።

'የት ነኝ?' ራሱን ጠየቀ።

ዓይኖቹን መልሶ ከድኖ አሰበ፡፡ 'ክምሲኑ' ከሚል መልስ በቀር ወደ አእምሮው የመጣ ነገር የለም፡፡ 'ክምሲኑ' ከማላውቀው ቦታ ወስዶ ጥሎኛል፡፡ ግርንጊዳስ?... ሞቶ ይሆን?" እንደገና ዓይኖቹን በደንብ ከፍቶ አካባቢውን ለመቃኘት ሞከረ፡፡ አሸዋው ላይ የወደቁ ጥላዎች ያየ መሰለው፡፡ 'ተይዣለሁ' ሲል አሰበ፡፡ 'አብቅቶልኛል፡፡'

አንገቱን በግድ አቃንቶ የወደቀበትን ቃኘ፡፡ ቀሚስ ተበጫጭቋል፡፡ በአረብኛ ቋንቋ የሚነጋገሩ ሁለት ሰዎች ቆመው እየተመለከቱት ነበር፡፡ በአሸዋ የተደፈነ ጆሮውን አራግፎ ለመነሳት ከጀለ፡፡ ወገቡ እንደ ልጥ ተሰውሗል፡፡ ግርንጊዳ በአካባቢው እንደሱ ወድቆ እንደሆነ ለማዬት ቃኘ፡፡ ከእሱ በቀር የወደቀ አካል አይታየውም፡፡

በክንፈሩ ዙሪያ የተከመረውን አሸዋ ጉሽ ጠላ ፋት እንዳለ ሰው እንትፍ፡ እንትፍ፡ ብሎ በአረብኛ ቋንቋ የሚናገሩትን ሰዎች በእንግሊዝኛ ለማናገር ሞከረ፡፡

"ዱ ዩ ስፒክ ኢንግሊሽ?" ተንተባተበ፡፡ አልመለሱለትም፡፡ "ዩቶፒ?" ሲሉ መልሰው ጠየቁት፡፡ አንድ ነገር ትዝ አለው፡፡ ግብፅ ውስጥ "ኢትዮጵያዊ" ነኝ ብሎ መናገር እንደ እባብ መቀጥቀጥን እንደሚያስከትል የተነገረው ትዝ አለው፡፡ "እባብና ኢትዮጵያዊ ካገኘህ ቀድመህ

ኢትዮጵያዊውን ግደል" የሚባለው የግብፆች ብሂል ትዝ አለው።

"ሱዳኒ" ሲል መለሰ። ሆኖም ግን ይህ መልስ ዋጋ ቢስ እንደሆነ ወዲያው ተረዳ። 'አረብኛ የማይናገር ሱዳናዊ ነኝ' ህሊናውን መከረ።

ሚራጌና እንደምንም ተጣጥሮ ለመነሳት ተልፈሰፈሰ። አንደኛው ግብፃዊ እጁን አቀበለው። "አመሰግናለሁ።" እየተንገዳገደ ቆመ። ከቋንጃው ጅማት የተመዘዘ ይመስል እንደ ቄጠማ ተንቀጠቀጠ። የአሸዋ መአት ከላዩ ላይ ረገፈ።

ወደሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ሲመለከት የቤተክርስቲያን ጉልላት ተመለከተ።

"ሴንት አንቶኒ?" በጣቱ የቤተክርስቲያኑን ጉልላት እየጠቆመ ጠየቀ። የእንጦንስን ገዳም እንደጠየቀ የገባቸው ግብፃውያኑ ራሳቸውን በአዎንታ ነቀነቁ። አለባበሳቸው አመክሮ ውስጥ የሚገኙ የገዳሙ መነኮሳት እንደሆኑ ጠቆመው። በእንግሊዝኛ ቋንቋ መግባባት አለመቻላቸው ግን ስለ እንጦንስ ገዳም ኮፕቲክ መነኮሳት የሰማውን ሁሉ ገደል ከተተበት። ከዚህ ቀደም ስለዚህ ገዳም የሰማው እስከ ፒ. ኤች. ዲ ዲግሪ ድረስ የተማሩ መነኮሳት እንዳሉ ነበር። ምናልባት ሁሉም መነኮሳት ምሁራን ላይሆኑ ይችላሉ በሚል

ማምት የቤተክርስቲያኑን ጉልላት በእጁ እየጠቆመ ለመራመድ ተውተረተረ። አልተቻለውም። ከኋላው ተከተለችው።

"ገርንጌዳ!..." ሜሪሻር ጥቂት ከተራመደ በኋላ ተጣራ።

"ገርንጌዳ!..." ድምፁ በበረሃው ተዋጠ። "ገርንጌዳ..."

# ፲፱

## ቦሌ ÷ ኢትዮጵያ

ኒቆዲሞስ፣ ቦሌ አለማቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ ቀድሞ ብሎ ነበር የተገኘው። ቃዴምስ ኢየሱ የፍተሻ ጣጣውን ጨርሶ ሲወጣ ተመለከተው። ከእሱ መኪና ኋላ ያጃቢዎቹ ሁለት መኪናዎች ቆመዋል። ከፊቱ ደግሞ ሌላ አንድ የግል አጃቢው መኪና ይገኛል። ጥብቅ ወዳጅነቱን ለመግለጽ ያህል እንጂ፣ አየር ማረፊያ ድረስ መጥቶ በቃዴምስ ደረጃ ያለን ሰው ለመቀበል ክብሩ እንደማይፈቅድ ተገንዝቦታል። ምንም እንኳ ከሚኒስትር ማዕረጉ በሽረት ሳይሆን በሹመት ዘወር ቢደረግም አንድም ቀን ዝቅ እንዳለ ተሰምቶት አያውቅም።

"ወዳጄ ቃዴምስ እንኳን በደህና መጣህ" አለ ከመኪናው ወርዶ እየጨበጠው።

"እንኳን ደህና ቆየኸኝ ኒቆ" ከፊት ካለው መኪና ሁለት ባልደረቦች ዱብ ዱብ ብለው ወርደው የኋላ በሩን በክብር ከፍተው ቃዴምስን ጋበዙት።

በማዕረጉ ቅደም ተከተል፣ የኒቆዲሞስ መኪና ከፊቱ አንድ መሪ አስቀድሞ የታዲዎስ መኪና ደግሞ ከኒቆዲሞስ ኋላ ተከታትለው ተወነጨፉ።

ቦሌ የሚገኘው የጋሙስ ጽህፈት ቤት ወለል ብሎ ተከፍቶ ተከታትለው የመጡትን መኪኖች ከዋጠ በኋላ መልሶ ተዘጋ።

በኒቆዲሞስ የግል ቢሮ መሃል ለመሃል የተዘረጋው ጠረጴዛ እንደሁልዜው አሸብርቋል። በሐምራዊው የጠረጴዛ ልብስ ላይ ሳይቀዳባቸው ጠጡብኝ ጠጡብኝ የሚሉ ውድ ውድ ብርጭቆዎች ተሰልፈዋል። ታዴዎስና ኒቆዲሞስ ብቻቸውን በጠረጴዛው ዙሪያ ተሰይመዋል። የሚቀማመስ ነገር ቀርቧል። ከውስኪውም እየተጎነጩ ሁለቱም በየራስ አእምሮአቸው ውስጥ ነገር ሲያብላሉ ቆዩና "የዲምላን ነገር እምን አደረስከው?" በማለት ታዴዎስ ጥያቄውን አስከተለ።

"ፎቶውን አስበትኛለሁ። ባህር ዳር ከተማ ውስጥ የሱ ፎቶ ያልተለጠፈበት ጉዳና የለም።"

"ታዲያ የተገኘ ፍንጭ የለም?"

"የለም። በጢስ አባይ አካባቢ በሚገኙ አካባቢዎች አሳሽ የፖሊስ ኃይል እንዲሰማራ ተደርጎ እስከአሁን ሪፖርት አልተደረገልኝም። ፎቶውን ይዘው እያንዳንዱን ቤት እያንኳኩ

በማሰስ ላይ ናቸው። ውሎ አበሉን ዳጎስ ስላደረኩላቸው ተሰላችተው ፍለጋቸውን የሚያቆሙ አይመስለኝም።"

"ለምን ዲምላን ይዞ ለመጣ ሰው ጠቀም ያለ ክፍያ እንደምንፈጽም አልገለፅክም?"

"ለአሳሽ ፖሊሶቹ እሱን ይዞ ለመጣ ሰው መጠኑ ያልተገለፀ ጠቀም ያለ ጉርሻ እንዳለው ነግሬአቸዋለሁ።"

"ለእነሱ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ዲምላን ይዞ ለሚመጣ ሰው ከሁለት ሚሊዮን ብር ያላነሰ ሽልማት እንደሚኖር ቢገለፅ ይሻል ነበር። ያካባቢው ህዝብ ምስጢር ጠባቂ መሆኑ በከፍተኛ ጥቅም ካልሆነ በቀር በነፃ እንኳን ሰው አህያ ቢጠፋ እንኳ አይጠቁምም።"

"ይህን ሳላስበው ቀርቼ እንኳ አልነበረም። ምናልባት በቀላሉ የሚገኝ ከሆነ ያን ሁሉ ገንዘብ ማፍሰስ ላያስፈልግ ይችላል ብዬ በማሰቤ ነው ነገሩን ችላ ያልኩት።"

"ዲምላ በቀላሉ ይገኛል ብለህ ታስባለህ? ዶን በናና ስለሱ ያለው ግምት ከፍተኛ ነው።"

"እኔም እኮ በደንብ አውቀዋለሁ። የዋዛ ባሪያ አይደለም። ...ግን...በህይወት ያለ ይመስልሃል?"

"እንዴ እንዴ በህይወት ያለ አይመስለኝም። ዲምላ ከሚራዥ ጋር ተናንቆ በመጨረሻም በሲጳራ እንደተገደለ ነው የሚታመነው። ግንባሩ ላይ እንደተመታ ነው የሰማሁት።"

"ግንባሩ ላይ የተመታ ሁሉ ይሞታል ታዲያ?... ልክ ስትተኩስበት የሞተ መስሎ እየዋኘ ቁልቁል እንደ አርጃኖ ተስቦ አምልጦ ቢሆንስ?..."

"የዶን ቦናኖ ማምትም እንዳንተው ተመሳሳይ ነው፡፡ ዲምላ በቀላሉ ይሞታል ብሎ መገመት ተስኖታል፡፡"

"ካልሞተማ እስካሁን አንድ ነገር ያደርግ ነበር፡፡ እስከዛሬ አንድ ኮሽታ ሳያሰማ የት ይኖራል?"

"ምናልባት ሚራኝን ፍለጋ እየተንከራተተ ቢሆንስ? ኢክስካቫተር ዶዘሩን ጠምዶ አያርስበት? በሚራኝ እጅ የሚገኘው ካርታ በእጁ ካልገባ ኢክስካቫተሩ ብቻውን ምን ይሠራለታል?"

"...ሚራኝም እኮ ኢክስካቫተር ዶዘሩ የተቀበረበትን ቦታ ሳያውቅ አይቀርም፡፡ እስከ ሰባራ ድልድይ አብረው ከተጓዙ አንድ በጋራ የሚያውቁት ነገር አላቸው ማለት ነው፡፡"

"ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን አስከዛሬ አላሰብኩትም ነበር፡፡ ሚራኝን መያዝ ሁሉንም ነገር መያዝ ነው ማለት ነው፡፡"

"ተራራው በፍጥነት መሰበር አለበት፡፡ ኮማንዶዎቹ የእኛን ትእዛዝ በመጠባበቅ ላይ ናቸው፡፡"

"መቼ ይሁን?"

"ነገ ማታ ተራራውን ሰብረን እንገባለን፡፡ ስለዚህ እኔና አንተ በፍጥነት ቀደም ብለን ሄደን ነገሮቹን ማጠን አለብን፡፡ የአውሮፕላን ትኬት ለነገ ጠዋት በረራ እንዲዘጋጅልን

አደርጋለሁ። ኒቆዲሞስና ታዴዎስ ይህን ከተነጋገሩ በኋላ ደውለው በጠዋት ወደ ባህር ዳር የሚበረው አውሮፕላን ትኬት እንዲዘጋጅላቸው አስደረጉ።

# ፳

## እንጦንስ ገዳም + ግብፅ

ሚራኘር የገዳሙን መግቢያ አልፎ እስኪገባ ድረስ ሁለቱ መነኮሳት ከኋላው ይከተሉ ነበር። ነገር ግን ልክ የገዳሙን መግቢያ እንዳለፈ አንዱ ከፊቱ ቀድሞ ሁለተኛው ደግሞ ከኋላው ሆነው አጀቡትና ወደ ገዳሙ አስተዳደር ቢሮ ወሰዱት።

ሚራኘር ወደ ገዳሙ አስተዳደር ቢሮ ከመግባቱ በፊት አጠቃላይ የግቢውን ገፅታ ለመቃኘት ሞክሮ ነበር። ቅጥሩ፣ ጉልላታቸው የእንቁላል ቅርፅ ባላቸው ቤቶች ተሞልቷል። ቤቶቹ በጭቃ የተመረጉ ጉተራዎች ይመስላሉ። ሁሉንም በፍጥነት ገርምሞ ሳይጨርስ ወደ አንድ የእንቁላል ቅርፅ ወዳለው ቤት ይዘውት ገቡ። አንድ ጢማም መነኩሴ ተነስተው ተቀበሉት። ለቡራኬ አጎነበሰ። እርሳቸውም በኮፕቲክ ኦርቶዶክስ የቡራኬ ፀሎት ከተልጎመጎሙ በኋላ ባረኩትና እንዲቀመጥ ጋበዙት። ይዘው ያመጡት ሁለቱ ሰዎች ሄደው ነበር።

መነኩሴው ትኩር ብለው ሲያዩት ከቆዩ በኋላ ከየት እንደመጣና ስሙ ማን እንደሚባል ጠየቁት፡፡ ሚራኸርም የክርስትና ስሙን በማስቀደም ከኢትዮጵያ እንደመጣ ሳይደብቅ ነገራቸው፡፡ ንግግራቸው በእንግሊዝኛ ስለነበር ሚራኸር ሁሉንም ነገር ለማስረዳት አልተቸገረም፡፡

"ለምን እንደመጣህ ትገልፅልኛ?" አሉ አንድ መዝገብ ገልጠው ስሙንና ከየት እንደመጣ ከመዘገቡ በኋላ፡፡

"አባት ሆይ ... አመጣጤ እንኳ ብቻዬን አልነበረም፡፡" ሚራኸር ከየት እንደሚጀምር ግራ ተጋባ፡፡

"...የበረሃው ክምሲን ለያዬን እንጂ ከአንድ ወንድሜ ጋር ነበር የመጣነው፡፡ ከኢትዮጵያ እዚህ ድረስ በረሃውን አቋርጠን የመጣነው ከዚህ ቀደም ወደዚህ ቅዱስ ቦታ ለምነና የመጣ ወንድማችንን ለመጠየቅ ነው፡፡" አለና ገፅታቸውን ለማጤን ሞከረ፡፡ ቀና ብለው ሳያዩት መፃፋቸውን ቀጥለዋል፡፡ ንግግሩን ሲያቋርጥ ፅሁፋቸውን አቁመው ተመለከቱት፡፡ የተናገረው ነገር አሳምኗቸው ይሁን አይሁን ለማጤን ከጀለ፡፡ ሆኖም ምንም አይነት ስሜት ፊታቸው ላይ ሊያይ አልቻለም፡፡ ጥቂት በጥሞና ሲመለከቱት ቆዩና፡፡

"ጓደኛህ እንኳ... ካንተ ቀደም ብሎ ደርሷል፡፡ ከፍተኛ ጉዳት ላይ ስለሆነ ወንድሞች እየረዱት ነው፡፡ እንደ አንተ መናገር ቀርቶ ውሃ እንኳ ለመጠጣት አልተቻለውም፡፡"

"አባት.. ሳየው እችላለሁ?" አለ ሚራዥ የዣጊንዳ በህይወት መኖር አጠራጥሮት፡፡ በሌላ በኩል እሱንም ለብቻው እየመረመሩት ይሆናል ሲል ተጠራጠረ፡፡ ያልጠበቁት ነገር ገጥሟቸው ተለያዩ እንጂ እንደደረሱ ለሚጠየቁት ነገር መልስ ለመስጠት ተዘጋጅቶ የነበረው ሚራዥ ነበር፡፡

"ለመሆኑ ስንት ወራት ፈጀባችሁ?" ሲሉ ከሀሳቡ አናጠቡት፡፡ ከባድ ጥያቄ ነበር፡፡ ከኢትዮጵያ ግብፅ ድረስ በእግር ተጉዞ ለመግባት ስንት ወራት እንደሚፈጅ አያውቀውም፡፡ ይህን መሰል ጥያቄም እጠየቃለሁ ብሎ አልገመተም ነበር፡፡

"የተጓዝነውን ወራት እንኳ በቁጥር ለመገመት ያዳግታል፡፡ አልቆጠርነውም፡፡ ልባችን እዚህ ስለነበር የተራመድነውን እርምጃ፣ በበረሃው ውስጥ ያሳለፍነውን ጊዜና መከራ ልብ አላልነውም፡፡" አለና ወራቱን በቁጥር ከመግለፅ ተቆጠበ፡፡ በዚሁ ጥያቄያቸውን እንዲያበቁ በልቡ ሳይፀልይ አልቀረም፡፡ 'ዣጊንዳን ጠይቀውት ቁጥር ጠርቶ ይሆን? ኧረ እንዲያውም! በእግር እንዳልመጣን ተናግሮስ ቢሆን?' ሚራዥ በሀሳብ ተወጠረ፡፡

"ለመሆኑ ልትጠይቁት የመጣችሁት ወንድም ማን ይባላል?" አሉ መነኩሴው የሚራዥን ግራ መጋባት እያጤኑ፡፡ "ምነው ግራ የተጋባህ ትመስላለህ?"

“አይ ግራ እንኳ አልተጋባሁም፡፡ ምናልባት የድካም ስሜት ይሆናል፡፡ የበረሃው ጉዞ እንደ ቀትር አባብ ያራግፍል፡፡” በማለት ግራ መጋባቱን ካስተባበለ በኋላ “አባ አልፋ ይባላል፡፡ አልፋ…” ብሎ መናገር አስመናሩን ለመስማት ጓጓ፡፡ መነኩሴው ግን ዝም ብለው ያጤኑት ጀመር፡፡

“እዚህ አልመጣም ይሆን? ወይስ በረሃው በልቶት ይሆን? አልፋ …”

“ለምንድን ነበር የፈለጋችሁት?”

“ያው ቅድም እንዳልኩት ደህንነቱን ለመጠየቅ ነው፡፡ በድንገት ተለይቶን ስለመጣ ደህንነቱ እስከዛሬ እንዳሳሰበን ነው፡፡”

“ወንድሜ ይህን ስነግርህ አዝናለሁ፡፡ አልፋ ይሁን ወይም ሌላ ሰው ከሁለት አመት በፊት… እዚህ ታች አበረሃው ውስጥ ሞቶ ተገኝቷል፡፡ ምናልባት ጊንጥ ወይም አባብ ነድፎት ይሆናል፡፡”

ይህን ሲሰማ ሚራኸ ሰማይና ምድሩ የተገለባበጠበት መሰለው፡፡ መናገር አልቻለም፡፡ ደነዘዘ፡፡ ደነገዘ፡፡ ምላሱን እንኳ ማላወስ አልቻለም፡፡ ጉሮሮው ሲደርቅ ተሰማው፡፡ ከጀርባው ያለውን ግድግዳ ለመደገፍ ወደ ኋላው ተለጠጠ፡፡ ነገር ግን አልቻለም፡፡ ከግድግዳው ሳይደርስ በጀርባው ተዘረረ፡፡ ጭንቅላቱ እንደ ቦንብ የፈነዳ መሰለው፡፡

## አስቴጥስ በረሃ፤ ግብፅ

ሜሮዳና ጌራ በዴር33 ውስጥ ሆነው ከተከመረባቸው የአሸዋ መርግ እንዴት መውጣት እንደሚችሉ ሲያወጡ ሲያወርዱ ከቆዩ በኋላ ጌራ በድፍረት አንድ ነገር ለማድረግ ወሰነ፤ እሱም የዴር33ን መስኮት መክፈት ነበር፡፡ ሆኖም ሜሮዳ አጥብቃ ተቃወመችው፡፡

"አብደሃል? መስኮቱን ስትከፍተው አሸዋው ጭራሽ ወደ ውስጥ ገብቶ ቢውጠንስ?"

"ሜሮዳ ... ሁሉንም እኮ ሞከርን፡፡ ያልሞከርነው ይህን ብቻ ነው፡፡"

"አንድ ነገር ግን አልሞከርንም"

"እስኪ ንገሪኝ! ምን?...ምንድን ነው ያልሞከርነው?"

"ለምሳሌ ሞተር አስነስተህ ወደ ኋላ ወይም ወደፊት ለመንዳት አልሞከርክም፡፡ ምናልባት የአሸዋው ክብደት ከሞተሩ ጉልበት ሊቀል ይችላል፡፡ የተጫነን ሁሉ ከባድ አይደለም፡፡ በስህተት እስከ ነፍሱ የተቀበረ አስከሬን እንኳ ለመውጣት ይታገላል፡፡"

"አስከሬኑ የሚሞክረው እኮ ታዲያ ሳጥኑን ለመስበር ነው። እኔም ያልኩት ያንኑ ነው። መስኮቱን መክፈት።"

"ከፍተን ብንወጣ እንኳ አሸዋው ውስጡን ገብቶ ይሞላዋል። ከዛ በምን ገብተህ ሞተር ልታስነሳ ነው? ወይስ የግብፅን ፖሊሶች ጠርተህ እንዲጎትቱልህ ልትጠይቅ ነው?"

ጌራ ጥቂት ካሰበ በኋላ በሜሮዳ ሀሳብ ተስማማ። የዶጅ33ን ሞተር አስጓርቶ ከቀሰቀሰ በኋላ ዝቅተኛ ማርሽ አስገባ። ቀጥሎም ወደ ኋላ ለመውጣት የኋላ ማርሽ አስገብቶ ነዳጅ መስጫውን ተጫነ። ንቅንቅ አላለችም። በመቀጠል የፊት ማርሽ አስገብቶ ነዳጅ መስጫውን ረገጠ። ዶጅ33 ከቅርፊቷ እንዳልወጣች ጫጩት እዛው መንፈራገጥ ያዘች። ወደ ፊትና ወደኋላ አያሌ ጊዜ ሞከረ። እየቆዩ የተወሰነ ቦታ እያገኘች መጣች። በመጨረሻ ግን ያለ የሌለ ጉልበቱን ተጠቅሞ የፊት ማርሽ በማስገባት በኃይል ረገጣት። ዶጅ33 ከገደሉ እንደሚወጣ ፍልፈል ከዋጣት አሸዋ ውስጥ ተልወስውሳ ወጣች። ሜሮዳና ጌራ ተአምር የተፈጠረ ያህል በማያውቁት ስሜት ተፋጠው ተያዩ። ሜሮዳ አይኖቿንና አፏን እኩል ከፍታ በሲቃ ሳቀች፤ ጌራም ተከተላት። ሜሮዳን አንዳች የሚገፊትር ኃይል ወደ ጌራ ወረወራት። ከንፈሩን ግጥም አድርጋ ሳመችው።

"ሜሪ... ወጥቼ ካላየሁ ከዛ መአት ውስጥ ተመንጥቀን እንደወጣን ለማመን አልችልም።" አለ ጌራ የዶር33ን መስኮት እየከፈተ።

"እኔም አላምንም። በህይወት ያለንም አይመስለኝም። ሞተን ይሆን?... ይሄ ጣረ ነፍሳችን እንዳይሆን!"

ሁለቱም ወጥተው አካባቢውን ለመቃኘት ሞከሩ። እልም ካለ በረሃ መሃል ቆመው ራሳቸውን እስኪያገኙት ድረስ በጣረ ሞትነት እንጂ በህይዎት ያለ አልመሰላቸውም ነበር።

ቀስ በቀስ ከጥጋቸው ያለውን ሁሉ ሲመለከቱ ያዩትን ማመን ተሳናቸው። ከምሲኑ አምጥቶ የሰቀላቸው ከአንድ በበረሃው መሃል ከሚገኝ ኮረብታ ላይ ነበር። ዙሪያው በሸለቆ የተከበበ ኮረብታ።

ዶር33 ከዚህ ጥልቅ ሸለቆ ውስጥ ወርዳ ልትፈጠፈጥ የቀራት በግምት አምስት ሜትር ያህል ብቻ ነበር። ወደ ኋላቸውም ከዚሁ የበለጠ ርቀት አልነበረም። ሁለቱም ዙሪያቸውን ሲቃኙ አዞራቸውና መሬቱን ቆንጥጠው ተቀመጡ።

"የፈጣሪ ያለህ!" አለ ጌራ ሜሮዳን እየተመለከተ። "እንዴት ነው የታደገን?"

ሜሮዳ ጌራን አቅፋ ተንሰቅስቃ ታለቅስ ጀመር፡፡ ሜሮዳን ስታለቅስ ሲያይ ለጌራ የመጀመሪያው ነው፡፡ እሷ ታለቅሳለች ብሎ ገምቶ አያውቅም ነበር፡፡ ለቅሶዋ ከመትረፋቸው የተነሳ እንደሆነ በመገመት አጥብቆ አቀፋት፡፡

"ለመሆኑ እነ ሚራኘር ይተርፋሉ ብለህ ትገምታለህ?" አለችው እንባዋን እየማገች፡፡

"አይመስለኝም፡፡" አለ ጌራ አንገቱን እየደፋ፡፡ "ተሟሙረን በበረሃው ብንፈልጋቸው ሳይሻል አይቀርም፡፡"

"ጌራ አብደሃል? ቀን እኮ ነው፡፡ ስንዘዋወር ብንገኝ እኮ ለወሬ ነጋሪ እንኳ ሳንተርፍ መቅረታችን ነው፡፡ ባይሆን በዶሩ33 ውስጥ የተተከለውን ስክሪን እንሞካከር ሞተው እንኳ ከሆነ የወዳደቀ አስከሬን ያሳየን ይሆናል፡፡"

"ቅድም ሞክረነው እንደማያሰራ አይተሽ አይደል እንዴ?"

"ቅድም አሸዋው ውስጥ ስለተዳፈነን ቢሆንስ?"

ወዲያው ጊዜ ሳያጠፉ ወደ ዶሩ33 ገቡና ስክሪኑን እያበሩ እያጠፉ ይሞካክሩ ጀመር፡፡

# ፳፱

## እንጦንስ ገዳም ÷ ግብፅ

ሚራኘር ከረጂም ደቂቃዎች በኋላ ዓይኖቹን ሲገልጥ ከገርንጊዳ ጐን ራሱን አገኘው። ካሉበት ጠባብ ክፍል ውስጥ ከእነሱ በቀር ማንም አልነበረም።

ሚራኘር የገርንጊዳን በህይወት መኖር ለማወቅ ቀና አለ። የገርንጊዳ ፊት እንዳልሆነ ሆኗል። ልክ እንደልብሳቸው ተሸነታትሯል። በአውሎ ነፋሱ ጊዜ ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰበት ተረዳ። የተሸነታተረ ቁስሉ የደረቀ ደም ኀርሷል።

"ገርንጊዳ" ሚራኘር በጥሪ ሊቀስቅሰው ሞከረ።

"ገርን...ገርን...ገርን..."

የገርንጊዳ ዓይኖች ቀስ በቀስ ተከፈቱና እንደገና ተዘጉ።

"በህይወት አለህ?..." ገርንጊዳ ዓይኖቹን እንደከደነ ተናገረ።

"አለሁ። ገርንጊዳ አንተስ ተርፈሃል?..."

"አስረውን ነው? የት ነን?"

"ገዳሙ ውስጥ ነን::" አለ ሚራኸር ገዳሙ ውስጥ እንደሆኑ እርግጠኛ ሆኖ:: "ያሰሩን አልመሰለኝም::"

"እ...አልፋ..."

"አልፋ ሞቷል:: በከንቱ ነው የደከምነው::"

"ሞቷል? ማን ነገረህ?"

"ወደ ገዳሙ አስተዳደር ቢሮ ገብቼ በጥያቄ ሲያጣድፉኝ ነበር:: ያኔ ጠይቄ መሞቱን ነግረውኛል:: ከዛ በኋላ ራሴን ስቼ ነበር መሰለኝ የሆነውን አላውቅም:: አንተስ ጠይቀውህ ነበር?"

"እ... አይ... ማንም የጠየቀኝ የለም:: እዚህ ማን እንዳመጣኝ እንኳ አላውቅም::"

"በረሃው ውስጥ ወድቀህ አግኝተውህ ይሆናል::" አለና ሚራኸር ከጥጋቸው የተቀመጠውን ቀልቀሎ አንስቶ ገርንጊዳን ውሃ አጠጣውና "አስረውናል ብለህ ትገምታለህ?" ሲል ጠየቀው::

"እኔ እንጃ ..." አለ ገርንጊዳ ውሃውን ገርግጮ ሲያበቃ:: "መነኩሳት አደሉ እንዴ? እንዴት የእግዜር እንግዳ ሊያስሩ ይችላሉ?"

"የግብፅና የኢትዮጵያ መናኝ አንድ እንዳይመስልህ:: የግብፅ መናኞች ከጥንት ጀምሮ እንግዳ ተመስለው በሚገቡ ጠላቶች ስለተጠቁ በቀላሉ የሚለቁን አይመስለኝም::

ለማንኛውም ተበረታታና በጊዜ ውልቅ ብለን ብናመልጥ ይሻለናል::"

"እንኳን የምናመልጥበት የምንቆምበት ጉልበት ከየት አምጥተን?"

"አይዞህ ቀስ እያልክ ለመንቃት ሞክር::" ሚራኸ ገንጊዳን ለማቃናት ሞከረ:: "በሞት ሽረት ትንቅንቅ ውስጥ ያለ ጉልበት የማይታመን አቅም አለው::" ገንጊዳ ከብዙ ሙከራ በኋላ ተልፈስፍሶ ተነሳና በቀልቀሎ የተቀመጠውን ውሃ አንስቶ ወደ ጉሮሮው አንቆረቆረው::

"እግርህ ተጐድቷል?" ሲል ሚራኸ ጠየቀው::

"አይ... እግሮቼ እንኳ ደህና ይመስሉኛል:: ጥቂት ወገቤ ላይ ግን ይሰማኛል::" በዚህ መሀል የጠባቧ ክፍል በር ተከፍቶ አንድ መነኩሴ አንገታቸውን አስቀድመው ገቡ:: መነኩሴው ሚራኸን በጥያቄ ያጣደፉት መነኩሴ ናቸው::

"ወንድሞች... ነቃችሁ?..." ካሉ በኋላ አንድ በግምጃ የተጠቀለለ ነገር ለሚራኸ አቀረቡለት:: "አልፋ ነው ያልከኝ? የእሱ ነው:: ምናልባት የፀሎት መጽሀፉ ይሆናል:: በግዕዝ ቋንቋ የተፃፈ ሳይሆን አይቀርም:: እኛ ልንፀልይበት አንችልም:: ምናልባት የፀሎት መፃህፍቶቻችሁን ከምሲኑ ቀምቷችሁ ከሆነ ፀልዩበት::"

ሚራኘ ውስጡ በደስታ ሲሞላ ታወቀው፡፡ አልፋ ቢሞት እንኳ አልፋ ጥሎት በሄደው ማስታወሻ ውስጥ አንድ ምስጢር ይገኝ ይሆናል በሚል ተስፋ እጆቹን በግምጃ ወደ ተጠቀለለው ጥቅል ሰደደ፡፡

"አይዟችሁ ወንድሞች፡፡ ከምሲኑ ሁልጊዜም እንደዚህ ነው፡፡ ፈጣሪ ጠብቋችሁ እንጂ አያሌ ሰዎችን ፈጅቷል፡፡" ካሉ በኋላ በሌላ ከረጢት ያመጡላቸውን ሽልጦ ከሁለት ገምሰው አካፈሏቸው፡፡ ሚራኘ ጥቅሉን የመፍታት ስሜቱ ቢያይልበትም ከጥርጣሬ ላለመውደቅ ሲል የሰጡትን ሽልጦ ያላምጥ ጀመር፡፡ በእርግጥም ተርቦ ነበር፡፡ ገርንጊዳ ሽልጦውን ተቀብሎ ወደ አፉ ሲልክ የመነኩሴን ቡራኬ ለመጠባበቅ እንኳ ጊዜ አልነበረውም፡፡ መነኩሴውም እንደተራቡ ስለገባቸው ወጥተው ውልቅ አሉ፡፡ ሁለቱም ሽልጦአቸውን በውሃ ካወራረዱ በኋላ በግምጃ የተለበጠውን ጥቅል ፈቱት፡፡ ለረገርም ጊዜ ከመቀመጡ የተነሳ አቧራ ውጦት ነበር፡፡

ተሰንብግበው ግምጃውን ፈቱት፡፡ በውስጡ ቡብራና ላይ በቁም ፅሁፍ የተፃፈ የፀሎት መፅሀፍ ነበር ያገኙት፡፡ በግዕዝ ቋንቋ የተፃፈው ይህ የፀሎት መፅሀፍ በውስጡ መዝሙረ ዳዊት፣ መልክአ ጊዮርጊስና መስጥመ አጋንንት የተደበላለቁበት ነበር፡፡ ሚራኘ ግራ ተጋባ፡፡ ግብፅ ድረስ የሚያስጉዝና ለበረሃ ስቃይ

የሚዳርግ ሳይሆን ሀገራቸው ውስጥ እያንዳንዱ ደብተራ እንጠልጥሎት የሚዞረውን መረጃ ነበር ያገኙት፡፡

ሚራኸና ዠንጊዳ ተስፋ በመቁረጥ ተፋጠው እየተያዩ እያለ ያሉበት ክፍለ በር ተበርግዶ ተከፈተ፡፡ በድንጋጤ ክው ብለው ወደ በሩ ሲዞሩ በረሃው ውስጥ ያገኟቸው ሁለቱ አረብኛ ተናጋሪ መነኮሳት በንዴት ጡፈው በመግባት ላይ ነበሩ፡፡ ከመግባታቸው ሚራኸንና ዠንጊዳን እያዳፉና እየጎተቱ ከጠባቧ ክፍል አስወጧቸው፡፡ በገዳሙ መሀል ለመሃል ባለው ጥርጊያ መንገድ እያዳፉ ከገዳሙ እንዳስወጧቸው ከገዳሙ በር ላይ ቆማ ወደ ምትጠብቃቸው ክፍት መኪና እንደ እቃ ወርውረው ጫኗቸው፡፡ የፖሊስ መለዮ የለበሱና የታጠቁ ሁለት ሰዎች ዘለው እንደወጡም መኪናዋ የበረሃውን አቧራ እያቦነነች ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ተወነጨፈች፡፡

# ፳፫

## አስቴጥስ በረሃ ÷ ግብፅ

ሜሮዳና ጌራ የዴርЗ3ን ውጫዊ ክፍል ያጠለቃትን አቧራ ሲያራግፉ ከቆዩ በኋላ እንደገና ወደ ውስጧ ገቡ። አልታያቸውም እንጂ እነርሱ ራሳቸውን አቧራ አጥልቋቸው ነበር። የዓይኖቻቸው ሽፋሽፍቶች በብናኝ ተሞልተው ወፍጮ ቤት የዋሉ መስለዋል። በውስጧ ያለውን አቧራም ሙልጭ አድርገው ካፀዱ በኋላ ሞተሯን ቀሰቀሱ።

ሞተሯን ሲያሞቁ ከቆዩ በኋላም በውስጧ የተገጠመላትን ስክሪን ቁልፎች ይነካኩ ጀመር። ከብዙ ድካም በኋላ ብዥ ብዥ የሚል ምስል መጣ። ከትእግሥት አስጨራሹ ጥበቃ በኋላም ምስሉ እየጠራ መጣ።

ሁለቱም በምስሉ ላይ የሚያዩትን አለመኑም፤ ሚራዥና ገንጊዳ በክፍት የፖሊስ መኪና ተጭነው ሲጓዙ የሚያሳይ ምስል ነበር የመጣላቸው። እንደተያዙ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀባቸውም።

"ይዘዋቸዋል" አለ ጌራ ተስፋ በመቁረጥ በሁለት እጆቹ ጭንቅላቱን ይዞ። "የተፈራው ነገር ደረሰ። አሁኑኑ ነው የሚረሽኗቸው።"

"አስረው እንደሚመረምሯቸውማ አትጠራጠር። ሰርገው የገቡ ኢትዮጵያውያን ሰላዮች ይመስሏቸዋል" አለች ሜሮዳ የበለጠ ወደ እስክሪኑ እየተጠጋች።

"ለመሆኑ እኛ ያለነው የት ነው?"

"ከበረሃው እስካልወጣን ድረስ አስቂጥስ በረሃ ውስጥ ሳይሆን አይቀርም ያለነው።"

"እነርሱስ?"

"ከዚህ ሁሉ ..." አለችና ሜሮዳ የስክሪኑን አቅጣጫ ጠቋሚ ቁልፍ ተጫነች። አሁን ያሉት እዛው ከምስራቃዊው በረሃ ቢሆንም እጅግ ርቀው ነበር። ሚራችና ዣንጊዳን ጭና የምትከንፈው የፖሊስ መኪና ደግሞ ከእነሱ በስተደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ሰማኒያ ስድስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ነበር።

"ምንድን ነው ማድረግ ያለብን?" ጌራ ሜሮዳ አቅጣጫ ጠቋሚውን ቁልፍ ዘግታ ምስል ከሳቹን ቁልፍ ተጭና እንደተመለሰች ጠየቃት።

"እስኪመሽ ድረስ እዚህ መቆየት አለብን። ምንም አይነት ሀሳብ ቢመጣልን በዚህ ሰዓት ምንም ማድረግ አንችልም።"

“እስኪመሽ ቢገድሏቸውስ?”

“አሁን ማዳን እስካልቻልን ድረስ የማያመጣው ለውጥ የለም::” ብላ ፍርጥም አለች ሜሮዳ::

“ይህቺ መኪና ብትይዝ አራት ወይም አምስት ፖሊሶችን ቢሆን ነው::” ይህን አለና ጌራ የዶ.ር33ን ቁልፎች ይጫጫን ጀመር:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ረጅም በ ቁ ቅርዕ የተሰራ መሳሪያ ወጣ:: “ይህን መሣሪያ እስከዛሬ አይተሽው አታውቂም:: በምስጢር የተያዘ ነበር:: የጨረር መሣሪያ ነው::”

ሜሮዳ እስከዛሬ በተደበቃት ምስጢር እርር ድብን ትል ጀመር:: “ይህን ያህል አንተማመንም ማለት ነው?”

“የመተማመን ወይም ያለመተማመን ጉዳይ አይደለም:: ምስጢር ነው ማለት ምስጢር ነው:: ምናልባት እስካሁን ምስጢሩን የያዝኩት አላግባብ እንዳንጠቀመው በመፍራት ነው::”

“ለመሆኑ ማን ማን ያውቃል?”

“እኔ፣ ሻጊዝ፣ ሚራኘና ዣንጊዳ ብቻ:: ሻጊዝ የነደፈው መሣሪያ ነው:: ይልቁንስ አጠቃቀሙን ላሳይሽ::”

“የጨረር መሣሪያ ላንዴ የተላከው ለብዙ ነው:: ይህን መሣሪያ የኛ ሰዎች በተጫነበት መኪና ላይ እንድጠቀመው ልታስጠናኝ ከሆነ ተሳስተሃል፤ አላረገውም::”

"ይህን ነው ላስጠናሽ ያልኩሽ። አንድን ኢላማ ነጥሎ ለመምታትም ሆነ በጅምላ ለመደምሰስ ያገለግላል።" ካለ በኋላ ጌራ ይህንኑ በ 'ቶ' ቅርፅ የተሠራ ረቂቅ መሣሪያ አጠቃቀም ያሳያት ጀመር። በ 'ቶ' አናት ቀለበቱ ውስጥ አሥራ ሶስት ቁልፎችና ኢላማውን ነጥሎ የሚያሳይ መነጽር አለው። ከ'ቶ' ጫፍ ስር ደግሞ ጨረሩ የሚወጣበት ቀዳዳ ተበጅቶለታል። "ተኩስ ብንከፍት መኪናው ባጠቃላይ ይጋያል። ይህ መሣሪያ ግን ያለ አንዳች ኮሽታ እያንዳንዱን ኢላማ ለቅሞ ይጨርሳል።" አለና ጌራ ዶር33ን ወደ ኋላ ያሽከረክራት ጀመር። ያለውን ጠባብ ቦታ እንደጨረሰ እንደገና ወደፊት አስወነጨፋት።

ዶር33 ተቆንናበት የነበረውን ኮረብታ ለቃ ሸለቆውን ቁልቁል እያዩች ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ከነፈች።

# ፳፬

ባህርዳር ÷ ኢትዮጵያ

ጣና ሆቴል ብዙ ግርግር አይታይበትም፡፡ ፍተሻው ከወትሮው ጠንከር ብሏል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት እነ ኒቆዲሞስ በዚህ ሆቴል ውስጥ ስለሚገኙ ነው፡፡ ወዘ ልውጥ ቀርቶ የተለመደ ደንበኛ እንኳ በቀላሉ ወደ ሆቴሉ መግባት አይቻለውም፡፡ እንዲያውም ከሚገባው ይልቅ የሚመለሰው ይበዛል፡፡ ምክንያቱ "ልዩ ዝግጅት ተይዟል" የሚል ነው፡፡

ኒቆዲሞስና ታዴዎስ ኢያሱ መናፈሻው ውስጥ ተቀምጠው ከጣና ሐይቅ የሚመጣውን ንፁህ አየር በማጣጣም ላይ ናቸው፡፡ ሌሎች ሁለት እንግዶች አብረዋቸው ቆይተው ሄደዋል፡፡ እነዚህ ሁለት እንግዶች ዲምላን በማስስ ላይ የተጠመደውን ግብረ ኃይል የሚመሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ከሰዎቹ እስከ አሁን የተገኘ መረጃ የለም፡፡ ዲምላን የበላው ጅብም አልጮኸም፡፡ ሆኖም አግኝተን ቀብረነዋል ያሉ ሁለት የአባይ ዳር ባላገሮች ተይዘው በመመርመር ላይ ናቸው፡፡

"ወይ ጥጋብ!" አለ ኒቆዲሞስ የባላገሮችን ድፍረት ሲያስላስል ቆይቶ። በምን ድፍረት ነው ያገኙትን የሰው አስከሬን ለፖሊስ ሳያሳውቁ የሚቀብሩት? ከዚህ ቀብር ጀርባማ የዲምላ ማሳሳቻ ሴራ ሳይኖርበት አይቀርም።"

"ዛሬ ወደ ማታ ሄጄ ተቀበረ የተባለውን አስከሬን አስቆፍሬ አይቸዋለሁ። ቢበሰብስም የአጥንቱ ግዙፍነትና ሁለመናው ዲምላን ይመስላል።" አለ ታደዎስ ኢያሱ ሊያጥወለውለው እየቃጣው። "እኔ በበኩሌ ዲምላ መሆኑን አምኛለሁ። ስምቱ እንዳለትም አስከሬኑን ያገኙት በአባይ ወንዝ ዳርቻ ነው። ከሰባራ ድልድይ በጣም ወረድ ብሎ መገኘቱ ደግሞ የሞተበትን ቦታ በመጠቆሙ እሱን ወደመሆን ይቀርባል። በዛ ላይ ሁለቱ ገበሬዎች አስከሬኑን ያገኙት እንጂ የቀየውን ሰው ጠርተው የአካባቢውን ሽማግሌዎችም ነግረው፣ ፊላጊ ዘመድ ቢያጡ ነው የቀበሩት። አሰሙን ፎቶ ስላነሳሁት በደንብ መመልከት ትችላለህ። በራት ሰዓት ባታዩው ይመረጥ ነበር። ያጥወለውላል።" አለና ለኒቆዲሞስ በርከት ያሉ ፎቶዎችን ሰጠው።

ኒቆዲሞስ የንባብ መነፅሩን ከሰካ በኋላ የአስክሬኑን ፎቶዎች እየገላበጠ ተመለከታቸው።

"የማይታመን!...ዲምላ ሞቷል ብሎ ማን ያምናል?!... ህ ... ይህ መቼስ ተአምር መሆን አለበት!...

ዲዎላ በነዛ ምናምንቴዎች ተገድሏል ቢባል ማን ያምናል?!" አለና እሱንም ለማጥወልወል ሲከጅለው ለታዲዎስ ፎቶዎቹን እየተጠየፈ መለሰለት። "ሞቶም የሚከረፋ ክርፋታም ባሪያ! ሲኦል መቼስ እሱ ከሞተ ወዲህ ግማቷ በአሥር እጅ ጨምሮ ይሆናል። ለመሆኑ ዶን ቦናኖ እነዚህን ፎቶዎች አይቶ የሚያምን ይመስልሃል?"

ታዴዎስ ኢያሱ የኒቆዲሞስን መልስ ሳይመልስ ኮለኔል ኪሩቤል መጥቶ ተቀላቀላቸው። ቀይ ቀበሮ ተብለው የተሰየሙት የጋሙስ ኮማንዶዎች ዋና አዛዥ ነው። ጣና ሆቴል ውስጥ በተያዘለት ፈረስ የሚያስጋልብ ክፍል ውስጥ ጥቂት ረፍት እንዲያደርግ ቢተውትም አላስቻለውም። የሰሞኑ ረፍት የማይሰጠው የጋሙስ ግርግር እንኳን ንዑህ እንቅልፍ ሊያስተኛው ዓይኖቹን እንኳ ሊያስከድነው አልቻለም። በየቀኑ የሚሰማው አዲስ ነገር ነው። በዛ ላይ ቀይ ቀበሮዎቹ ግዳጃቸውን በማያዳግም ሁኔታ እንዲምጡ ከፍተኛ ኃላፊነት ብቻም ሳይሆን ከሰማይ የሚከብድ እምነት የተጣለበት ሰው ነው። በተለይም የኒቆዲሞስ መመኪያ ተብሎ ከመታወቁ በተጨማሪ ለጋሙስ የጀርባ አጥንት ከሆነው የአፋኝ ቡድን ጀርባ የዚህ ሰው ጠንካራ ክንድ አለበት ተብሎም ይታመናል። እንዲያውም ይህ ሰው ጋሙስ አንድ ርምጃ ሳይራመድ ሁለት ርምጃ ከፊት የሚቀድም ነውም ተብሎ ይሞካሻል። ይህ ሆኖ

ስለ መረር ባሉ ውይይቶች መሐል ጣል የሚያደርጋቸው ቀልዶች አይወደዱለትም።

ኪሩቤል ከኒቆዲሞስና ከታዴዎስ ፊት ለፊት ወንበር ስቦ ተቀመጠና ከታዴዎስ እጅ ወስዶ የዲዎላ የተባሉት አፅመ ገብ ፎቶዎች እንደገና ተመለከታቸው። "ሳጥናው እንጂ እንደ አርኪዮሎጂስት!" አለና ፈገግ አለ። ታዴዎስና ኒቆዲሞስ ግን ዝም አሉት።

ኒቆዲሞስ ቱስካኖውን ለኩሶ ሲያበቃ፣ "ኪሩቤል እስኪ አንተን ልጠይቅህ ዶን ቦናኖ እነዚህን ፎቶዎች አይቶ የዲዎላን መሞት አምኖ የሚያረጋግጥ ይመስልሃል?" አለው አንዴ ምን እያትጎለጎለ።

"አንዳንዴ ሁኔታዎች አስገድደውን እናምናለን። የማንሸሸው እውነታ አእምሮአችንን በመሳምት መደሻ ወቅሮ ሲያጣምመን አንዳንድ እውነታዎችን ከመቀበል በቀር አማራጭ የለንም። ለምሳሌ ባለፈው አንድ ውስኪ ቤት ውስጥ..."
ኒቆዲሞስ አቋረጠው። "ጀምርክ እንግዲህ!... ይህን ቀልድና ቁምነገር መቀላቀልህን በምን ጠበል ባስለቀኩት?"
"ኒቆ ... የኔን በሽታ ከውስኪ በቀር የሚፈውስ ጠበል የለም። እና እላችሁ ባለፈው..." ቀጠለ። ኪሩቤል ሁሌም

እንደዚህ ነው። ተው ካሉት እንደሚብስበት ስለሚያውቁ ዝም አሉት። "ውስኪ ቤቱ ውስጥ ያገኘሁት አንድ ጎልማሳ ጭንቅላቱን በመላምት መደሻ ሲያጣምመኝ አመሸ እላችኋለሁ። መላምት ካሉት ሁሉም መላምት ነው። ምን አለኝ መሰላችሁ... 'ኮለኔል' ቢለኝ 'አቤት' አልኩት። 'ኮለኔል ከምልህ ከፋፍል ብልህ ይቀለኛል' ብሎኝ እርፍ! እኔም ጠበሉን ቀማምሶ እንደተናገረኝ በመገመት ከፋፍል ያለበትን ሁኔታ በመላምት እንዲያስረዳኝ ጠየኩት። ቀጠለና ያዝንብብኝ ጀመረ! 'እስኪ እግዜር ያሳይህ! ህዝቡ የሀገር ፍቅሩ እንደ ጉም ተኗል። ሀገራዊ ስሜቱ እንደ ይሁዳ ክዶታል። ሠራተኛው ተስፋ ቢስና አብሮ መሥራት የማይችልና የዘር ዛር እንዘርዝሮ እናቱ ላይ ወጥቶበት አጥንት ቆጠራ ገብቷል። ሙጣጭ የሀገር ፍቅር አለኝ የሚለውም ራሱን እንደ ሁለተኛ ዜጋ የሚቆጥርና መንፈሱ የላሸቀ ነው። አንተ የምትጠብቃቸው ባለሥልጣናት ደግሞ የአልጠግብ ባይነትና የስግብግብነት ጋኔን ስለመታቸው በየቀኑ አዋጅ በማውጣት ጠላቶቻቸውን ይፈጁበታል። ሙስና እንዲሰሩ እንኳ የተፈቀደላቸው የሚመስሉ አለቆችና ምንዝሮች አሉ። ለመሞስን ራሱ ለሚሞስንልህ መሞሰን አለብህ። እንደዚህ ውርደት ውርጅብኝ የወረደበት ሀገር ኮለኔል ስትሆን አትሸማቀቅም? እኔ አንተን ብሆን ማዕረጌን በሙቶስ ቆርጬ ወዝ አደር እሆን ነበር።' አይለኝም መሰላችሁ!"

"ጥሩ ውስኪ አጠጥቶሻል!" አለው ኒቆዲሞስ ከትከት ብሎ ስቆ። "ከዛ ምን አደረክ?"

"ምንም!" አለ ኪሩቤል ፈገግ ብሎ። "እንጆቴ ቢያርም መላምቱን የማፈርስበት መላምት ስለሌለኝ ስቄ ተውሁት። መላምት ባቀርብለት እንኳ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በተደጋጋሚ የሰማው ስለሚሆን አፌን በዳቦ ብዬ ዝም አልኩ።"

"እኔ ግን አንተን ብሆን ኖሮ በኩርኩም ጭንቅላቱን ነበር አንገቱ ውስጥ የምከትለት።"

"እና ...."

"ቢቃ ቢቃ ...." አለ ኒቆዲሞስ ኪሩቤል እንዳይናገር ቴስካኖ የያዘበት እጁን ከፍ እያደረገ። በዚህ መሐል፣ "ዶን ቦናኖ" ሲል ታዴዎስ ወሬያቸውን ወደ ነበረበት ለመመለስ ሞከረ። "ዶን ቦናኖ ማመን አለማመኑ ዲምላን ከሞት አያስነሳውም። ይልቁንስ ይህንን እንተወውና ስለቀጣዩ ጉዳይ ብንነጋገር ይሻላል። አሁንም ያከተመ ነገር የለም። በሚራንዳ እጅ የሚገኙትን መረጃዎች በእጃችን ካስገባን መርከቡን ከማውጣት የሚያግደን አንዳች ነገር አይኖርም።"

ለአፍታ ዝምታ ከሰፈነ በኋላ ኒቆዲሞስ ሰዓቱን ተመለከተ

"ጠዋት ላይ ዶን ቦናኖ ባህር ዳር ይገባል። ከዛ በፊት ግን ቢያንስ ተራ-ራው መከበብ አለበት። ኪሩቤልም ቀልዱን

አቱዎማ ስላላችሁ ዝግጅት ባጭሩ አስረዳን::" አለና ቱስካናውን ሁለቴ ከማገ በኋላ:: "ለመሆኑ ወደ ተራራው ቃኚ ልከህ ነበር?"

"አዎ ልኬ ነበር::"

"ነበር?..." አለ ኒቆዲሞስ በክፉ አይን እየተመለከተው:: "ምን መረጃ አገኙ?"

"ምንም አይነት መረጃ አላገኙም::"

"ማለት ..."

"ምንም አይነት መከላከል ሳይገጥማቸው ወደ ተራራው አናት ወጥተዋል:: በተራራው ወገብ ላይ ተሰርቶ የነበረው ምሽግም ከባለፈው ጦርነት ወዲህ ምንም አይነት እንቅስቃሴ እንዳልተደረገበት ተደርሶበታል::"

"ተራራውን ሰብረው ለመግባት አልሞከሩም?"

"ይህን ለማድረግ ትዕዛዝ መቀበል ነበረብኝ:: የተራራውን አናት በጥብቅ እያሰሱ ቀጣይ ትዕዛዝ እንዲጠባበቁ ነው ያዘዝኳቸው::"

ኒቆዲሞስ የተገባደደ ቱስካናውን ልምክክ አርጎ ከሳበው በኋላ ትርኳሹን መሬት ጥሎ በንዴት ደፈጠጠው:: ምንም አልተናገረም:: ምንምም አላሰበም:: ከደቂቃዎች በኋላ፣

"አሁኑኑ ሰብረው እንዲገቡ አዝዛቸው! እዛው ውስጥ እንደፍልፈል አድፍጠው ይሆናል:: ቀያዩቹን ቀበሮዎች ግን

አንድ ነገር አስጠንቅቅልኝ።" አለ ኒቆዲሞስ ላዳን ላዳን እየተነፈሰ።

"ምን ብዬ ላስጠንቅቃቸው?"

"ሌሎቹን ፍልፈሎች እንደፈለጋችሁ አኝኳቸው። ነገር ግን እነዚህኞቹን..." ኒቆዲሞስ የሁለት ሰዎች ፎቶዎች ከቦርሳው አውጥቶ አቀበለው የሚራኘርንና የሻጊዝን ፎቶዎች።

"እነዚህኞቹን ፍልፈሎች ምን ያድርጓቸው?"

"ለአለቃችሁ አቆዩለት በላቸው!" አለና ኒቆዲሞስ ቱግ ብሎ ተነሳ። "ኪሩቤል! መጠንቀቅ ያለብህ እነዚህ ሁለት ሰዎች በስህተት እንዳይገደሉ ነው!" ታዴዎስንና ኪሩቤልን በተቀመጡበት ጥሏቸው ወደ ክፍሉ እየተጣደፈ ሄደ።

# ፳፫

## አስቴንጥስ በረሃ ÷ ግብጿ

"ዱ.ር33 የደቡብ ምዕራብ አስቴኖስ አቅጣጫን ይዛ በመብረር ላይ ናት። በአካባቢው ሰዓት አቆጣጠር 11:55። ዓይኗ ከመያዙ በፊት ሚራዥንና ዣንጊዳን ማትረፍ እንዳለባቸው የቆረጡት ሚሮዳና ጌራ ዓይኖቻቸውን ቁልቁል እንደ ንስር አሞራ ተክለው በመስኮቱ ላይ ናቸው። አለበለዚያ ይህ ሳይሆን ቢቀር የሚራዥና የዣንጊዳ ህይወት እንዳበቃለት አምነዋል። ያለ ፍርድ አንገታቸው በሻምላ ሊቀላ በዓይነ ህሊናቸው ተመልክተዋል።

በግምት ከግማሽ ሰዓት ጉዞ በኋላ በረሃውን አቋርጣ አቧራውን እያቦነነች የምትጓዝ ክፍት መኪና ከበታቻቸው ተመለከቱ።

ሚሮዳ፣ የዱ.ር33ን እስክሪን ተመልክታ ከበታቻቸው ከምትከንፈው መኪና ጋር አመሳከረች። ያለ አንዳች ጥርጥር ጌራ ዝቅ ብሎ እንዲበር ነገረችው።

"ስህተት እንዳይፈጸም ሜሮዳ፡፡ መኪናዋን አቧራ ስላለበሳት ሌላ ልትሆን ትችላለች፡፡ አንዴ ትክክለኛነቱ ሁሉም ነገር መሆማት አይቀርም፡፡ የግብፅ የጦር ሚሳኤሎች ወደኛ ከመወንጨፋቸው በፊት በፍጥነት ስዎቻችን ይዘን ከግብጽ ውልቅ ማለት አለብን፡፡ ዘመቻው አጭርና ፈጣን መሆን አለበት፡፡"

"አውቃለሁ፡፡ መኪናዋ ራሷ ለመሆንዋ ግን ጥርጥር የለኝም፡፡ አቧራው፣ ፍጥነቷና የምትጓዝበት አካባቢ ስክሪኑ ላይ ከማየው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ዝቅ ብለህ ብረር፡፡"

ዶር33 ዝቅ ብላ መብረር ጀመረች፡፡ ሜሮዳ በ'ዮ' ቅርጽ የተሠራውን የጨረር መሣሪያ ወደ ታች ደግና አላማዋን ማሰስ ጀመረች፡፡ አቧራው ግዳይዋን ጋርዶታል፡፡

"በነፋሱ አቅጣጫ ሁንልኝ፤ አቧራው ተግኖኛል፡፡" አለች ሜሮዳ ከመሣሪያው መነፅር ዓይኗን ሳትነቅል፡፡ ነፋሱ ከደቡባዊ ምዕራብ ወደ ሰሜናዊ ምስራቅ አቅጣጫ እየነፈሰ ነው፡፡ ዶር33 የደቡባዊ ምዕራብ ክንፍ ዝቅ ብላ መብረር ጀመረች፡፡ ሜሮዳ ከመኪናው ኋላ የተጫኑት ሰዎች በግልፅ ታይዋት፡፡ ሁለት መሣሪያቸውን የወደሩና መላ ፊታቸውን በሮጣ የጠመጠሙ ፖሊሶች ተመለከተች፡፡ ሌሎች ሁለት ሰዎች ደግሞ ከሥር ተንበርክከዋል፡፡ እነዚህኞቹ ሁለት ሰዎች ደግሞ ከሥር ተንበርክከዋል፡፡ እነዚህኞቹ

በመግረፊያው መንዕር ውስጥ ዓይኗን ማገደች። አንዳኛው ፖሊስ ኢላማዋ ውስጥ ከመግባቱ የጨሬር መተኮሻ ቁልፉን ተጫነችው። እንደ ክር የቀጠነው ጨሬር ሄዶ ሲሰፋበት የመንዕሩ ምስል አሳየት። ከመቅፅበት ፍንግል ሲል ተመለከተች።

"ኤጭ! ድምፅ አልባ መግረፊያ እንደት እንደምጠላ ብታውቅ!" አለች ሁለተኛውን ፖሊስ ኢላማዋ ውስጥ ለማስገባት እየፈለገች።

"የጠላትህን ጩኸትና ጣር ካልሰማህ መግደልህ መርዝ ስጥቶ ሲጥ ከምታደርግ የቤት ሠራተኛ በምን ይለያል?"

"ይልቅ መፈላሰፉን ተይውና ቀጥይ" አለ ጌራ "የሚቀጥለው ፖሊስ ተኩስ ሳይከፍት ቅድሚው!"

ሁለተኛው ፖሊስ መግረፊያውን ሲያነሳ ተመለከተችው። የመስቀል ቅርፅ ያለው ኢላማዋ ጭንቅላቱ ላይ ተመሳቀለ። ምላጩን ከመሳቡ በፊት እንደመርፌ የቀጠነው ጨሬር ጭንቅላቱን ሲበሳው አውቶማቲክ መግረፊያው ከእጁ ከዳው።

በዚህ ጊዜ ሚሬኘና ዝርንጊዳ ሁለቱ ፖሊሶች ያለ እንዳች ኮሽታ ሲወድቁ ሲያዩ፣ ግራ በመጋባት ወደ ስማይ

ተመለከቱ። የሚያውቋት ዶ.ር33 እንደ ነምር አሞራ በላዩቸው ላይ እያንገርበበች ነበር።

ወዲያው ረጅም ሰንሰለት ከዶ.ር33 ሆድ ወጥቶ ወደታች እየተወናጨፈ ወረደ። ሚራኘር ተቅመድምዶ ተነሳ። ዛሮንጊዳም እየተፍገመገመ ተከተለው።

ሚራኘር ኻርዋኻርዌ የሚጫወተው ወፍራም ስንሰለት ከእጁ እስኪገባ ጠብቆ ዘሎ ተጠመጠመበት። ሰንሰለቱ ከወዲያ ወዲህ ወገቡን እንደተመታ ዘንዶ ይወራጫል። ገርንጊዳ የሰንሰለቱን ጫፍ በቀላሉ ለመያዝ አልቻለም። እጆቹ አየር እየቀዘፉና አንዳንዴም የሰንሰለቱ ጫፍ እየሸነቆጣቸው ወደራሱ ይመለሱ ጀመር።

በዚህ ቅፅበት ከመኪናዋ ጋቢና የጥይት ሩምታ እንደተልባ ይንጣጣ ጀመር። በጋቢናው መስኮት ብቅ ያለው ፖሊስ ወደ ዶ.ር33 እና በሰንሰለቱ ላይ ተንጠላጥሎ ኻርዋኻርዌ ወደሚጫወተው ሰው ጥይት እንደ ቆሎ በመዝራት ላይ ነው። ገርንጊዳ ከረጂም የዛፍ ቅርንጫፍ ፍሬ ለማውረድ እንደሚዘል እረኛ እመር እመር እያለ ሲጥር ቆይቶ በመጨረሻ ሰንሰለቱን ለቀም አደረገው።

ዣንጊዳ በመንጠላጠል ላይ እያለም ከሥር የሚንጣጣው ጥይት አላባራም። ሚራዥንና ዣንጊዳን ጥይት እንዳያገኛቸው ስንሰለቱን ኾርቋኾርቄ እንዲጫወት የሚያደርገው ጌራ ሜሮዳን አንድ ነገር ወደ ኋላ አመለከታት።

"ጨጬኸት ከፊለግሽ ከኋላ ክፍል ያለውን ቦንብ አውጭና ወደ ታች እነሆ በረከት በይው።" አለና ቦንቡን ፊቷ ወደ ታች እስክትወረውር ይጠባበቅ ጀመር። ሆኖም በዚሁ አፍታ ዣንጊዳ በኃይል ሲያቃስት ተሰማ። ከታች እንደ አሸን የሚፈላው ጥይት ታፋውን አግኝቶት ነበር።

"ፍጠኚ ሜሮዳ! ሳይወድቅ ፍጠኚ!" ጌራ ጮኸ።

ሜሮዳ የቦንቡን ቀለበት መንጭቃ ቁልቁል ለቀቀችው። በሴኮንዶች ውስጥ በረሃውን የሚሰነጥቅ ፍንዳታ አጓራ። ወዲያው ክፍቷ መኪና ወደ ነበልባልነት ተቀየረች።

# ፳፪

## ዳጋ÷ ኢትዮጵያ

የምድር ውስጡ ዋሻ ከዓመታት በኋላ እንደገና መዕዳት ጀምሯል:: በሻጊዝ አነቃቂ ንግግር ነበር በናንዳታው የፈራረሰውን የምድር ውስጥ ከተማ እንደገና ወደ ነበረበት ለመመለስ ዘመቻ የተጀመረው::

ሻጊዝ እየተሟሟረ የጥንቱን ዋሻ ሲመለከት ከዋለ ካደረ በኋላ ነበር ቁጭት የተቀላቀለበትንና ለስብከት የቀረበውን ንግግሩን ሁሉንም ሰብስቦ ያሰማው::

"በዚህ ልንኖርም ላንኖርም እንችላለን::" በማለት ነበር የጀመረው:: "ነገር ግን ይህንን የምድር ውስጥ ከተማ አባቶቻችን ለመሥራት የፈጀባቸውን ያህል ጉልበት ቀርቶ አንድ ቋጥኝ ለመናስጥ ያወጡትን ላብ ያህል እንኳ ሳይልበን ተስፋ መቁረጣችን ያሳዝናል:: አባቶቻችን ሌሎችን ነፃ እንድናወጣ በእኛ ላይ ታላቅ ተስፋ ነበራቸው:: እኛ ግን ራሳችንን እንኳ ማዳን ተስኖን ከሊጥ እንደገባች ጫጩት መንፈሳችን እንደ ላባዋ ላሽቋል:: ለምን?... ያለ ትግል ድል አቀዳጃለሁ ብሎ የሚገምት በመካከላችን አለ? ያለ መራብ፣

ያለ መታረዝ፣ ያለ መሳደድ ድል የለም። የተልፈሰፈሰን አልመሰላችሁም? ከዚህ ዋሻ ውጥተን ጠላትን ስለመደበቅ ብቻ ለምን እናስባለን? እዚህም ስለመኖር ለምን አናስብም? ይህ የፈራረስ የምድር ውስጥ ከተማ ለእኔ የፈራረሰችው ሀገሬ ምሳሌ ነው። ብታምኑም ባታምኑም ይህ ትውልድ የተናደውን የመካብ፣ የፈራረሰውን የመጠገንና የወደቀውን የማቆም ግዴታ አለበት።" ካለ በኋላ ሁሉም በቆሙበት የሸማግዝ ክናዱን ሰብስቦ ራሱ ዕዳቱን ጀመረ። ሌሎችም ተከተሉት።

በቃጠሎው ወቅት የወዳደቁት አዕሞች ተሰብስበው ከተከፈኑ በኋላ በአንደኛው የዋሻው ክፍል በክብር እንዲቀመጡ አስደረገ። ለቀናት በፈጀው ዕዳት የምድር ውስጡ ከተማ እንደ ጥንቱ በቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ባይሞላም ጥሩ ገፅታ መላበስ ጀመረ።

የሻጊዝ እቅድ ዋሻውን መዕዳት ብቻ አልነበረም። ከጣቅርን ተራራ ተነስተው በምድር ውስጡ መንገድ ሲመጡ ይዘውት የመጡት መሣሪያ በየክፍሉ እንዲተከልም አድርጓል። በመሆኑም የዋሻው ክፍሎች ለመኖሪያ ብቻ ሳይሆኑ ወደ ተለያዩ የህክምና፣ የምርምርና ጥናት፣ የመሰብሰቢያና የእቃ ግምጃ ቤትነት ተሰይመዋል። ይህ ሁሉ ሆኖ ሲያበቃ ሁሉም

ወደየምድብ ሥራው ገብቶ ደፋ ቀና ማለት ጀምሯል። በዚህ ወቅት ነበር ዶ/ር33 ከግብፅ የተመለሰችው።

ዶ/ር33 ወደ ዋናው ገብታ ከቦታዋ እንደቆመች፣ ቆስሎ የሚያጣጥረውን ዣንጊዳን ይዘው እነሚራኘ ወረዱ። ሁሉም ከየክፍሉ እየወጣ የሆነውን ለማየት ከበባቸው።

ዣንጊዳ ወደ ህክምና ክፍሉ ገብቶ እርዳታ ማግኘት እንደ ጀመረ የጥያቄ መዓት ለሚራኘ ይዘንብበት ጀመር።

“አልፋ ተገኘ?”

“የሚቀጥለውን ቦታችንን አመለከታችሁ?” እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች ቢኘርጎደጎዱም፣ ሚራኘ ግን ለጊዜው ምንም መልስ እንደሌለው ተናግሮ ሲያበቃ፣ ይቅርታ በመጠየቅ ብቻውን መሆን እንደሚፈልግ ገለፀና የአልፋን መዝገበ ፀሎት ይዞ ወደ አንድ ክፍል ገባ።

# ፳፯

## ጣቅሮን ተራራ÷ኢትዮጵያ

ጣቅሮን ተራራ የጨለማ በርኖሱን ተጎናጽፎ ተኝቷል። ምሽቱ እጅግ ቢገፋም በላዩ ላይ ያደፈጡት ኮማንዶዎች ግን አላንጎላጁም። ከተራራው አናት በስተምዕራብ በኩል አንድ መግቢያ ቢያገኙም ትእዛዝ እስኪመጣ ድረስ እንዲጠብቁ በተነገራቸው መሠረት ወደ ተራራው ከርሰ ምድር አልዘለቁም። ይህ በሆነበት ሁኔታ የምሽቱን ፀጥታ የሚያናጋ ድምፅ በተራራው አናት ላይ ተሰማ የሚንደቀደቅ ሄሊኮፕተር ድምፅ።

ሄሊኮፕተሩ የተራራውን ቁጥቋጦዎች በውጅምጅሚቱ እያላጋ እንዳረፈ፣ በውስጡ የነበሩት ሰዎች መውረድ ጀመሩ። ኒቆዲሞስ፣ ታዴዎስ እና ኮሎኔል ኪሩቤል ከሌሎች አጃቢዎቻቸው ጋር እንደወረዱ በራዲዮ መልእክት ተገኘ ወደ ተባለው በር በፍጥነት አመሩ፤ ወደ ተራራው ሆድ ያስገባል ወደ ተባለው በር። ኒቆዲሞስ፣ የዛገውን የብረት በር ቆሞ ሲያስተውል ከቆየ በኋላ ኮሎኔል ኪሩቤል ኮማንዶዎችን ሰብረው እንዲገቡ ትዕዛዝ እንዲያስተላልፉ ነገረው። ኪሩቤልም ለደህንነታቸው ሲባል እነሱ ወደ ሄሊኮፕተሩ

እንዲመለሱ ካደረገ በኋላ ኮማንዶዎቹ በሩን ሰብረው እንዲገቡ አዘዘ፡፡

እጅግ ጥንታዊ የሚመስለውና በጠንካራ ብረት የተሠራው በር በኮማንዶዎች ርብርብ እንደ ተሰበረ፣ ራሳቸው ላይ የሚንቦገቦጉ ባትሪዎችን ያጠለቁት ኮማንዶዎች በጥንቃቄ ወደ ተራራው ሆድ መግባት ጀመሩ፡፡ አንዱ አንዱን እየሸፈነ ያለ አንዳች ኮሽታ የገባው የኮማንዶ ሠራዊት ዋሻውን እንደ ጉንዳን በቅዕበት ይወረው ጀመር፡፡ በዋሻው ውስጥ እየገባ የተሸጎጠው ኮማንዶ አንድም ያገኘው ነገር እንደሌለ ለኮሎኔል ኪሩቤል እንዳሳወቀ፣ ኒቆዲሞስንና ታዴዎስን እስከ ጥንቄቅ አጃቢዎቻቸው አስከትሎ ወደ ተራራው ሆድ ተመልሶ ይዟቸው ገባ፡፡ ኮሎኔል ኪሩቤል ግራ የተጋባ በሚመስል ሁኔታ ኒቆዲሞስና ታዴዎስ ላይ ይጮህ ጀመር፡፡

"ይህ ሁሉ ሠራዊት እዚህ ተራራ ላይ በውርጭ እየተጠበሰ የሰነበተው ባዶ ዋሻ ለመጠበቅ ነበር?" ሲል ኒቆዲሞስን አፋጠጠ፡፡ "ቀድሞም ትክክለኛ መረጃ አልነበራችሁም፡፡ ከመጀመሪያው ጦርነት በኋላ እዚህ እንደ ማይቀመጡ በተደጋጋሚ ብለፈልፍም ልትሰሙኝ አልቻላችሁም፡፡ ሁለተኛ ወረራ እንደሚፈፅሙባቸውና ሁለተኛው ከአንደኛው የከፋ እንደሚሆን መገመት

ያቅታቸዋል ብላችሁ ነው? እንደ ሰጣችሁን መረጃ ከሆነ ቡድኑ በአያሌ ሳይንቲስቶች የተመሠረተ እንደሆነ ነው::"

"እሺ የት ገቡ? አለ ኒቆዲሞስ በትልቅ ፓውዛ ባትሪ በተራራው ክርስ ምድር ውስጥ የተገነባውን እጅግ ውስብስብ ዋሻ እየተዟዟረ በመመልከት ላይ እያለ:: "...መቼስ ሰማይ ሰንጥቀው አይወጡ:: እንደ እኔ እንደ እኔ እነዚህ ሸለምጥማጦች ከዚህ ተራራ ውጪ ይሆናሉ ብዬ አልገምትም::"

"እንዴት እንዴት? ተራራውማ ይኸው ገብተንበታል:: እንደ እንሽላሊት በዋሻው ንቃቃት ውስጥ አይጣበቁ!" ኪሩቤል የፌዝ ፈገግታውን አሳዩ::

"በእኔ ይሁንብህ::" አለ ኒቆዲሞስ ፈርጠም ብሎ:: "ከዚህ ዋሻ ጋር የተያያዘ ሌላ ዋሻ ይኖራቸዋል:: እያንዳንዷ ሽንቁር በደንብ መጠናት አለባት::"

"እንዴት እንዲህ ልትገምት ቻልክ?" አለ ኪሩቤል ወደ ኒቆዲሞስ ግራ በመጋባት ዞሮ:: "ሁሉንም ነገር በግምት እየተመራን እስከ መቼ እንዝዛለን! አመርቂ ባልሆነ መረጃ ሰዎቻችን መንገላታቸው ተገቢ አይመስለኝም::"

"እየውልህ ኪሩቤል!... እኔ በበኩሌ ኒቆዲሞስ ባለው እስማማለሁ::" አለ ታዴዎስ በግርምት ራሱን እየነቀነቀ:: "እዚህ ተራራ ውስጥ ለአመታት ታስሬአለሁ:: እጅግ የተደራጀና በቴክኖሎጂ መሣሪያዎች የተሞላ ነበር:: አሁን

እንደምታዩት ግን በጣሽ ወረቀት ላይ የለውም። ከተቆረጠው መጥተው ቢሄዱ ጥሩ በሆነበ ከዝቤሬዎች ጋር የተላቀለባቸው ሰዎቹን ምልክት ያዩ ነበር። ሆኖም እንዳቸውም ምልክት አለነሁን ከመጤብ በኋላ ከላዩም። ስለዚህ ኒቆዲሞስ እንዳለው ከዚሁ ጥሻ ጋር የተያያዘ ሌላ ጥሻ ሊኖራቸው ይችላል ብሎ መገመት ቀላል ነው።"

"ስማኝ ኪሩቤል!... የፈጀውን ጊዜ የፈጀውን ኃይል ይፍጅ እንጂ ይህ ጥሻ በደንብ መጠናት አለበት። እያንዳንዱ ሽንቁር መመርመር አለበት!" ብሎ ኒቆዲሞስ ኪሩቤልን ያዘት ለብቻው ዘወር ካረገው በኋላ በለሆሳስ "ኪሩቤል! ስማኝ... ጠዋት ላይ ዶን ቦናኖን ባህር ዳር አውሮፕላን ማቢያ ሄደን መቀበል አለብን። ይህ ጥሻ ግን በሰዎቻችን እንደ ተያዘ ይቆይ። በጥብቅ እያንዳንዱ ቅርፊት እንዲጠና ትዕዛዝ አስተላልፍ። እኔ ምልህን ስማ። ሁልጊዜ በራስህ መንገድ ብቻ መጓዙ አያዋጣህም።" በማለት አስጠነቀቀው። ኪሩቤልም የኒቆዲሞስን ሁኔታ ካጤነ በኋላ ተሰላሰለና ወታደሮቹ እዚሁ እንዲቆዩና ጥሻውን እየበሩ እንዲመረምሩ ትዕዛዝ አስተላለፈና እነ ኒቆዲሞስን ተከትሎ ከተራራው ወጣ። ሄሊኮፕተሯ እነ ኒቆዲሞስን ከአጃቢዎቻቸው ጋር እንደያዘች ከጫነች በኋላ እየተንደቀደቀች ከተራራው ተነሳች።

# ፳፫

ዳጋ÷ኢትዮጵያ

ሚራዥ የአልፋን መዝገበ ፀሎት በጥንቃቄ ማንበቡን ተያያዞታል። በእርሱ ግሬት ወደ ግብፅ ሄደው በገርንጊዳ ላይ ለደረሰበት ጉዳት ራሱን በራሱ ተጠያቂ ከማድረጉም በላይ ለገርንጊዳ ካለው ልባዊ ፍቅር የተነሳ ውስጡ ተሰብሯል። የወንድሙን ያህል ለሚወደው ጓደኛው መቁሰል ቤዛ ይሆን ይመስል የአልፋን መዝገበ ፀሎት አንድ ምስጢር እንዲያቀብለው ያተረማምሰዋል።

በአልፋ መዝገበ ፀሎት ውስጥ ከተደጎሱት ሶስት የተለያዩ የፀሎት መፃህፍት መጨረሻ ላይ  አንድ ለዬት ያለ ፅሁፍ በመመልከቱ ቅጭም ብሎ ያጤነው ጀመር። ሶስት ገፅ ከግማሽ ብቻ ያለው ይህ የብራና ፅሁፍ የፀሎት ባህሪ እንደሌለው ተገነዘበ። ከዛ ይልቅ የግል ማስታወሻ ወይም የግለ ታሪክ ባህሪ ያለው ፅሁፍ  እንደሆነ ለመገመት አላዳገተውም።

ሚራዥ የፀሎት መፅሀፉን ዚጋና ጥቂት አሰላሰለ። በዚህ መፅሀፍ ውስጥ ያያቸው አንዳንድ አስማት መሰል ቃላት

ከዚህ በፊት በኪራኮስ አባት ማስታወሻ ውስጥ ከተገኙት አደናጋሪ ቃላት ጋር ተመሳስሎት እንዳላቸው አስታወሰ። ምንም ጊዜ ሳያባክን ብቻውን ከተቀመጠበት ክፍል ወጥቶ ኪራኮስን ፈልጎ ይዞት ተመለሰ። ኪራኮስ አንድ ክፍል እየቀባ ስለነበር በቀለም ተጨማልቋል።

ሚራኘ ከአልፋ መዝገበ ሀሎት ጋር ተያይዞ ያገኘውን ፅሁፍ ገልጦ ለኪራኮስ አሳየው።

“ይህ ፅሁፍ በአንተ አባት ማስታወሻ ውስጥ ከተገኘው ፅሁፍ ጋር ይቀራረባል ልበል?” በማለት ፅሁፉን እንዲያነበው ለኪራኮስ ሰጠው።

ኪራኮስ በጥንቃቄ ፅሁፉን አንብቦ እንደጨረሰ፣ “መቀራረብ ብቻ አይደለም፤ ይመሳሰላል። ይህ የሚለየው ግለ ታሪክ ስለሚመስል ነው። ለማደናገሪያ ያህል ‘በስመ አብ ወወልድ መንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ’ የሚል መንደርደሪያ መጨመሩ እንጂ ሌላ ልዩነት የለውም። ‘ተ’ በመሀላቸው የተጠለሰመባቸው አስማት መሰል ቃላቶቹ ከብዕር አጣጣላቸው በቀር ተመሳሳይ ናቸው።

ሚራዥ ቆሎ በሚመስል የቀለም ፅሁፍ የተከተቡትን በ‘ቶ’ የተሞሉ ቃላት አንድ በአንድ ለኪራኮስ ሲያነበንብለት አስማት

የሚደግም አባይ ጠንቋይ ይመስል ነበር፡፡ "ኤልቶኤል... ኤላቶኤል...አዳቶኤል...ኤማቶኤል...ኤልቶራን... ኤልቶዛር... ጌሰም.... ጌልቶጌል... አክቶኤም.... ካልቶኤብ... ኢዛቶናን... ባዜቶናን... ጎቦቶድራ... ጼንቶሎን፣ አፍቶጼን፣ ኢጋቶኤድ... የሀቶራድ... ዮራቶራድ..." የሚሉ አስማት መሰል ቃላትን ደጋግሞ አነበበላት፡፡

ኪራኮስ ሚራኻርን ለረዥም ደቂቃዎች ሲመለከተው ቆየና ጥሎት ወጣ፡፡ ከደቂቃዎች በኋላ የአባቷን ማስታወሻ ይዞ ተመለሰና አስማት መሰል ቃላት ያሉበትን ገፅ ገልጦ እሱም ለሚራኻር አነበበላት፡፡

"ኤልቶኤል...ኤላቶኤል...አዳቶኤል...ኤማቶኤል...ኤልቶራን... ኤልቶዛር... ጌሰም.... ጌልቶጌል... አክቶኤም.... ካልቶኤብ... ኢዛቶናን... ባዜቶናን... ጎቦቶድራ... ጼንቶሎን፣ አፍቶጼን፣ ኢጋቶኤድ... የሀቶራድ... ዮራቶራድ..." ተመሳሳይ አስማቶች፡፡

ልዩነቱ የአልፋ ዕሁፍ፣ "በእሉ አስማቲከ አግርር ሀርዩ ወሀላእትዩ" የሚል መደምደሚያ ስላለውም ነው፡፡ ጥርት ያለ የግዕዝ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም፣ "በእነዚህ አስማቶችህ ጠላቶቼን ያዝልኝ" ማለት ነው፡፡ ሚራኻር የምሁት ፈገግታ

አስማት በተባለው ቃላት ላይ አሳዩ፡፡ ፊደሎቹም መልሰው ያላገጡበት መሰለው፡፡

"እኔ ምልህ ኪራኮስ..." አለ ሚራዥር ዓይኖቹን ከቃላቶቹ ላይ ሳይነቅል፡፡ "...አስማት ላለመሆኑ እንዳች ጥርጥር የለኝም፡፡ ከስንት ደብተራ ጋር ያደኩ ሰው ነኝ፡፡ እንዲህም ብሎ አስማት የለ፡፡ እነዚህ በ'ቶ' የተሞሉ ቃላት የድርጅቱ መግባቢያ ቃላት የነበሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ጥቂት የድርጅቱ ሰዎችም ይግባቡባቸው እንደነበር መጠርጠር ነው፡፡ እነዚህ በአልፋና በአንተ አባት ማስታዎሻዎች ብቻ የተቀመጡ ቃላት ሁሉቱም ወደ ሌሎች ቦታዎች ሲላኩ የድርጅቱ አባል ለመሆናቸው ማረጋገጫ ይሆኑ ዘንድ የሚነበቡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡" በማለት መልሱን የኪራኮስ ዓይኖች ይነግሩት ይመስል ዓይኖቹን ዓይኖቹ ላይ አንከራተታቸው፡፡

ኪራኮስም በበኩሉ ሚራዥርን ለረጅም ደቂቃዎች ሲመለከተው ከቆዩ በኋላ እንደገና ቃላቶቹን ሲያጤን ቆይቶ ቀና አለ፡፡

"ሚራዥር አንድ ነገር ልብ ብለሃል?" አለ ኪራኮስ አስማት መሰሎቹ ቃላት መሀል አንዱ ቃል ላይ ጣቱን ጠቁሞ፡፡ "ይህን... ጌስም... የሚል ቃል ተመልክተሽዋል?... 'ቶ' ፊደል የለበትም፡፡ ምስጢር ቢኖረውስ?"

"...ጌሰም" ማለት በግዕዝ ቋንቋ ነግ ማለት ነው:: ለምን 'ቶ' እንደሲሰበት ግን ለእኔም አልገባኝም::"

"ይህ ብቻ አይደለም:: ጌሰም ከሚለው ቃል ቀጥሎ የተጻፉት ቃላት በጥቁር ሲሆኑ ከእርሱ በፊት ያሉት ግን በቀይ ቀለም ነው:: ይህም ራሱን የቻለ ጉዳይ ነው::"

"ከጌሰም በፊት ያሉት... ኤል ስለሚበዛባቸው ቢሆንስ?... ኤል ማለት ትርጉሙ እግዚአብሔር ማለት ነው:: በመሆኑም የቱም ሰሁና፡ ፀሐፊዎች የቅዱሳንን እና የአምላክን ስም በቀይ መፃፋቸው የተለመደ ነው::"

"ይህን ስትል አንድ ነገር ተገለጠልኝ::"

"ምን?"

"እስኪ ሁሉንም ቃላት 'ቶ' እየገደፍን እንፃፋቸው?" ሚራኘር ከኪሱ ብዕር መዝረጠና በቃላቶቹ መሀል የተሰነቀረውን 'ቶ' እያወጣ እንደገና ፃፋቸው::

"ኤልኤል...ኤላኤል...አዳኤል...ኤማኤል...ኤልራን... ኤልዛር... ጌሰም.... ጌልጌል... አክኤም.... ካልኤብ... ኢዛናን... ባዜናን... ጎበድራ... ጴንሱን፣ አናጼን፣ ኢጋኤድ የሀራድ... ዮራራድ..." የሚሉትን ለብቻ ዕፎ ደጋግሞ አነበባቸው:: ሁለቱም ትርጉም በነፈጓቸው ቃላት ላይ አፍጥጠው ለረጅም ደቂቃዎች ከቆዩ በኋላ ሚራኘር "የቦታ ስም ነው!" ብሎ ሳይታሰበው ጮኸ::

"ምን?!" ኪራኮስ ሰያይፎ የጻፋቸውን ቃላት ተሰንበብንገ ተመለከተ። "በምን መንሻነት?"

"ጌልጌል የሚለው ቃል ጌልጌላ ከሚለው ቃል ተንሻፎ የተጻፈ ነው ብለን እናስብ። በግዕዝ ቋንቋ ቤት፣ ሥፍራ፣ ቦታ የሚል ትርጉም ይሰጣል። አክቶኤም የሚለውንም 'ሱ'ን በ'ቶ' ተክተው የጻፉት ይመስለኛል። አክቶኤም- አክሱም፣ ካልቶኤብ- ካሌብ፣ ኢዛቶናን- ኢዛና፣ ባዜቶናን- ባዜን፣ ጎቦቶድራ- ጎበድራ፣ ጴንቶሌን- ጴንጤሌዮን፣ አፍቶጼን- አፍጼ… ይመስለኛል። እነዚህ ደግሞ በአክሱምና በአክሱም አካባቢ የሚገኙ ቦታዎች ናቸው። ትጠራጠራለህ?"

"እሺ. ኢጋቶኤድ፣ የሀቶራድ፣ ዮራቶራድ… የሚሉት ቃላትስ?"

"እነዚህም ባናውቃቸው እንጂ የቦታ ሥሞች ይመስሉኛል።" አለና ሚራኘር ቀልጠፍ ብሎ ተነሳ።

"ምነው?" አለ ኪራኮስ ግራ ተጋብቶ።

"አሁኑኑ ወደ አክሱም መብረር አለብን።"

"አብደሃል?..."

"ሌላውን እዛው እናጣራዋለን። ለማንኛውም ለማብራራት ጊዜ ስለማይኖረን ጉራን ብቻ አሳምነን ውልቅ ማለት ብቻ ነው። ተከተለኝ።" ሚራኘር ኪራኮስን በተቀመጠበት ጥሎት ወጣ። ኪራኮስ ከመከተል በቀር አማራጭ አልነበረውም።

# ፳፱

## ጣና ሆቴል÷ ባህር ዳር

ዶን ቦናኖ ከአራት ጠባቂዎቹ ጋር ባህር ዳር አውሮፕላን ጣቢያ እንዳረፈ በቀጥታ ያመራው ወደ ጣና ሆቴል ነበር። ኒቆዲሞስና ታዴዎስ ኢያሱም ከአጃቢዎቻቸው ጋር ሆነው በክብር ተቀብለውታል፡፡ ለጉምቱ ጉምቱ ባለ ሥልጣናት አስቀድሞ የዶን ቦናኖ መልካም ስምና ዝና በመሰበኩ በጣና ሆቴል ውስጥ ሞቅ ደመቅ ያለ ግብዣ ተዘጋጅቶለት ነበር የጠበቀው፡፡ በፕሮግራሙ መሠረትም ቅልጥ ባለው የእራት ግብዣ ላይ አንዳንድ ባለሥልጣናት ንግግር አደረጉ፡፡

"እያደገ ለመጣው ኢኮኖሚያችን እመርታ የኮሎምቢያ ባለሃብቶች ኢንቨስት እንዲያደርጉ እናበረታታለን፡፡"

"ኮሎምቢያ እና ኢትዮጵያ ወዳጅነታቸውን በኢንቨስትመንት ያጠናክሩታል፡፡"

"መንግሥት ለአምስት አመቱ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ መሳካት ኢንቨስትመንት አንዱና ዋነኛው የጀርባ አጥንት ነው ብሎ ያምናል፡፡"

እነዚህን የመሳሰሉ ክሊሼ ዲስኩሮች ሲሰሙ አምሽተው... በውስኪና በሻምፓኝ መራጨት ግብግቦው እስኪጠናቀቅ ድረስ ዶን ቦናኖ ሲቅበጠበጥ አመሸ። ፕሮግራሙ ሳይንዛዛ በቶሎ እንዲቋጭ ያደረገው የህሊና ፀሎት አልሰመረም። አሰልቺ የሆነበት ዲስኩር ጆሮውን ሲነድፈው 'ጆሮዬን እኮ አልተከራዩሁትም።' ብሎ ነበር በውስጡ። እያንዳንዱ ባለሥልጣን እየተነሳ የሚናገረው ተመሳሳይ ከመሆኑ የተነሳ የትኛው የትኛውን እንደተናገረ ለማስታወስ እንኳ አይቻልም። ዶን ቦናኖ ትእግስቱን ያስጨረሰውን ዲስኩር 'የበቀቀን መዝሙር' ሲል ሰይሞታል። ኮሎምቢያ ውስጥ ግቢውን የሞሉት በቀቀኖቹ እንደሚያደርጉት አንዱ የአንዱን በቃሉ ያጠናው ያህል እንደ 'አቡነ ዘበሰማያት' ሲደግምበት ሲያመሽ ሊያብድ ጥቂት ነበር የቀረው። 'የማይፈልጉትን መስማት ያህል የሚመር ነገር የለም።' ሲልም በልቡ አፈላሰፈውታል። ቱስካኖውን የሚያጨስበትና ከውስኪው የሚጎነጭበት ጊዜ ያመት ያህል ርቆት ነበር። ታንቲራውና ዲስኩሩ እያዘገመ ተጠናቆ እርሱም በበኩሉ ኢትዮጵያ ውስጥ "ኢንቨስት ሲያደርግ" የላቀ ደስታ እንደሚሰማው ገልፆ ባጭሩ ምፀታዊ ዲስኩሩን እንዳሰማ በካድሬ ቅልጥ ያለ ጭብጨባ ጋዜጣዊ መግለጫው ተጠናቀቀ።

ዶን ቦናኖ በመስላቸት የተፈጠረበትን ድብርት ለማስለቀቅ ያህል ውስኪውን ሁለቴ ከጨለጠ በኋላ ተስካኖውን ለኩሶ ወደ ተያዘለት ክፍል አመራ።

በክፍሉ ውስጥ ጥቂት ረፍት እንዳደረገም ኒቆዲሞስንና ታዴዎስን አስጠርቶ በክፍሉ ውስጥ ያነጋግራቸው ጀምሯል። ኮለኔል ኪሩቤልም የጣቅርን ተራራን ሰብሮ የገባውን ኮማንዶ አዛዥ እንደመሆኑ መጠን አብሮ የስብሰባው ተካፋይ ሆኗል።

ከኒቆዲሞስም ሆነ ከታዴዎስ እንዲሁም ከኮለኔል ኪሩቤል የሰማውን አስደንጋጭ መርዶ ዶን ቦናኖ መቀበል አቅቶት ይደነፋ ጀመር። በተራራው ከርሰ ምድር ውስጥ በተገነባው ዋሻ ውስጥ አንድም የዴርቶጋዳ አባል ያለመገኘቱ ጉዳይ ሊዋጥለት አልቻለም። ካላዩ እንደማያምን ከገለፀ በኋላም በነጋታው ጠዋት ወደ ጣቅርን መሄድ እንደሚፈልግ ተናግሮ ሶስቱንም አሰናበታቸው።

# ፴

## አክሱም ÷ ኢትዮጵያ

በኮረብታዎች እግር ስር ለጥ ባለ ሜዳ ላይ የተቆረቆረችው የአክሱም ከተማ እስከ ፀጥታዋ ላጤናት፣ ከህገ ልቡና እስከ ህገ ኦሪት የተሰበከባት፣ ከሁለት መቶ በላይ ነገሥታት ዘውድ ደፍተው ቅብአ ነገሥት የተቀቡባት፣ ከአረብ እስከ ሩቅ ምስራቅ ሲራራ ነጋዴ የተራኮተባት አትመስልም። ልዩ መለያዋ ፀጥታ ነው። ፀጥታ።

የገናናው አክሱም ስልጣኔ አሻራዎች የሆኑት ሰማይ ጠቀስ ሐውልቶቿ በፀጥታ ይታዘባሉ። የአንድ ወረዳ አነስተኛ ከተማ እንጂ የታላላቆቹ ነገሥታት መናገሻ፣ የሃይማኖት፣ የፍልስፍናና የኪነ ህንፃ መነሻ አትመስልም። ስመ ገናናዋ አክሱም በሐውልቶቿ ስር ኮስምና ከስማለች።

ከስልሳ ሺህ በላይ የማይሆኑ ነዋሪዎች የሚገኙባት ይህቺው አነስተኛ ከተማ ጥንታዊውን ሥልጣኔ ረግጣ በኮረብታዎች ስር ተሰጥታለች። የሳባ መናገሻ፣ የጥንታዊቷ ኢትዮጵያ የስልጣኔ፣ የሥነ ጥበብ፣ የኪነ ጥበብ ጅረት መነሻ፣ የዕላተ

በኢትዮጵያውያን ዘንድ፣ እንደ ሙሴ መንበር በመሆንዋም በኢትዮጵያውያን ዘንድ፣ እንደ

ኢየሩሳሌም፣ ቅድስት ከተማ ተብላ የምትቆለጳጰሰው አክሱም፣ ከኩሽ እስከ ሴም ከሳባ እስከ ያፌት በአዶሊስ በሯ ጎብቶ የተገበያየባትና ዘሩን አዋህዶ የተጋባባት፣ ከሮም እስከ ፋርስ፣ ከባቢሎን እስከ ህንድ የተሸማመተባት፣ ከደንጋይ ወቃሪ እስከ ወርቅ አንጣሪ ከቀራጺ እስከ አናጺ የተጠበበባት አትመስልም። ታሪኳ ነፋስ እንደ ጠረገው ደመና አርቃናን ጥሏት አልፏል። ነገር ግን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አንገቱን ቀና እንዲያደርግ የሚያደርጉት የአርኪዮሎጂ ግኝቶቿና ሐውልቶቿ በፀጥታ ውስጥም ታሪክን ጮክ ብለው እስካሁን በከረብታዎቿ ሥር ይዘምራሉ።

በዚህች ፀጥታ በዋጣት፣ ዝምታ በደበታት ከተማ ውስጥ ሁለት ወዘልውጦች ታይተዋል- ሚራችና ኪራኮስ። ዶር33 በሌሊት አምጥታ በአክሱም ከተማ አቅራቢያ ጥላቸው ነበር የተመለሰችው- ከንግሥተ ሳባ ጥንታዊ ቤተ መንግሥት ፍርስራሽ አቅራቢያ። በረባዳማው ሥፍራ ባገኙት ሸጥ ውስጥ እንደ ድርጭት አድፍጠው ሌሊቱን ካነጉ በኋላ ነበር በጧት ወደ ከተማዋ የገቡት።

ጎብኚ ለመምሰል የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። የፀሐይ መከላከያ ባርኔጣም ደፍተው ካሜራ ባንገታቸው

እንጠልጥለዋል፡፡ ባዘሏቸው እንስተኛ ሻንጣዎችም መቀያየሪያ ልብሶችንና ማስታወሻዎችን ይዘዋል፡፡ የአልፋና የባክስ ማስታወሻዎችም ከያዟቸው ስንቆች ዋነኛዎቹ ናቸው፡፡

ወደ አክሱም ከተማ እንደገቡ በቀጥታ ያመሩት በከተማዋ መሃል ወደሚገኘው ረምሃይ ሆቴል ነበር፡፡ በታላቁ የአክሱም ንጉሥ ረምሃይ ስም በተሰየመው በዚህ ሆቴል ውስጥ አልጋ ከያዙ በኋላ የማለዳ ቁርሳቸውን ተመግበው በቀጣይ ማድረግ ያለባቸውን ማውጠንጠን ያዙ፡፡ በእቅዳቸው መሠረት አካባቢውን በውል የሚያውቅ አስጎብኚ ማፈላለግ ነበረባቸው፡፡ የሆቴሉ እንግዳ ተቀባይ ስልኮችን ከደዋወለ በኋላ አንድ ወጣት አስጎብኚ እየከነፈ ከተፍ አለ፡፡ አስጎብኚው በትህትና እየተቅለሰለሰ ስሙን አስተዋወቃቸው፡፡

"አውአሎም እባላለሁ" አለ በፈገግታ፡፡

እነሱም መልሰው ራሳቸው እንኳ የማያስታውሱትን የሽፋን ስም ነገሩት፡፡

"አውአሎም ስትል አንድ አውአሎም የሚባል ጀግና አስታወስከኝ" አለ ማሪሻር ወሬ ለመቀጠል ያህል፡፡ "አውአሎም የሚባለው ኢትዮጵያዊ ጀግና ኢትዮጵያ የአድዋ ጦርነትን እንድታሸንፍ፣ ያንበሳውን ድርሻ የወሰደ ሰላይ ነው፡፡ አፄ ምኒልክ የጣሊያንን ጦር ስለ ትጥቁና ስለ ስንቁ መረጃ

አደዋ ላይ እስክናነጫጨው የታጠቀውን የጣሊያንን ጦር በመርና በጎራዴ አንበረክከታል::" ካለ በኋላ፣ "ስለዚህ ጀግና ሰምተህ አታውቅም? በስሙ በመጠራትህ ልትኮራ ይገባሃል!" ሲል መልሶ ጨበጠው:: አውአሉምም በደስታ እየተፍለቀለቀ ጠበቅ አድርጎ ጨበጠው::

ከዚህ በኋላ ቡና እየጠጡ የጎበኙትን መርሃ ግብር ነድፈው አክሱምን ለማሰስ ተነሱ:: ሚራኘና ኪራኮስ ከደፉት ባርኔጣ በተጨማሪ ጥቁር መነፅሮች በማድረጋቸው ማንም እንደማይለያቸው ተስፋ አድርገዋል::

አውአሉም ይዞት በመጣው ሚኒባስ ከጫናቸው በኋላ ከተማውን ሰንጥቆ የሚያልፈውን አውራ ጎዳና ይዞ ጉዟቸውን ቀጠሉ:: ከተማውን እንደጨረሱም የመኪናው ግንጭል ዳገታማውን የኢና ሲትማን ጎዳና ይቧጥጥ ጀመር::

ከኮረብታው ግርጌ እንደደረሱም አውአሉም ከመኪናው እንዲወርዱ ካዘዛቸው በኋላ ከአንድ ግድብ ዳር አቆማቸውና ገለፃውን ጀመረ::

"ይህ የንግሥተ ሳባ የመዋኛና የመታጠቢያ ገንዳ ግድብ ነው:: ስፋቱ መቶ ሜትር በሰላሳ አምስት ሜትር ሲሆን አምስት ሜትር ጥልቀት አለው:: ከክርስቶስ ልደት

በፊት በአንድ ሺህ ዓመት ዓለም ከአለት ተጠርቦ የተሠራ ሲሆን ማይ ሺም በመባልም ይታወቃል። የሺም ውሃ ማለት ነው። ስያሜውም ንግሥተ ሳባ ትታጠብበት ስለነበር የተሠጠው ነው። በአራተኛው ክፍለ ዘመን ክርስትና ሲገባ አብርሃና አጽብሃ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠመቁበት ቦታ ነው። እንቀጥል።" ብሎ ወደ መኪናው ተመለሰና ኮረኮንቻማውን አቀበት ተያያዙት።

"ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺህ አመት ቀደም ብሎ ዘመናዊ የመዋኛ ገንዳ ነበረን ነው የምትለኝ?" በማለት ማሬቸር ደገመለት።

"እንዴታ!" አለ አውአሉም ኮራ ብሎ። "እኛ ያልጀመርነው ምን አለና!"

"አሁን የኋለም ጥሬ መሆናችን ያሳዝናል።"

ከዳገቱ መሃል ደግሞ ወረዱና ከአንድ ከድንጋይ ካብ ወደ ተሠራች ደሳሳ ቤት ገቡ። በውስጧ የአክሱም ስልጣኔ እጅግ ባበበት ዘመን የቆመ ሀውልት ይገኛል። ይህ ሀውልት ከክርስቶስ ልደት በኋላ በአራተኛው ክፍለ ዘመን በንጉሡ ኢዛናና ሳይዛና ዘመን የቆመ ነው። የሁለቱ ወንድማማቾች ንግሥና ኢትዮጵያን ሁለት ንግሥታት በአንድ ዘውድ ላይ ያነገሡች ብቸኛዋ ጥንታዊት ሀገር ያደርጓታል። በእርግጥ ከሁለቱ ንግሥታት ኢዛና ጠንከር ያ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል። ይህ ሀውልት በ332 ዓ.ም በታላቁ የአክሱም

ንጉሥ በኢዛና ዘመን የቆመ እንደሆነ በሦስት ቋንቋዎች፣ ማለትም በዕግዝ፣ በሳባ፣ እና በግሪክ ቋንቋዎች ላዩ ላይ እንደ ቆሎ የፈሰሰው ፅሁፍ ያስረዳል። በዚሁ ቁመቱ 2.50 ሜትር ወርዱም 1.ሜትር በሆነው በዕሁፍ የተንቆጠቆጠ ሀውልት ላይ "ኢዛና ንጉሠ አክሱም፣ የሳባ፣ የሂምያር፣ የቤጃ፣ የሲያም፣ የሳልሂን፣ የራይዳንና የመርዌ (የኑስ) ንጉሠ ነገሥት ድል አድራጊው የእግዚአብሔር ልጅ" የሚል የድል ጦማር ሰፍሮበታል። ያመፁ ህዝቦችን፣ ሠራዊቱን ልክ እንዳስገበረና ምርኮኞችንም በጉዞ ወቅት በየቀኑ ሃያ ሁለት ሺህ የስንዴ እንባሻና በቂ የወይን ጠጅ ይሰጧቸው እንደነበር ይገልፃል። "ይህ ኢትዮጵያ ጥንትም የምርኮኛ አያያዟ ለአሁኑ ዘመን አስተሳሰብ መነሻ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው።" ሲል አውአሎም ጨመረላቸው።

አሁን የት እንዳለ የማይታወቁ የወርቅ፣ የብርና የነሀስ ሀውልቶችም ንጉሥ ኢዛና እንዳቆመና ይህኛው የድንጋይ ሐውልት ግን በላዩ ላይ የተዘረዘሩት የግዛት ስሞች ኢትዮጵያ የመንን ጨምሮ ትገዛ እንደነበረ የሚያስረዳ እንደሆነ አስጎብኛቸው ገልፆ ጉዟቸውን ሽቅብ ቀጠሉ። ዳገቱን ጨርሰው ከኮረብታው አናት ላይ እንደወጡም የገናናዎቹ ነገሥታት የአፄ ካሌብና የልጁ የአፄ ገብረ መስቀልን ቤተ መንግሥት አገኙ። በቤተ መንግሥቱ ፍርስራሽ ሥር

ከመሬት በታች ወደተገነባው ዋሻ ይዟቸው ገባ። ይህም ዋሻ የነገሥታቱ ምሥጢራዊ እቃዎች ይቀመጡበት የነበረ እንደሆነ ከነገራቸው በኋላ በዋሻው ግድግዳ ላይ የተቀረፁትን ምልክቶች ይመለከቱ ጀመር። ሚራዥ የአበባ ቅርፅ ያለውንና ባሁኑ ዘመን የቴምፕላሮች ምልክት ተደርጎ የሚወሰደውን የመስቀል ቅርፅ በዋሻው ግድግዳ ላይ ተቀርፆ ሲመለከት

"ተመልከት ኪራኮስ... ይህ የመስቀል ቅርፅ፣ አሁን የቴምፕላሮች ምልክት ይባል እንጂ መነሻው ከእኛ እንደነበር ይህ ጥንታዊ ምስል ማስረጃ ነው።" አለው።

"ይህ ቀርፁ በላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ቅርፃ ቅርፆች ላይ የሚታዩት ምልክቶች እኮ. በውል መጠናት ያለባቸው ምስጢሮች ናቸው። ናዚ የተጠቀመው የስዋስቲካ ምልክት ሳይቀር ከእኛ የተወሰደ ነው። በአሁኑ ዘመን ዓለም ለክፉም ለደግም የሚጠቀሙቸው ምልክቶች ከእኛ ይወሰዱ እንጂ አባቶቻችን ለምን ይጠቀሙቸው እንደነበር የተደረገ ጥናት የለም። የምልክቶችን ምስጢር ቀድመው የተረዱት አባቶቻችን እውቀታቸው በየሥርቻው ወድሟል።" ኪራኮስና ሚራዥ ይህን እየተነጋገሩ ጥንት እንደ ወርቅ አልማዝና ሉል ይቀመጡባቸው የነበሩ የድንጋይ ሳጥኖችን ጎብኝተው እንደገና ኮረብታውን ለቀው ቁልቁል ወረዱ። እኩለ ቀን ሆኖ ስለነበር ወደ ሬምሃይ ሆቴል ተመልሰው ለምሳ ተሰየሙ።

ከሰዓት በኋላም፣ የፈራረሰውን የንግሥት ሳባን ቤተ መንግሥትና እፁብ ድንቅ የሚባል የኪነ ህንፃ ጥበብ ቅሪት ያለበትን የታዕካን ቤተ መንግሥት ከጎበኙ በኋላ ወደ አክሱም ጽዮን ማርያም ዋና ሙዚዬም አመሩ። ከሙሴ ፅላት መቀመጫ መዳረሻ ላይ ባለው ሙዚየም ውስጥም፣ በወርቅ የተለበጡ መፃህፍትን፣ የወርቅ ገርንጥላዎችን፣ የአጋል ቅብ ክርቻዎችን፣ የብር ከበሮዎችን፣ የአንበሳ ምስልና 'ሞ' የሚል ፊደል የተቀረፀባቸው ብርሌዎችን፣ የብርጭቅ ኩስኩስትና ሰሀኖችን፣ የብርጭቅ ዕዋዎችን፣ በወርቅ የተንቆጠቆጡ ካባዎችንና ጫማዎችን፣ የአፄ ዮሐንስን ፀጉር እስከ ወርቅ ወለባው፣ ከቀጭኔ ጭራ የተሠራ ጭራ፣ እና አክሱም የሚል ፅሁፍ የተቀረፀባቸው ደቃቅ እንቁዎችን ጎብኝተው ወጡ። ሚራዥ ደቃቆቹ እንቁዎች የሚፈልውን ቦታ ይጠቁሙት ይመስል ፊቢ ሲመለከታቸው ቆይቶ ነበር የወጣው።

"የሚፈልገውን የማያውቅ ሰው ስለሚፈልገው ነገር..." የሚል ፅሁፍ የት እንዳነበበ ባያስታውስም ይህንኑ ሀሳብ እያሰላሰለ ያክሱም ሥልጣኔ ምልክት ወደ ሆኑት ሀውልቶች ግቢ ገባ። ኪራኮስ አካባቢውንና እስካሁን የጎበኙትን በሙሉ ያስመታከት ቪዲዮ ይቀርፅና ፎቶም ያነሳ ነበር። በዚህ ድርጊቱ አስጎብኛቸው መገረሙን አልደበቀውም።

"ይህን ሁሉ ካሜራህ ይችልልሃል? ለምን ዝም ብለህ ዋና ዋናውን ብቻ አታነሳም?" ነበር ያለው አስጎብኛቸው አውአሉም።

"ጓደኛህም እንዳንተው ነው። የሆነ ያልሆነውን ዝም ብሎ ያነሳል።"

ኪራኮስ በአስገራሚው ንግግር ድንጋጤውን እየታገለ፣ "ያው... ለቦታው ካለን ስሜት የተነሳ ነው። አክሱም ውስጥ ምን የማያስደንቅ ነገር አለ ብለህ ነው? ሳር ቅጠሉ ሁሉ ያሳሳል። ሰዓሊ ብሆን ኖሮ እንደ ተራራ ላይ ተቀምጬ ሁሉንም ስስል ብውል በወደድሁ።" አለው። ኪራኮስ ይህም ሆኖ ፎቶ ማንሳቱንም ሆነ ቪዲዮ መቅረፁን አላቆመም። አስጎብኚዎቻቸውን እየተከተሉ በርካታ ቅርፅ አልባና በቅርፅ ያሸበረቁ ሐውልቶችን ይጎበኙ ጀመር። በጥበብ እየረቀቁ ከትንሽ ተነስተው የሚመጡት ሐውልቶች በመጨረሻ በታላቁ ንጉሥ በረምሃይ ተሠርቶ በወደቀው ሐውልት ያበቃሉ። ሚራዥ ከቆሙት ሐውልቶች ይልቅ ያስደነቀው የወደቀው የረምሃይ ሐውልት ነው። ከሁሉም በተለዬ ሁኔታ ዙሪያውን በልዩ ልዩ ቅርፆችና ምልክቶች ያሸበረቀ ነው። ይህ ከሁሉም ግዙፉና ረጅም የሆነው ሐውልት የአክሱምን የሥልጣኔ ጣሪያ የሚያንፀባርቅና በቁመቱም በግዝፈቱም ከግብፅ ሀውልቶች ጋር ቢቆም የዝሆንና የአይጥ ያህል ልዩነት የሚያሳይ ነው። በላዩ ላይ የተቀረፁት የፎቅ ቅርፆችና ሌሎች ምልክቶች ምን እንደሚጠቁሙ እስካሁን አልተደረሰባቸውም።

"ኪራኮስ... እኔን እንደዚህ ሐውልት የሚያስገርመኝ ነገር የለም።" አለ ሚራዥን ዙሪያውን እየዞረ ፎቶ ሲያነሳና ሲገረም ከቆዩ በኋላ። "በሶስት ሜትር መዞሪያ አንድ መቶ አሥር ሜትር ከፍታ ያለውን ሀውልት ለማቆም የቻሉ ጀግኖች! በኤፍል ታወር የሚኩራሩት ፈረንሳዮች ይህን ሲያዩ

ማፈራቸው የማይቀር ነው መቼስ። ረምሃይ ታላቅ ነው! አምስት መቶ ሃምሳ ቶን የሚመዝነውንና በዓለም ግዙፉን ሐውልት ያቆመ ጀግና! ክብር ይገባዋል! ይህን ግዙፍ ሐውልት ቅድም ከጎበኘነው ከጎቦ ዱራ ተራራ ድረስ በምን አስጭኖ አምጥቶት ይሆን? ስንት ዝሆኖች ተንበርክከው ይሆኑ? ስንት ሰዎች ደቀው ይሆን? በነገራችን ላይ…" አለ ሚራዥር ወድቆ የተሰባበረውን ሐውልቱ በዓይኑ ያቆመው ይመስል እየተመለከተ። "ይህ…የወደቀው የአክሱም ሐውልት ሲቆም የኢትዮጵያ ትንሣኤ ይሆናል የሚል ትንቢትም አለ።"

"እንድ ቀን ሐውልቱስ ኢትዮጵያስ መነሣታቸውና መቆማቸው መች ይቀራል!" ኪራኮስ የሚራዥርን ትክሻ ቸብ ቸብ አደረገው። የሚራዥር ዓይኖች ከወደቀው የአክሱም ሐውልት ላይ እንደ ተተከሉ በእንባ ተሞልተው ነበር። ባለሁለት መግቢያ በሮቹ ወዳሉት ወደ ንጉሥ ረምሃይ መቃብር ገብተው ከአንድ ወጥ ጥቁር አለት ተቀርፆ የተሠራውን ድፍን የድንጋይ ሣጥን እስኪመለከቱ ድረስ የሚራዥር ዓይኖች እንደ ወረዙ ነበር።

# ሰባ

## ባህር ዳር +ኢትዮጵያ

ዶን ቦናዋ ወደ ጣቅርን ተራራ እንደሚያሄድ ተወስኗል። ኮሎኔል ኪናቢል ዶን ቦናዋ ወደ ተራራው መሄዱ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ካስረዳ በኋላ ነበር የተወሰነው።

ኮሎኔል ኪናቢል በዶን ቦናዋ መሄድ ፋንታ የጣቅርንን ተራራ እና በውስጡ ያለውን ውስብስብ ዋሻ የሚያሳይ ቪዲዮ ቀርፆ ጣና ሆቴል ድረስ ካመጣ በኋላ፣ "አንዳንድ ነገሮች እኛ ሳንሄድ ይመጣሉ።" በማለት ነበር በላፕቶፑ ከፍቶ እንዲመለከት የጋበዘው።

ዶን ቦናዋ በጣቅርን ተራራ ውስጥ የሚገኘውን ውስብስብ ዋሻ የሚያሳየውን ቪዲዮ ከተመለከተ በኋላ ባግራሞት ራሱን እየነቀነቀ "በምን ቆፍረውት ነው?!" ሲል ጠየቀ። "ከሜክሲኮ እስከ አሜሪካ ለእፅ ማመላለሻነት ምድር ለምድር በማፊያዎች የተቆፈረውን ዋሻ ነው ያስታወሰኝ።" ሲልም አደነቀ።

"ጦርነቱ ከቀላል ቡድን ጋር እንዳልሆነ ያስገነዝባል።" አለ ኒቆዲሞስ ተንቀሳቃሽ ምስሉን አብሮ ሲመለከት ከቆዩ

በኋላ፡፡ "ቢሆንም እንደ ጃርት በጢስም ቢሆን አፍነን ከተደበቁበት እናስወጣቸዋለን፡፡"

"እንደ እኔ እንደ እኔ እዚህ ተራራ ውስጥ ያሉ አይመስለኝም፡፡ ቀደም ሲል እንደነገራችሁኝ በዚህ ተራራ ላይ ሁለት ጦርነቶችን አድርገዋል፡፡ በድልም ተወጥተዋል፡፡ ነገር ግን እንደ ገና የበሰለ ጦር እንደሚከባቸው ስለሚገነዘቡ መኖሪያቸውን ወደ ሌላ የማይታወቅ ሥፍራ አድርገዋል የሚል ግምት አለኝ፡፡" አለ ዶን ቦናኖ ቪዲዮውን ከተመለከተ በኋላ፡፡

"ከተራራው ወጥተው እንዳልሄዱ መረጃ አለኝ፡፡" አለ ኒቆዲሞስ፡፡ "የአካባቢው ሚሊሻዎች በንቃት የተራራውን ዙሪያ እንዲጠብቁና የሚያዩትን እንቅስቃሴ በሙሉ እንዲጠቁሙ አስደርጌ ነበር፡፡ ነገር ግን ከዚህ ተራራ ወጥቶ የሄደ የሰው መንጋ እንደሌለ አረጋግጠዋል፡፡ በእኔ ግምት ከዚህ ተራራ ጋር የሚያያዝ ሌላ ዋሻ አለበለዚያ ደግሞ እዚሁ ተራራ ውስጥ ካለው ዋሻ ቀጥሎ ያለ ሌላ ዋሻ አላቸው፡፡ በመሆኑም ይህኛውን ዋሻ ዙሪያውን በመናድ የሚቀጥለው ጉረኖአቸው ይገኛል፡፡ የሚል እምነት አለኝ፡፡"

"ታዲያ ይህን ካሰብክ ለምን ጊዜ ታባክናለህ?!" ዶን ቦናኖ አንባረቀ፡፡ "አሁኑኑ ዙሪያውን መናድ ይጀምሩዋ!"

"እንደ ኢሉሚናቲዎችን አዳራሽ ተራራው ተንዶ ስምምነቶችን ጭምር አብረው ቢዳፈኑስ?" ከኪሩቤል ግንባር ላብ ተንቆረዘዘ።

"አንተ ደግሞ ሰሞኑን የምታመጣው ሀሳብ ሁሉ የቦቅቦቃ ሀሳብ ሆኖብኛል!" ኒቆዲሞስ ኪሩቤል ላይ ጮኸበት። "ከመቼ ወዲህ ነው ተራራ እንደ ህንፃ ሲደረመስ ያየኸው? ችግር አለ?!... ቢደረመስም ባይደረመስም፣ ቢናድም ባይናድም ዋናው ዙሪያውን መቆፈር አለብን! አሁኑኑ ይህንኑ እንዲያደርጉ አዝዛቸው!"

ኪሩቤል የወረዛ ግንባሩን በመዳፉ ምዥቶ የሬዲዮ መገናኛውን ወደ አፉ አስጠጋ። "ዙሪያውን ቆፍሩት!" ካለ በኋላ በረጅሙ ተንፍሶ ወጣ። በኪሩቤል መልእክት ግራ የተጋባው ኒቆዲሞስ ኪሩቤል ሲወጣ፣ ኋላውን በዓይኖቹ እንደ ሽንኮራ አገዳ ላጠው።

# ፴፪

## አክሱም + ኢትዮጵያ

የሚራኘር ዓይኖች ድልህ መስለዋል። እንቅልፍ ባይኑ ሳይዞር ነበር ያደረው። ቀኑን ሙሉ በአክሱም ቡሪያ ሲቀርፃቸውና ሲያነሳቸው የዋላቸው ምስሎች ሊሰጡት የቻሉት ፍንጭ የለም። በአልፋ ማስታወሻ ውስጥ ካገኛቸው አስማት መሰል ቃላት ውስጥ የተፈቱት ጥቂቶች ናቸው። "አክቶኤም፣ ካልቶኤብ፣ ኢዛቶናን፣ ጎቦቶድራ፣ የመሳሰሉት ቃላት "በአክሱም፣ በካሌብ፣ በኢዛና እና በጎቦ ድራ" በፊቱም ሲሉ፡ ገና እንደተቆላለፉ ናቸው። "ባዜቶናን እና ጴንቶሉን" የሚሉትን ሁለት ቃላት የፈቷቸው አመሻሽ ላይ ነበር።

ክርስቶስ ከመወለዱ ስምንት አመት ቀደም ብሎ ነግሦ ከክርስቶስ ልደት በኋላም እስከ ዘጠኝ ዓመተ ምህረት ድረስ የቆየውን የንጉሥ ባዜንን መቃብር ቢጎበኙም ያገኙት አንዳች ምልክት አልነበረም። ከአክሱም ወደ አድዋ በሚወስደው ጎዳና በአንድ ኮረብታ ሥር የሚገኘውን የንጉሥ ባዜን መቃብር ሲጎበኙ አንዳች ፍንጭ የሚያገኙ መስሏቸው ነበር።

ሆኖም ወደ መቃብሩ የሚያወርዱትን ከድንጋይ የተፈለፈሉ ደረጃዎች ወርደው አዳራሽ ወደ ሚመስለው ክፍል እንደገቡ ከኮረብታው ሽንጥ ላይ የተከፈቱት አራት መቃብሮች ላይ ቢያፈጡም ግምታቸው መና በመቅረቱ፡ በመቀጠል ያቀኑት ወደ አቡነ ጴንጤሌዎን ገዳም ነበር።

ወደዚህ ከአክሱም ከተማ ሶስት ኪሎ ሜትር ወጣ ብሎ በሚገኘና እንደ ጦር በተቀሰረ ኮረብታ ላይ፣ ቁልቁል ከተማዋን ለመጠበቅ የተሠራ ማማ የሚመስለው የአቡነ ጴንጤሌዎን ገዳም የደረሱት ከመሸ ቢሆንም ያገኙት አንዳች የተለዩ ነገር አልነበረም።

ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ በሆኑት አቡነ ጴንጤሌዎን በአምስተኛው ምዕት አመት ወደ ተሠራው ወደዚህ ገዳም ከአለት ተቆርቁረው በታነፁት ደረጃዎች ወርደው፣ ከድንጋይ የተፈለፈለውን የድንጋይ በርሚልና ንጉሥ ካሌብ ዓለም በቃኝ ብሎ ለልጁ ዙፋኑን አውርሶ መጥቶ በምናኔ ያረፈበትን መቃብር ቢመረምሩም ምንም ያገኙት የተለዩ ነገር አልነበረም። ከዚህ በኋላ የሌሊቱን መንጋት ተጠባብቀው ከአክሱም ከመውጣት በቀር ሌላ ምርጫ እንዳልነበራቸው ተነጋግረው ወደየክፍላቸው ቢያመሩም ሲነጋ ሁለቱም የተገናኙት ባይኖቻቸው እንቅልፍ ሳይዞር ነበር። ቁርሳቸውን

ተመግበው ቡና ከጠጡ በኋላ፣ የአልፋን መዝገበ ዐለት ያገላበጡ ገቡ፡፡ ሌሎች ያልተፈቱ ቃላት አፍጥጠው ይጠብቋቸው ነበር፡፡ "...አፍቶጺን፣ ኢጋቶኢድ፣ የሀቶራድ፣ ዮራቶራድ"

"አፍቶጺን... የሚለው አፍጼ ማለት ሳይሆን አይቀርም፡፡ አፍጼ... ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ ናቸው፡፡" ሚሬኝ ግምቱን አስቀመጠ፡፡

"የእርሳቸው ገዳም የት ነው የሚገኘው?"

"የሀ እንደሆን ከዚህ በፊት ሰምቻለሁ፡፡" አለ ሚሬኝ የሀቶራድ የሚለውንም እየተመለከተ፡፡ "የሀቶራድ የሚለውም የሀ የሚለውን ለመጠቆም ሳይሆን አይቀርም፡፡"

የሆቴል ክፍያቸውን ከከፈሉ በኋላ ወደ አዲግራት የሚሄደውን የህዝብ መጓጓዣ ተሳፍረው ከአክሱም ወጡ፡፡ ሃያ አምስት ኪሎ ሜትሮችን ያህል ተጉዘው የአድዋ ተራሮችን እንዳለፉ ወደ ግራ የሚታጠፍ የኮረኮንች መንገድ እንዳዩ አውቶብሱን አስቁመው ወረዱ፡፡ ለአምስት ወይም ለስድስት ኪሎ ሜትር ያህል የእግር ጉዞ እንዳደረጉም ወደ ጥንታዊቷ የሀ ከተማ ገቡ፡፡

# ፴፫

## ጣና ሆቴል+ባህርዳር

ኒቆዲሞስ የሆቴሉን መናፈሻ አቋርጦ ወደ እሱ የሚገሰግሰውን ሰው አይቶ በደመነፍስ ቱር ብሎ ተነሳ። የሲ.. አይ. ኤው ወኪል ዶናልድ ነው። ከሌሎች ሁለት ሰዎቹ ጋር በፍጥነት እየተራመደ ቀረበ። ምንም ቀጠሮ አልነበራቸውም።

"ምን ትሰራለህ እዚህ ሚስተር ዶናልድ?" ኒቆዲሞስ አፉ ተሳስሮ የጠቀው። አልመሰሰለትም። ይባሱን እሱም ሌላ ጥያቄ አስከተለለት።

"እስካሁን አልያዛችሁትም?"

"ምን ነካህ ሚስተር ዶናልድ እንዲህ በቀላሉ ይሆናል ብለህ ጠብቀህ ነበር?" አለ ኒቆዲሞስ እንዲቀመጡ ወንበር እያሳያቸው።፤ የራሱን ወንበር ስቦም እየተቀመጠ። "የሚታረድ ዶሮ እንኳ ለመያዝ ጥቂት ማስቸገሩ አይቀርም። ያንተ እዚህ መምጣት ግን ገርሞኛል።"

"ምንም የሚያስገርም ነገር የለውም። ያንተ እንቅስቃሴ ምን ላይ እንደደረሰ ለማዎቅም ይሆናል አመጣጤ። የማግዝህ ነገር ካለም እንደዛው።"

"ተነጋግረን ነበር እኮ ሚስተር ዶናልድ፡፡ ሁሉንም በዝርዝር እነግርሃለሁ፡፡ አሁንም የእናንተ እዚህ መቆየት ጥሩ አይደለም፡፡ ለመሆኑ መቼ መጣችሁ?"

"ጠዋት መድረሳችን ነው፡፡ መምጣታችንን ካልወደድከው እንደገና ጠዋት መመለስ እንችላለን፡፡ አሁን እንኳ ስለመሸ ወደ አዲስ አበባ መሄድ አንችልም፡፡"

"መምጣታችሁ አስከፍቶኝ አይደለም፡፡ ሆኖም የእኔ ከእናንተ ጋር መቆየት ጥሩ አይደለም፡፡"

"ይገባኛል፡፡" ካለ በኋላ ዶናልድ ጥቂት አሰብ አድርጎ "ለመሆኑ ምን ላይ ደረሳችሁ?" ብሎ ጠየቀው፡፡

"ተራራውን ሰብረን ገብተን ነበር፡፡ ነገር ግን በዛ የለም፡፡"

"ምን!?" የዶናልድ ዓይኖች ተበለጠጡ፡፡

"ተራራው ውስጥ የለም፡፡"

"የት ደረሱ ነው የምትለኝ?"

"እሱን ለጊዜው ማወቅ አይቻልም፡፡ ወይ ተራራ ቀይረው ይሆናል አልያ እዛው ተራራ ውስጥ ሌላ ዋሻ ቆፍረው ገብተው ይሆናል፡፡ ያም ሆነ ይህ ተራራውን እያስናድኩት ነው፡፡"

"ተራራ እንዴት ነው ልታስንድ የምትችለው? በድማሚት ነው?"

"አይደለም" የዋሻውን ግድግዳዎች እያስናድኩ ነው፡፡ ምናልባት እዛው ተራራ ውስጥ ከሆነ ሌላ ክፍል ይከፈታል፡፡"

"ታዲያ እስካሁን የተገኘ ፍንጭ የለም?"

"የለም፡፡ ዋሻው ሰፊ በመሆኑ በዚህ ፍጥነት ክፍሎቹ በሙሉ ተንደው ሊያልቁ አልቻሉም፡፡ እንዲያውም…" አለና ወደኋላ ዞሮ ተመለከተ- ኒቆዲሞስ ከኮለኔል ኩሩቤል ከራሱ ሰምቶ እንዲያምን ሊጠራለት ዞሮ ቢመለከት ከእርሱ ራቅ ብሎ መናፈሻው ውስጥ ተቀምጦ የነበረበት ወንበር ባዶውን እንደሆነ አየ፡፡

ኒቆዲሞስ ተነስቶ ኪሩቤል ተቀምጦበት ወደ ነበረው አቅጣጫ ሄዶ ዙሪያውን ቢያስስም ሊያየው አልቻለም፡፡ ምናልባት ክፍሉ ውስጥ ገብቶ አርፎ ይሆናል በሚል ወደ ክፍሉ ሄዶም አንኳኳ፡፡ አልተከፈተለትም፡፡ ደጋግሞ እያንኳኳ እያለ ዕዳ፡ ከተፍ አለችና "የሉም እኮ ጌታው፡፡ ቅድም እንደወጡ አልገቡም፡፡" ስትል ማንኳኳቱ አጉል ድካም ብቻ እንደሆነ ነገረችው፡፡ ኒቆዲሞስ ተንቀሳቃሽ ስልኩን አወጣና የኮለኔል ኪሩቤልን ቁጥር ፈልጎ ደወለ፡፡ ነገር ግን "የደወሉላቸው ደንበኛ ቴሌፎን ለጊዜው ጥሪ አይቀበልም፡፡" ከሚል ድምፅ በቀር የኪሩቤል ድምፅ አልተሰማም፡፡

# ፴፬

## የሀ፦ኢትዮጵያ

ማራኸርና ኪራኮስ ወደ ጥንታዊቷ የሀ ከተማ ገብተዋል። ከጭቃ ቤቶች በቀር ለዓይን የሚገባ ቤት የሌለባት መሆኗን ሲያይ "ፊተኞች ኋለኞች ይሆናሉ" የሚለው ብሒል ትዝ አለው - ማራኸርን። "ከሀገር የሀ ከፊደል ሀ ይቀድማሉ።" ሲባል በልጅነቱ የሰማውም ተከተለበት። አቢራ ያጠለቃትን ይህችን ጥንታዊት ከተማ አቋርጠው ሲጓዙ ከክርስቶስ ልደት በፊት ባለው ዘመን ውስጥ የሚገኙ ሳይመስላቸው አልቀረም።

እንደ አርኪዮሎጂስቶችና ታሪክ ፀሐፊዎች ምስክርነት፣ የሀ የተቆረቆረችው ከክርስቶስ ልደት በፊት ስምንት ምዕተ አመታት ቀደም ብሳ ነው። የጥንት ከተማ- የዳአማት ማማ። ከባቢሎን ውድመት በኋላ የኩሽና የሴም ዘሮች እንደገና በዘርና በቋንቋ ተቀላቅለው፣ ዘራቸውን አግአዝያን፣ ቋንቋቸውን ግዕዝ ያደረጉባት የኢትዮጲስ እትብት የተቀበረባት የኢትዮጵያ ሀሁ መሠረት የሀ። የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ።

ሚራኘር በዚህች አፈር ባጠለቀት ከተማ መሀል ቆሞ ዙሪዋን ተመለከተ፡፡

"በታሪክ መርከብ ላይ የምንሳፈፍ መሰለኝ፡፡" አለ በዙሪያዋ የከበቧትን ተራራዎች እየቃኘ፡፡ "በነዚህ ተራራዎች ላይ የዋሊያ አርማ የነበረው የዳዕማት ባንዲራ ሲርገበገብ፣ ዓይኑ ህሊናዬ ወደ ኋላ ሄዶ ተመለከተ፡፡ ዕዝኑ ህሊናዬ ኩሽና ሴም እንደገና አንድ ሆነው በግዕዝ ቋንቋ ሲፈላሰፉ አሰማኝ፡፡ ያሁኗን ኢትዮጵያ ተነስተው ቢመለከቱ፥ ምን ይሉ ይሆን? 'ተቀላቅለን ሳለ እንደገና ለምን ተለያያችሁ? ማንኛችሁ ናችሁ ንፁህ ሴም? ማንኛችሁ ናችሁ ንፁህ ኩሽ?' የሚሉን አይመስልህም ኪራኮስ? ማን ይሆን ታሪካችንን አዳፍኖ ሙጃ የተከለበት? ኢትዮጵያን በሆርኩ ቁጥር የእናቴን ወይም የአባቴን መቃብር አያሉ መቃብሮች ካሉበት መካነ መቃብር ውስጥ እንደሚፈልግ ልጅ የመሰልኩ ይመስለኛል፡፡ መቃብር ላይ መረማመድ!... አንዳቸው ተነስተው ለዚህ በቅጥፈት ታሪኩ ተቀብሮበት ኮምፓሱ እንደጠፋበት መርከብ ያለ አቅጣጫ ለሚንሳፈፈው ትውልድ ሁሉንም ቢነግሩት እንዴት ጥሩ ነበር!"

ሁለቱም ይህንን እየተነጋገሩ የየሀን ከተማ ሰንጥቆ የሚያልፈውንና ማይ መኸለ የሚባለውን ወንዝ ተሻግረው

ወደ ኮረብታው ከወጡ በኋላ ኮረብታው ላይ ተከፍሶ ቁልቁል ከተማዋን የሚመለከተውን ጥንታዊውን የየሀ ሕንፃ ለማየት ገቡ፡፡

በአሥራ ስድስተኛውና በአሥራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን እነ ጀምስ ብሩስና ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ የመሳሰሉ አሳሾች አይተው የተገረሙበት ይህ ጥንታዊ ሕንፃ ከአክሱም በፊት ከመታነፁም በተጨማሪ ህንፃው የተገነባባቸው ግዙፍ ጥርብ ድንጋዮች ያለ አርማታ ተያይዘው ከሶስት ሺህ አመታት በላይ መቆየታቸው ማንንም የሚያስደንቅ ነው፡፡

"የአፍሪካ ካሜሎት" ተብሎ የሚቆለጳጰሰውን የጎንደር ቤተ መንግሥት ሲጎበኝ የተደነቀው ሳያንስ ድንጋዮቹ አንዳች አርማታም ሆነ ብረት ሳያያይዛቸው ይህን ያህል ምዕተ አመታት በመቆየታቸው ማራኘር አዞሮት ይወድቅ ያህል ከህንፃው መሀል ቆሞ "የሀዮራድ!" ሲል ጮኸ፡፡

የትርጉሙ ምንነት ባይገባውም በአስማት መሰሉ፣ ቃላት በመመራት እዚህ በመድረሳቸው ጫፍ ለመድረስ አንድ ቃል ብቻ እንደቀራቸው ተገንዝቧል፡፡ "አፍቶጼን" የሚለውን አፍሄ በማለት ስለተረጎመት "ዮራዶራድ" የሚለው ብቻ ነው የቀራቸው፡፡ አቡነ አፍሄ ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ ሲሆኑ

በስድስተኛ ክፍለ ዘመን ወደዚህ ቦታ በመምጣት ይህን ህንፃ ቤተ መቅደስ አድርገው የክርስትናን ሃይማኖት እንደሰበኩበት ይውቃል። ባሁኑ ጊዜ ግን የአቡነ አፍጼ ቤተ መቅደስ ከዚህ ጥንታዊ ህንፃ ወጥቶ አሥር ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ተገንብቷል፡

የሚቀራቸውን ቃል ትርጉም ህንፃው ይነግራቸው ይመስል ሚሌኖና ኪራኮስ ይደጋግሙት ጀመር።

"ዮራቶራድ"

"ዮራቶራድ"

"ዮራቶራድ"

"ዮራቶራድ"

ምንም ሊገባቸው የሚችል ቃል ወደ አእምሯቸው አልመጣም። ቃሉ ራሱን ይፈታ ይመስል እንደገና ይደጋግሙት ጀመር።

"ዮራቶራድ"

"ዮራቶራድ"

"ዮራቶራድ"

"ዮራቶራድ"

ከቆይታ በኋላ እንደ ደከሙ ያሉ መነኩሴ ወደ እነርሱ ሲመጡ ተመለከቱ።

"ኪራኮስ ዝም በል። እንደ ጅል ስንመሀ... እብዶች መስለናቸው እንዳይሆን። ሰዓቱም እየመሸ ስለሆነ ማደሪያ እናገኝም።" በማለት አንሾካሾከ ሚራዥ እየቀረቡ የመጡትን መነኩሴ እጅ ለመንሳት እርሱም እየቀረበ።

"እንደምን ዋላችሁ?" አሉ መነኩሴው በሚንቀጠቀጥ ድምፅ። "እስትበኚ አጥታችሁ ነው?"

"እግዚአብሔር ይመስገን አባ እንደምን አመሹ? እየመሸ በመሆኑ ማንንም አላገኘንም።" አለ ሚራዥ ለመሳለም እየጎነበሰ።

"ከወዴት መጥታችሁ ነው?" አሉ መነኩሴው ሚራዥን በጥሞና እየተመለከቱ።

"ደፍቱኝ" አለ ሚራዥ ያልሰማ መስሎ በማደናቆር።

ኪራኮስ በተራው መጥቶ ሲሳለም መነኩሴውን ከእግር እስከራሳቸው ተመለከታቸው-- ሚራዥ። ውስጡ ተሸበረበት። ከዚህ ቀደም አይቷቸው የሚያውቅ መሰለው። መልሶ ደግሞ ከሌላ መነኩሴ ጋር የተመሳሰሉበት መሰለው።

መነኩሴው አሳልመዋቸው ሲያበቁ ምርኩዛቸውን ብብታቸው ወሽቀው ተደገፉና ስለ ጥንታዊው ህንፃ ይተርኩላቸው

ጀመር። ስለ ህንጻው በታሪክ የሚያውቁትን ደገሙላቸው እንጂ አዲስ ነገር አልጨመሩላቸውም። ህንጻውን አስጎብኚተዋቸው እንዳበቁ በስተሰሜን ወደሚገኘው ሙዚየም ወሰዷቸው። እግረ መንገዳቸውን ሲያልፉም ከቤተ ክርስቲያኑ ግድግዳ ላይ የተሰጠፉትን የስድስት ዋሊያዎች ምስል አሳይተዋቸው ሲያበቁ "በአርኪዮሎገር ቁፋሮ የተገኙ ናቸው። የዋሊያዎቹ ትርጉም ምን እንደሆነ አልታወቁም፤ ሆኖም የጥንቱ ዳእማት መንግሥት አርማ ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ይገመታል።" ብለው ማሪሻርን ገርመም አድርገው በማዩት ደረጃውን ወርደው ወደ ትንሽዋ ሙዚዩም ወሰዷቸው።

በሙዚየሟ ውስጥ የብራና መፃህፍትንና በአርኪዮሎጂ ቁፋሮ በሳባውያን ቋንቋ ተፅፈው የተገኙ የድንጋይ ላይ ፅሁፎች አሳይተዋቸው ወጡ። ሙዚዬሙን ከቆለፉ በኋላም ሽቅብ በደረጃው ወጡና እነ ማሪሻርን ከኋላቸው ተከተሏቸው።

ማሪሻር ኮረብታው ላይ ካለው ከአቡነ አፍጼ ቤቴክርስቲያን ግርጌ ቆሞ አሻግሮ የሀን የከበቧትን ተራሮች ይለከት ጀመር። የተራሮችን ብዛት ሲመለከት፣ የሀ፣ ፈጣሪ ተራሮችን ፈጥሮ ሲጨርስ የተረፈውን የከመረባት የተራራ ግምጃ ቤት መሰለችው። ተራሮቹ አንዳች ነገር ይነግሩት ይመስል ባይናቹ

ተማፀናቸው፡፡ በስተምዕራብ ባሉት ተራሮች ጠርዝ ላይ የምታስመስለው ጀምበር በመጥለቅ ላይ ናት፡፡

ሚራኝ ቆሞ ግራ በመጋባት ላይ እንዳለ መሰለው እያዘገመ መጡና ምርኩዛቸውን ተደግፈው ፊት ለፊቱ ቆሙና በጥሞና ይመለከቱት ጀመር፡፡

ሚራኝ ትገዘ ሲለው ሙዚዬሙን የጎበኙበትን መክፈል እንደነበረበት ገባውና ከቦርሳው አውጥቶ ጥቂት ያብር ኖቶች ዘረጋላቸው፡፡

"አይ... ተወው ልጄ... እንዴው የት ልታድሩ ነው? መሸቶባችኋ፡፡ ካልሆነ እዚሁ እኔው ዘንድ ብታድሩስ ብዬ ለመጠየቅ ነበር አመጣጤ፡፡ በጨለማ ከምትሰቃዩ የእኔው ጉርብጥብጥ የእንጨት አልጋ ይሻላችኋል፡፡ የሚቆረጠም ጥሬም አይጠፋም፡፡" መነኩሴው አሁንም ዓይኖቻቸውን ካይኑ ላይ አልነቀሉም፡፡ "የእኔ ልጅ?" አሉ አሰከተሉና ድምፃቸውን ለስለስ አድርገው፡፡

"አቤት አባቴ..." አለ ሚራኝ አንድ እርምጃ ወደፊታቸው ቀርቦ፡፡

"ከዚህ በፊት አይቼሀለሁ ልበል?... ከቅድም ጀምሬ ሳስተውልህ የማውቅህ ይመስለኛል፡፡ ተመሳስለህብኝ ይሆን?"

"እኔም እኮ…" አለ ሚራዥ ቅጭም ብሎ እየተመለከታቸው። "እኔም እኮ የት እንደሆነ አጣሁት እንጂ የማውቀዎት ይመስለኛል። እዚህ ነው እንዳልል ከዚህ ቀደም እዚህ ሥፍራ መጥቼ አላውቅም። ወደ መሀል ሀገር ብቅ ብለው ያውቃሉ?"

"እርግጥ ነው። ግን ቆይቷል…" ብለው አንገታቸውን ደፉ።

ሚራዥ ከዳጋ በቀር ሌላ ቦታ መኖሩን ተዋውቆ ስለማያውቅ "ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳምን ያውቁታል?" ሲል በድፍረት ጠየቃቸው።

ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው ብትት ብለው ቀና አሉና፣ "እዛ ነበርክ? አዎ አውቀዋለሁ።" አሉ ይበልጥ ቀረብ ብለው።

"እዛ ማንን ያውቃሉ?" ሲል ጠየቃቸው እያቅማማ።

"አዬ… አሁንስ የማውቀውም የለኝ። አልቀዋል። እንዴት ተረፍክ አንተ?" አሉ ያሰረውን በ'ቶ' ቅርፅ የተሠራ መስቀል በውል እያስተዋሉ።

ሚራዥን አንዳች ስሜት ወረረው።

"እርስዎ እዛ ውስጥ ነበሩ?

“አሁንማ ሙሉ በሙሉ አስታውሼሀለሁ፡፡” አሉ ጥያቄውን ሳይመልሱለት፡፡ “የአባ ዝንበሩ ልጅም አይደለህ?... እግዚአብሔር ታላቅ ነው፡፡ የእሱን ልጅ ሳይ እሱን ያየሁ ነው የመሰለኝ፡፡ እግዚአብሔር ቸር ነው፡፡” አሉና ሚራዥን እቅፈው ይንሰቀሰቁ ጀመር፡፡

ከደቂቃዎች መሳቀስ በኋላ መነኩሴው ሚራዥንና ኪራኮስን ቁልቁለቱ ላይ ወዳለችው ቤታቸው ይዘዋቸው ወረዱ፡፡

ደሳሰዋ ጎጆ ከውጭ እንደምትታየው አይደለችም፡፡ ውስጧ ንፁህ ነው፡፡ ገና ገብተው ከመቀመጣቸው የሽንብራና የስንዴ ንፍሮ አቀረቡላቸው፡፡ ከቅምጫናቸው ቀድተው ውሃ በዋምራ ሰጥተዋቸው ሲያበቁ ከፊት ለፊታቸው ተሰየሙ፡፡

ሚራዥ ምናልባት አያውቁ ይሆናል በማለትም፣ በሌላ በኩልም ምስጢር ያባከነ መስሎት ሲፈራ ሲቸር ከቆዩ በኋላ የመጡበትን ዋና ቁም ነገር ዱብ አደረጉላቸው፡፡ ለጥቂት ደቂቃዎች መነኩሴው አንገታቸውን ደፍተው ሲያሰላስሉ ከቆዩ በኋላ የሚራዥን እጅ ይዘውት ተነሱና ከጎጆዋ አስወጡት፡፡ የኪራኮስ ልብ በፍጥነት እየመታች ተከተላቸው፡፡

መነኩሴው በዝምታ ወደ ዳገቱ ወሰዷቸውና ከማደ ወደሚታዩት ተራሮች ጠቋሚ ጣታቸውን አነሱ፡፡ "ያ ማደ ተራራ ነበ አዶናይ ይባላል፡፡" አሉ ከተራሮች መሀል አንዱን እየጠቆሟቸው፡፡ ተራራው የአንበሳ ቅርፅ አለው፡፡ "የአምላክ ተራራ ማለት ነው፡፡" ካሉ በኋላ ወደሚራዥር ዞሩ፡፡ "ቅድም ስትጠሩት የነበረውን ስም ሰምቼ ነው ወደናንተ የመጣሁት፡፡ ዮራቶራድ...ዮራቶራድ...ዮራቶራድ...ስትሉ ነበር፡፡ ማን ነገራችሁ?" አሉና ፊታቸው ፈካ አለ፡፡

"አባ... ታሪኩ ረጅም ነው፡፡ እዚህ የመጣነው ግብፅ ድረስ ከንተከራተትን በኋላ ነው፡፡ ዳጋ እስጢፋኖስ ውስጥ የዘጉ አንድ አባ ኤስድሮስ የሚባሉ አባት ስንጠይቅ ወደዚህ ቦታ በተደጋጋሚ ይላክ የነበረው አልፋ የሚባል ሰው እንደነበረ ነገሩን፡፡ አልፋ ግን ከዳጋው ፍንዳታ በኋላ ወደ ግብፅ በመሄድ አስቄጥስ በረሃ ውስጥ ስመመነን መጓዙን ነገሩን፡፡ እኛ አስቄጥስ በረሃ ድረስ ሄደን በእንጦንስ ገዳም አልፋን ስንጠይቅ ግን በገዳሙ ውስጥ ያገኘናቸው አንድ አባት አልፋ በበረሃው ውስጥ በእባብ ይሁን በጊንጥ ተነድፎ ሞቶ እንደተገኘ አረዱን፡፡ በእጁ የተገኘውን የፀሎት መፅሀፉንም ሰጡን፡፡" ሚራዥር ከቦርሳው የአልፋን መዝገበ ፀሎት አውጥቶ አሳያቸውና ቀጠለ፡፡ መነኩሴውን የሀዘን ጦር ተተክለባቸው፡፡ "አልፋ መዝገበ ፀሎት ውስጥ ያገኘናቸውን ቃላት ከአክሱም ጀምረን እየፈታን እነሆ እዚህ ደርሰናል፡፡ የቀረንና መፍታት

ያልቻልነው ቃል ቅድም ስንደጋገመው የነበረው ነው... ዮራቶራድ::"

"የቃሉን ትርጉም ታውቁታላችሁ?" አሉ ሀዘናቸውን እየታገሉ:: አቀርቅረው ለደቂቃዎች ቆዩ::

"አናውቀውም አባታችን"

"በጥንታዊው የሳባውያን ልሳን፣ የዮራቶራድ ማለት ተቀላቀል ማለት ነው:: ይህ ቦታ ከብዙ ዘመናት በፊት የኩሽና የሴም ዘሮች ተቀላቅለው አንድ በመሆን የኢትዮጵያን ስልጣኔ የወጠኑበት በመሆኑ፣ ባሁኑ ጊዜ ግን በማይረባ ስብከት በጎሳና በጎጥ የተለያየውን ኢትዮጵያዊ ባንድነት ሰብስበን ኢትዮጵያን ከወደቀችበት ለማንሳት ካለን ህልም በመነሳት ነው ስያሜውን የመረጥነው:: መሸ እንጂ ወደዛው እወስዳችሁ ነበር:: ምናለ ቀደም ብትሉ::" አሉ መነኩሴው ወደ ጎቦ አደናይ አሻግረው እየተመለከቱ:: ሲታገላቸው የቆየውን ዕንባ ዘረገፉት::

"እንዲያው ካላስቸገርነዎት..." አለ ኪራኮስ አሻግሮ የአንበሳ ቅርፅ ያለውን ተራራ በጉጉት እየመለከተ::

"ለነገሩማ በቀን ከመሄድ አሁን ይሻላል:: እኔም ብሆን ምሽቱን ጠብቄ እንጂ በቀን ወደዛ ሄጄ አላውቅም:: መንገድ ስለመታችሁ እረፍት ብታደርጉ ብዬ እንጂ በቀን መሄድማ

እንደማንችል አውቃለሁ።" አሉ መነኩሴው ሁለቱንም አፈራርቀው እየተመለከቱ።

"ግዴለም ስለ እኛ አያስቡ። ብዙም ድካም የለብንም። ቢሆንም እዚህ እንደር ብንል እንኳ ልባችን አብሮን አያድርም።" ሚራዥ ተቁነጠነጠ።

መነኩሴው እንደገና ወርደው ጎጇቸውን ቆልፈው ተመለሱና ወደ ሰሜን አቅጣጫ የምትወስደውን ቀጭን መንገድ ይዘው መሯቸው። የሚራዥና የኪራኮስ ልቦች አታሟቸውን መደለቅ ጀምረዋል።

# ፴፫

## ዳጋ÷ጣና ሐይቅ

ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ደገማ፣ አንዷት ፈጣን ጀልባ የጣና ሐይቅን እየሰነጠቀች መጥታ ከዳጋ እስጢፋኖስ ደሴት ስትደርስ ሞተሯን አቀዘቀዘች፡፡ እንደ ጀት እያበረረ ካመጣት ካፒቴን ሌላ አንድ ሰው ከኋላ ተቀምጧል፡፡ ጥቁር ካፖርት ደርቦ ጥቁር ባርኔጣ ደፍቷል፡፡ በስተደቡብ ካለው ድብቅ ወደብ እንዳደረሰች ካፖርት የደረበው ሰውዬ በፍጥነት ወረደ፡፡ ጀልባዋን እስከ ካፒቴኗ እዛው ትቶ፣ ቀጭኗን መንገድ ይዞ በፍጥነት እየተራመደ ወደ አንድ ሸጥ ገባ፡፡ የተለመደውን የይለፍ ቃል እንደተናገረ አንድ የብረት በር በዝግታ ተከፈተለት፡፡ ወደ ውስጥ እንደዘለቀም በሩ በፍጥነት ተከረቸመ፡፡ ይህ በር በዳጋ ደሴት የደቡብ በር እየተባለ የሚጠራው ነው፡፡ ወደ ውስጥ እንደዘለቀ ሌላ አለም ጠበቀው፡፡ ፈራርሶ የነበረው በዳጋ ከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኘው ከተማ ቀድሞ ወደ ነበረበት ባይመለስም ትንሽ ነፍስ ዘርቷል፡፡ ከጣቅርን ተራራ ሲሰደዱ ያመጧቸው ድምፅ አልባ ጀነሬተሮች የዋሻውን ውስጣዊ ክፍል በብርሃን አንቆጥቁጠውታል፡፡

"ኪሩቤል እንኳን ደህና መጣህ!" ብሎ ሰዎች እየመጡ ከበቡት።

ኮሎኔል ኪሩቤል ቃርሚያ ወጥታ እንደተመለሰች አሞሬ ሚጨፌቅሯም እንደሚከቧት በሁሪያው ለተኮለኮሉት ሰዎች የሚነግራቸውን መርዶ ከምን መጀመር እንዳለበት ግራ እንደገባው ጌራ እና ሻጊዝ ከሩቅ ኮሪደሩን አቋርጠው ሲመጡ ተመለከተ። የያዘው መረጃ አዲስ ባይሆንም ለብዙሃኑ ከመናገር ለዋና ዋናዎቹ ብቻ ማቀበል እንዳለበት እነሱን ከሩቅ ሲያይ ተገለጠለት። እነሱ ወደ እርሱ እየተራመዱ እያለ እሱ ራሱ ወደነሱ አመራ።

ጌራ፣ ሻጊዝና ኪሩቤል ከብዙሃኑ ነጠል ብለው ሲወያዩ ቆዩና በፍጥነት ዶር33 ወዳለችበት ክፍል ሄደው ገቡ። ምን እንደነገራቸው ባለመታወቁ ሁሉም በያለበት ደንግጦ የሚሆነውን መጠባበቅ ጀመረ። ወደ ዶር33 እንደገቡ ሶስቱም ስክሪኑ ላይ አፈጠጡ። በሚራሻና በኪራኮስ ላይ የተገጠሙት ካሜራዎች ስራቸውን አላቆሙም። ሆኖም ጨለማ በመሆኑ ከምን ውስጥ እንዳሉ ለማየት አልቻሉም ጭልጭል የሚል መብራት ብቻ ከፊት ለፊታቸው ይታያል። በጉዞ ላይ እንዳሉ ቢያምኑም የት እንዳሉ ለማወቅ ግን አልተቻለም።

ጌራ ስክሪኑ ላይ ያሉትን የመረጃ ቁልፎች ሲነካካ ቆይቶ አቅጣጫ ጠቋሚው ገፅ ላይ አንዳንድ ፅሁፎች መምጣት ጀመሩ። በአቅጣጫ ጠቋሚው የመረጃ ገፅ ላይ 14.2833 ዲግሪ ሰሜን, 39.0167 ዲግሪ ምሥራቅ የሚል ቁጥር መጣ። ያሉበትን ትክክለኛ ቦታ የሚገልፅ እንደሆነ በማመናቸው በፍጥነት ወደዛው ለመብረር ወሰኑ።

ጌራ የዶር33ን ሞተር ካነቃቃ በኋላ ከደሴቱ ወጥታ ሐይቁን እየሰነጠቀች ካከበከበች በኋላ ወደ ሰማይ አፍንጫዋን ቀሰረች።

* * *

ዶር33 የሰሜን ኢትዮጵያን ሰማይ እየሰነጠቀች መጥታ የሀ ስትደርስ ሥጋ እንዳዩ አሞራ ቁልቁል ማንዣበብ ቀጠለች። የመረጃ ገፅ ቁጥሮች በየደቂቃው እየተለዋጡ ያንበሳ ቅርፅ ካለው ተራራ ላይ ቆሙ። ዶር33 ከተራራው ወገብ ላይ ከሚገኘው ረባዳ ቦታ ላይ ምቹ ሥፍራ ፈልጋ አረፈች።

* * *

ሚራዥና ኪራኮስ መነኩሴውን ተከትለው ወደ ተራራው እንደወጡ በስተሰሜን በኩል ካዞሯቸው በኋላ ተከፍቶ ወደ ጠቢቃቸው ዋሻ ይዘዋቸው ገቡ።

በዋሻው ውስጥ ጥቅጥቅ ያለውን ጨሊማ በያዟቸው የእጅ ባትሪዎች እየገሰሱ ዙሪያውን ይመለከቱ ጀመር። ... ዋሻው በጅምር እንደቀረ ግልፅ ነበር።

"ልጆቼ..." አሉ መነኩሴው ቆም አሉና። "በዲጋ እንዳደረግነው በዚህም ሞክረን ነበር። ሆኖም ከዲጋው ፍንዳታ በኋላ ቆሟል። ይህንን ቦታ ከምናውቀው ሰዎች ውስጥ ከፍንዳታው የተረፍነው እኔና አልፋ ነበርን። በአመታዊዉ ስብሰባ ምክንያት በዚህ ዋሻ ቁፋሮ ላይ ተሰማርተን ከነበርነው ውስጥ እኔና አልፋ ስንቀር ሲሉቹ ሄደው ነበር። የራቶራዴ ብለን የሰየምነው ዘመቻ ከጥቂት አባላት በቀር ማንም እንዳያውቅ ተደርጎ በምስጢር የተያዘበት ምክንያት ምናልባት በውስጣችን ሰርጎ ገቦች ይኖሩ ይሆናል በሚል ጥርጣሬ ነበር። በጅምር ቀረ እንጂ ህልማችን ታላቅ ነበር።" ብለው አቀረቀሩ።

ሚራኛርና ኪራኮስም ቅስማቸው ተሰብሮ አንገታቸውን ደፉ። ሚራኛር፣ በግብፅ በረሃ አሳሩን ያበላው ፍለጋ በዚህ በመደምደሙ ደንዝዞ ቀረ። እንኳንስ ያን ሁሉ አባል ቀርቶ ጥቂት ፍየሎችን እንኳ ማስጠለል የማይችል ጉረኖ ውስጥ ራሱን ሲያገኘው በህልሙ እንጂ በእውኑ አልመስልህ አለው።

ሶስቱም በትካዜ ተውጠው ባቀረቀሩበት ቅፅበት ሌላ ሶስት ሰዎች ከወደታች የሚራኙርን ስም እየጠሩ መጡ። ሚራኙ እነማን እንደሆኑ በድምፃቸው ስለለያቸው በእጁ ባትሪው ምልክት ሰጣቸው። ሶስቱም እንደደረሱ የሆነውን ሁሉ በመረዳታቸው ቁዘማውን ተቀላቀሉ።

በዚህ መሀል ኪሩቤል፣ "ጎበዝ… የሆነው ሆኗል። ሁሉንም ከእኛ በፊት የነበሩት ሠርተው እንዲሰጡን መጠበቅ አልነበረብንም። እነሱ የጀመሩትን የመጨረስ ሸክም ሁሉ በእኛ ትክሻ ላይ መውደቁን መረዳት አለብን። ነገር ግን አሁን ያላንበት ሁኔታ ለመቆፈርም ለመቆዘምም የሚያበቃ አይደለም። ጠላቶቻችን ወደ ጣቅርን ተራራ ገብተው የዋሻውን ግድግዳ ዙሪያ መቆፈር ጀምረዋል። ወደ ዱጋ የሚወስደውን የምድር ውስጥ መንገድ ለመክፈት ምናልባት የሚቀራቸው ጊዜ ያለ አይመስለኝም። የእኛ አፋጣኝ ውሳኔ ያስፈልጋል። እኔም በቶሎ መመለስ አለብኝ። ኒቆዲሞስ ከጠረጠረኝ ነገሩ ሁሉ ተበለሻሸ ማለት ነው።" አለና ሁሉንም አፈራርቆ ይመለከት ጀመር።

"መሸሸ ወይም መከላከል ነዋ! ሌላ ምን አማራጭ አለን?" አለ ጌራ አንድ ድንጋይ ላይ እየተቀመጠ።

"ለመሸሽም ሆነ ለመከላከል ጊዜ የለንም። ይልቁንስ አንድ ሀሳብ አለኝ።" አለና ሚራዥ ኮለኔል ኪሩቤልን ጎትቶ ከዋሻው አወጣውና ጥቂት ሲንሾካሾኩ ቆይተው ተመለሱ።

ሚራዥና ኮለኔል ኩሩቤል ከተወያዩ በኋላ ይዘውት የመጡትን ሀሳብ ለቀሪዎቹ ሲያቀርቡላቸው ሁሉም በሚራዥ አደገኛ ውስኔ ክው አሉ። ሚራዥ ግን ፊርጠም ብሎ ተከራከረ። በሀሳቡ ኮለኔል ኪሩቤልም በመስማማቱ ምንም እንኳ ውሳኔው አደገኛ እንደሆነ ቢያምኑበትም ቀስ በቀስ ግን እየተቀበሉት መጡ። በመጨረሻም ዶር33 ከጎቦ አዶናይ ተራራ ተነስታ ወደ ጣና ገሰገሰች።

ዶር33 ዳጋ እስጢፋኖስ ደርሳ ለዋና ዋናዎቹ አባላት የሚራዥ ሀሳብ ቀርቦ አያሌ ክርክር ተደርጎ እስኪወሰን ድረስ መንፈቀ ሌሊት አልፎ ነበር።

# ፴፯

## ጣና ሆቴል÷ባህር ዳር

ኮለኔል ኪሩቤል ወደ ጣና ሆቴል እንደገባ በቀጥታ ያመራው ወደ ኒቆዴሞስ ክፍል ነበር። መንፈቀ ሌሊት ቢያልፍም ኒቆዲሞስ አልተኛም ነበር። ውስኪውን ሲጨልጥ ደረሰበት። "የት ጠፋህ?" አለ ኒቆዲሞስ በሩን ከመክፈቱ። "መቼም እንደልማድህ መጠጥ ቤቶችን ለማዳረስ ሄደህ መሆን አለበት።"

"ይቁንስ ጨብጠኝ!" አለ ኪሩቤል እጁን በኩራት እየሰጠው። "የምስራች!"

"ሰክረህ ነው?" አለ ኒቆዲሞስ በኪሩቤል ከመጠን ያለፈ ደስታ ግራ ተጋብቶ። "ለማንኛውም ምስር ብላ፣ ለመሆኑ ምን ተገኘ?"

"እንዲህ በቀላሉ የሚነገር የምስራች እንዳይመስልህ ከዶን ቦናኖ ጋር ውስኪ ካላወረዳችሁልኝ አልናገርም።"

"ኡበደሀል? እኩለ ሌሊት እኮ አልፏል። በዚህ ደረቅ ሌሊት ቦናኖን የሚያስቀሰቅስ ነገር ምን ተገኘ?"

"በእኔ ይሁንብህ፡፡ ይህን የምስራች ለሁላታችሁም ሳልናገር እንቅልፍ አይወስደኝም፡፡ የጠጣሁ መስሎህ ከሆነ ተሳስተሃል፡፡ አፌን ማሽተት ትችላለህ፡፡"

"የምርህን ነው?"

"ሙት! ኒቆዲሞስ! እመነኝ ይህን ደስታ ሳትሰማ የሚነጋልህ አይመስለኝም፡፡"

ሁለቱም ተያይዘው ወደ ዶን ቦናኖ ክፍል ሄዱ፡፡ እሱም አልተኛም ነበር፡፡ ከአንድ ጠባቂው ጋር ውስኪውን እየጨለጠ አገኙት፡፡

"ምነው? እንቅልፍ አልወስዳችሁ አለ?" ሲል ጠየቃቸው ሁለቱንም አፈራርቆ እየተመለከተ፡፡

"አይደለም" አለ ኪሩቤል ጥርሶቹን ብልጭ አድርጎ፡፡ "መልካም ዜና ይዘን መምጣታችን ነው፡፡"

"ተገኘ?" አለ ዶን ቦናኖ በደስታ ከመቀመጫው ተነስቶ፡፡

"ውስኪ ካልወረደልኝ አልናገርም እኮ ነው የሚለው፡፡ አንዳንዴ እንደ ህፃን ያደርገዋል፡፡" አለ ኒቆዲሞስ ለታዴዎስ ስልክ እየደወለ፡፡

"ለውስኪ ነው? ምን ችግር አለው?" ዶን ቦናኖ አለፍ ብሎ ያለውን ጠረጴዛ በአገጩ አመለከተው፡፡ "እምጣና ክፈተው!"

ኮሎኔል ኪሩቤል ውስኪውን እየከፈተ እያለ ታዴዎስ ከተፍ አለ፡፡ ለሁሉም ከቀዳላቸው በኋላ፣ "እንዴ ብርጭቋችንን ከፍ እናድርግ!" ሁሉም ተከተሉት፡፡ ዓይኖቹን ጨፍኖ በቁሙ አንዴ ከጨለጠ በኋላ ወንበር ስቦ ተቀመጠ፡፡ በጉጉት ዓይኖቻቸውን እንደተከሉበት ሌሎቹም ተከትለውት ተቀመጡ፡፡

"ሚራዥ ተይዟል!" ሲል ኮሎኔል ኪሩቤል ጮኸ፡፡

"አ?!" ሁሉም አፋቸውን ከፈቱ፡፡

"አትቀልድ!" አለ ኒቆዲሞስ "አብደህ ወይም ሰክረህ መሆን አለበት፡፡"

እሱ ግን ሚራዥ እንዴትና በማን የት እንደተያዘ ያዘጋጀውን ትረካ ቀጠለላቸው፡፡

"ሚራዥ ከተራራው ጦርነት በኋላ ራሱን ደብቆ እዚሁ ባህር ዳር ውስጥ ቀበሌ አሥራ ሶስት አካባቢ ይኖር ነበር፡፡ አንድ የእኛ ሰው ጥቆማ ከደረሰው ቀን ጀምሮ መረቡን ዘርግቶ ሲከታተለው ቆይቶ ዛሬ ማታ መረቡ ዓሣውን ይዞለት ነበር፡፡"

"አመለጠ እንዳትል ብቻ፡፡" ኒቆዲሞስ አሰገገ፡፡

"ባለመረቡ ሚራዥን እንደያዘ ቀጥታ የደወለው ለእኔ ነበር፡፡ ነገሩን ለጊዜው በምስጢር እንድይዘውና ጠቀም ያለ

ጉርሻ እንደሚፈልግ አለበለዚያ ግን ፍንክች እንደማይል ይነግረኛል። ስልኬን እንድዘጋና ከማንም ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንዳላደርግም ያስጠነቅቀኛል። እኔም ያለኝን በማድረግ ወደ ቀጠረኝ ቦታ ሄጄ መደራደር ቀጠልኩ።"

"ለመሆኑ ምን ያህል ጠየቀ?"

"ከሚገኘው ጥቅም አንፃር ሲታይ ቀላል ነው፤ ሶስት ሚሊዮን ብር።"

"ያከፋፈሉ ሁኔታስ?" አለ ኒቆዲሞስ የጠራውን ገንዘብ ከቁብ ሳይቆጥር። "ለመሆኑ ሚራዥን በዓይንህ በብረቱ አየኸው?...ወይስ..ዝም ብሎ እየቀለደብህ ነው?"

"በትክክል አይቸዋለሁ። ሆኖም በአካል አይደለም፤ በቪዲዮ ነው። ሚራዥ ራሱ በቪዲዮ ባስተላለፈው መልእክት፣ በሞራሉና በአካሉ ላይ እንዳችም ጥቃት አይደረስበት እንጂ የስጠመውን መርከብ ካርታም ሆነ ኤክስካቫተር ዶዘሩን እንደሚሰጥ ገልጧል።"

"ኪሩቤል!" አለ ታዴዎስ። "እየቃዠህ መሆን አለበት። ያ ሞገደኛ ሰው ይህን ይላል ብዬ እኔ በበኩሌ አላምንም። ቶርች ቢደረግ እንኳ እንዲህ እንደማይል ሚራዥን ጠንቅቄ አውቀዋለሁ።"

"እንዳይመስልህ።" አለ ኪሩቤል። "ከተራራው ጦርነት በኋላ ድርጅቱ ተበትኗል። የድርጅቱ አባላትም ወደ ተለያዩ ሀገራት ገብተዋል። ከጥቂቶቹ ጋር ድርጅቱን ለማቆየት

ተደራድሮ እንደነበር ገልፆ ሁሉም በድርጅቱ ተስፋ በመቁረጥ የየራሳቸውን ህይወት ለመምራት የድርጅቱን ንብረት ተከፋፍለው መፈርጠጣቸውን ተናገሯል። እንዲያውም የድርጅቱ አባላት ራሳቸው በእጁ የሚገኘውን ካርታ ነጥቀው የሰጠመውን መርከብ አውጥቶ ለመቀራመት እሱን እያሳደዱት እንደሆነና ራሱን ለማዳን ያልተንከራተተበት ሥፍራ እንደሌለ ገልፆ እቅም ያለውና እሱን መታደግ የሚችል፣ የራሱን ድርሻም የሚሰጠው አካል ካገኘ ካርታውንም ሆነ ዶዞሩን እንደሚሰጥ የገለፀበት የቪዲዮ ክር በእጁ ይገኛል። ሁሉንም ተመልከቱና ተረዱት።" አለና የተጠቀለለ ቪ.ሲ.ዲ. ከኪሱ መዥርጦ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ።

ኒቆዲሞስ ተጣድፎ ላፕቶፑን አመጣና ቪ.ሲ.ዲውን ዶለው። ሁሉም ሚራዥን ለማዬትና ንግግሩንም ለመስማት አሰፈሰፉ። ቪ.ሲ.ዲውን አይተው እንዳበቁ ኒቆዲሞስ ወደ ክፍሉ ሄዶ የቼክ ደብተር ይዞ ተመለሰ። በሶስት ቼኮች ላይ ፊርማውንና የተጠራውን ገንዘብ ያለ አንዳች ማቅማማት አስቀመጠ።

"ስሙን ራስህ ፃፈው!" ብሎ ለኪሩቤል አቀበለው።

"ካሽ በልበት"አለው ኪሩቤል ቼኩን መልሶ እየገፋለት።

ክሊኔል ኪሩቤል ቼኮቹን ኪሱ ከተተና የተዘጋ ስልኩን ከፍቶ ቁጥሮች መነካካት ጀመረ፡፡ ጥሪው ሲንጫረር ከቆዩ በኋላ አንድ ጎርነን ያለ ድምፅ ተሰማ፡፡

"ተስማምቻለሁ፡፡ ቼኮቹ ተፈርመዋል፡፡ ዓሣውን እንዴት ነው የምንቀባበለው?" ኪሩቤል ፈጠን ብሎ ነገረው፡፡

ጎርነን ያለው ድምፅ ቼኮቹን የሚቀበላቸው ሰው የት እንዳለ ጠቆማቸው፡፡ አስከትሎም ዓሣውን የሚያስረክባቸው በምን መንገድ እንደሆነ ገለጻላቸው፡፡

# ፴፯

## ጣና ሓይቅ÷ ኢትዮጵያ

ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኗል፡፡ ለእነ ኒቆዲሞስ ቀኑ በቀላሉ
አልመሸላቸውም ነበር፡፡ በእቅዱ መሠረት፣ የምሽቱ መግፋት
ተጠብቆ ጉዞዉ ተጀምሯል፡፡ ስምንት ፈጣን ጀልባዎች ወደ
ሰሜናዊ ጣና በመክነፍ ላይ ናቸው፡፡ ከኋላና ከፊት ያሉት
ጀልባዎች የተራራውን ውስጥ ቀፋሮ አቁመው የተመለሱትን
ኮማንዶዎች ጭነዋል፡፡ ከመሀል ያለችው ጀልባ ደግሞ ኮሎኔል
ኪሩቤልን፣ ኒቆዲሞስን፣ ታደዎስን፣ ዶን ቦናኖን እና ተላልፎ
የተሰጠውን ሚራኘን ጭናለች፡፡ ንግግር የለም፡፡

ከዳጋ ደሴት በስተምዕራብ አቅጣጫ እንደደረሱ ስምንቱም ወደ
ወደቡ ሳይጠጉ ሞተር አቀዝቅዘው እንዲቆሙ ተደረገ፡፡
ሚራኘ፣ በሁለት ፈርጣማ ፈርጣማ ኮማንዶዎች ታጅቦ
እንዲወርድ ከተደረገ በኋላ ኤክስካቫተር ዶዘሩ ወደ
ተቀመጠበት ቦታ አመራ፡፡ ሁሉም ውሃ የማያስገባ የዋና
ልብስ እስከ መነፅሩና ኦክስጅን መስጫው ለብሰዋል፡፡ በሁለቱ
ጀልባዎች ላይ የሚንቦገቦጉት ፓውዛ መብራቶች ሚራኘ ላይ
በማብራት ላይ ናቸው፡፡ አንዳች ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ

ቢያሳይ ምላሹ እንዲሰበ የተነገራቸው አልሞ ተኳሾቹ በሁለቱም ጀልባዎች ላይ አነጣጥረውበታል።

ማራኝ ጠልቀው እንዲዋኙ ሁለቱንም ኮማንዶዎች የእጅ ምልክት ሰጥቷቸው ወደ ሐይቁ ጠለቀ። ሁለቱም በግራና በቀኝ አጅበውት እኩል ጠለቁ። ኤክስካቫተር ዶዘሩን ከፍቶ እንደገባ ሞተሩን ቀስቅሶ ለደቂቃዎች ሲያሞቀው ከቆዬ በኋላ፣ ጀልባ በላዩ ላይ ወጥቶ አደጋ እንዳያደርስበትና የደረሰበትንም ቦታ ጠቋሚ የሆነውን አንቴና ወደ ላይ እንዲወጣ ካደረገ በኋላ በካርታው መሪነት መርከቡ ወደ ሰጠመበት ቦታ ጎዞው ተጀመረ። ስምንቱ ጀልባዎችም ፍጥነታቸውን ቀንሰው ውስጥ ለውስጥ የሚጓዘውን አክስካቫተር ዶዘር ግራና ቀኝ አጅበው ይጓዙ ጀመር።

እኩለ ሌሊት ሊሆን አቅራቢያ ወደ አንድ ቋጥኝ የተከመረበት ቦታ ደረሱ። አሞራ ብቻ ሰፍሮበት የሚውል የድንጋይ ክምር ደሴት ነው። ከዚህ የቋጥኝ ክምር በስተምስራቅ በኩል በአምስት ሜትር ራዲዩስ ውስጥ መርከቡ እንደሰጠመ ካርታው ያመለክታል። ማራኝ በአምስት ሜትር ራዲዩስ ውስጥ ያለውን ደለል በኤክስካባተር ዶዘሩ መዳፍ ይዝቅ ጀመር። ሌሊቱ ከመንጋቱ በፊት ሁሉንም ነገር ለማጠናቀቅ፣

ዙሪያውን ጋውዞቸውን አብርተው በቆሙት ጀልባዎች ላይ የተቀመጡት ሁሉ በመቁነጥነጥ ላይ ናቸው።

ለሰዓታት ከወሰደው ቁፋሮና ደለል መዛቅ በኋላ 'ኳ' የሚል ድምፅ ተሰማ። ማሪሻየ የኤክስካቫተር ዶዘሩን ረጂም መብራት ለቆ ለማየት ሞከረ። የዛገ ብረት መሰል ነገር እንደሆነ አስተዋለ። ደለል መዛቁን ሲቀጥል የሰጠመው መርከብ ሙሉ በሙሉ መገለጥ ጀመረ። በላዩ ላይ የተጫኑትን ቋንጃች እየገለባበጠ ወደ ሐይቁ ጨመራቸው። ሐይቁ ከጎሽ በኋላ እየቆየ ድፍርስርሱ እየጠራ መጣ። ከዚህ በኋላ በኤክስካቫተር ዶዘሩ ጥፍር የመርከቡን የላይኛውን ክፍል ይቧጥጥ ጀመር። ዙሪያውን ከበሳው በኋላ የመርከቡ የላይኛው ጣራ ተከፈተ። በዚሁ ቅፅበት እልልታና ፉጨት ከጀልባዎቹ ላይ የሰማ መሰለው።

በጀልባዎቹ ላይ የተሳፈሩት ኮማንዶዎች የተዘጋጀላቸውን የዋና ልብስ እስከ መነፅሩና ኦክስጂኑ እያጠለቁ ወደ መርከቡ ገቡ። በወርቅ የተሞሉትን በርሚሎችም ለኤክስካቫተር ዶዘሩ ጣቶች እያመቻቹ በመስጠት ጀልባዎቹ ላይ ይቀረቅቡ ጀመር። ስምንቱም ጀልባዎች በበርሚሎች ግጥም ብለው ሞሉ። የሰጠመው መርከብም በርሚሎቹ ወጥተው እንዳለቁ ቋጥኝ እየተዛቀ እንዲሞላበት ተደረገ። በዚሁ ቅፅበት

የሚንጣጣ የተኩስ ድምፅ ይሰማ ጀመር፡፡ ሚራዥና ያገቱት ኮማንዶዎች ግራ በመጋባት ከላይ የሚሰሙትን የተኩስ ልውውጥ አድፍጠው ያደምጡ ጀመር፡፡

"ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀ ሚራዥ ያገቱትን ኮማንዶዎች ግራና ቀኝ እየተመለከተ፡፡ "እርስ በእርስ ተጀማመሩ እንዴ?"

ሁለቱም ነገሩ ስላልገባቸው አልመለሱለትም፡፡

"እንዳትነቃነቅ! የሚሆነውን እስክናጣራ ድረስ ከዚህ ንቅንቅ ማለት የለም!" አለ አንደኛው ቁና ቁና እየተነፈሰ፡፡


ሚራዥ ያላወቀ ይምሰል እንጂ፣ አስቀድሞ በተነደፈው እቅድ መሠረት፣ ስልሳ የሚሆኑ የዴርቶጋዳ አባላት ከዚሁ መርከቡ ከሰጠመበት የድንጋይ ክምር ሁለት መቶ ሜትር ራቅ ብላ በምትገኝ ሰው አልባ ደሴት ውስጥ በጊዜ መጥተው አድፍጠው በመጠባበቅ ላይ ነበሩ፡፡ ማርዬ ዋቆ ማርዬ፣ አድያም፣ ሳዶፍ፣ ኮ/ል አሲጋዝ እና ኪራኮስ የተካተቱበት ይህ ያደፈጠ ቡድን በፈጣን ጀልባዎች ከሁለት መቶ ሜትር በመወንጨፍ ነበር ወርቁን ጭነው ውልቅ ለማለት በማቆብቆብ ላይ ያሉትን ጀልባዎች በተኩስ ያጣደፋቸው፡፡ በሌላ በኩል ዴር33 ከዳጋ ደሴት ተነስታ የጣናን ሰማይ እየሰነጠቀች መጣችና ተኩሱን ተቀላቀለች፡፡ ሚሮዳ በፍ ቅርፅ

የተሠራውን የጨሬሬ. መማሪያ ትቃ ዴር33 ላይ በተጠመደው መትረጊስ ትተጋተግ ጀመር።

ሚራኘርን ግራና ቀኝ ያገቱት ኮማንዶዎች አድፍጠው ምንነቱ ያልገባቸውን የተኩስ ልውውጥ ሲያዳምጡ ከቆዩ በኋላ አንደኛው ወጥቶ ሁኔታውን አጣርቶ እንዲመለስ ተላከ። በዚሁ ቅፅበት ሚራኘር ብቻውን የቀረውን ኮማንዶ እንደነብር ዘሎ ተከመረበት። ኮማንዶውም የዋዛ አልነበረም። ሚራኘርን አንቆ ትንፋሽ አሳጣው። ሁለቱም ተናንቀው ይፈሳፈሱ ጀመር። እንደገመድ ተሸራርበው አንዱ ከላይ አንዱ ከሥር እየሆኑ ቦክስ መሰናዘራቸው ለደቂቃዎች ቀጠለ። በሰሞኑ ውጣ ውረድ የደከመው ሚራኘር ኮማንዶው በተደጋጋሚ ፊቱ ላይ ያሳረፋቸውን ቡጢዎች ሊቋቋማቸው አልቻለም። አጥንቱ የተሰነጠቀ መሰለው። ብዥርታ የጋረዳቸው ዓይኖቹ ሰመመን ውስጥ እንደገባ ታካሚ ዙሪያውን ማዬት ተሳናቸው። የኮማንዶው ቡጢ አልቆመም። በሚራኘር አፍና አፍንጫ ደም ተንገርቀገርቀ። እያቃሰተ ተዘረረ። ቆይቶ... ላፍታ ያህል ዓይኖቹን ገርበብ ሲያደርግ በኤክስካቫተር ዶዘሩ መስታውት ውስጥ እየዋኘ የሚመጣ ሰው ተመለከተ። ኮለኔል ኪሩቤል ነበር። እንደምንም ተጣጥሮ በእግሩ የበሩን ቁልፍ ተጫነለት። ኮለኔል ኪሩቤል እንደ እባብ ተስቦ እንደገባ በሚራኘር ፊት ላይ ተደጋጋሚ ቡጢ የሚያሳርፍበትን ኮማንዶ በፍጥነት

ተጠመጠመበት። ሚራዥር የገባውን ውሃ እየመጠጠ ከኤክስካቫተር ዳዘሩ የሚያስወጣውን ቁልፍ እንደ ምንም ብሎ በመጫን በደመ የተላውን ውሃ አስወጣው። ተንገዳግዶ ሲቃና ከስኤል ኪፋቢል ከማንደውን አጠናቀት ነበር። ከአርባ ደቂቃ በላይ የፈጀው ፈጣን የተኩስ ልውውጥ ተጠናቋል። ከነ ሚራዥር ወገን ሃያ አንድ ሰው ተመቶ ወድቋል። አሥራ ሁለት ሰው ሲቆስል ሲሶቹ ግን ተርፈዋል። በሌላ በኩል ራሱን ጨጪምሮ የኒቆዲሞስ ሰዎች አልቀዋል። ዶን ቦናኖ እና ታዴምስ አንዷን ጀልባ አስነስተው የማምለጥ ሙከራ አድርገው ነበር። ሆኖም ዱር33 ተከትላ ሁለቱንም አስቀርታቸዋለች። የጣናን ሐይቅ በደም ያቀላው ግብግብ እንደተጠናቀቀ ባዶዎቹ ጀልባዎች ቁስለኞቹንና በህይወት የተረፉትን ከጫኑ በኋላ፣ ወርቅ የተሞሉትን ጀልባዎች በማባጀብ ወደ ዳጋ ጉዟቸውን ቀጠሉ። የዳጋ ክርስ ምድር ሀዘንና ደስታ እኩል ሲፈራረቁበት ነጋለት።

⊹ወገግታ… ካልነጋን አይነጋም⊹


ይስማዕከ ወርቁ
ዴርቶጋዳ
ራማቶሐራ
ዮራቶራድ
ISBN_978_999_44_843_5_9
ዋጋ 48.50 ብር